# የሺዓ ኢስላም እምነት
# (ዐቃኢድ ኢማሚያህ)

በ አላማህ ሙሐመድ ሪዳ አል-ሙዘፈር

ትርጉም፡

ጣሂር መሐመድ ዓሊይ አል-ጎዳነምቢ

2003/2011

# የሺዓ ኢስላም እምነት (ዐቂዳ)

በ ሙሐመድ ሪዳ አል-ሙዘፈር

ትርጉም፡

ጣሂር ሙሐመድ ዓሊይ አል-ጎዳነምቢ

እጅግ ርህሩህና

አዛኝ በሆነው

በአላህ ስም

**ማውጫ** **ገጽ**

**መግቢያ.....................................................................1**

1. ዕውቀት የመፈለግ ግዴታና አስፈላጊነት................ 1
2. የተለያዩ የኃይማኖት ቅርንጫፎችን (ፉሩእአል አል-ዲን) በተመለከተ ሌሎችን መከተል (ተቅሊድ) አስፈላጊ ስለመሆኑ.................. 5
3. አመንክዮን በጠበቀ ሁኔታ በኃይማኖት ጉዳዮች ላይ ምክንያታዊ ፍርድ የመስጠት (የኢጅቲሃድ) አስፈላጊነት.................... 7
4. የሙጅተሂድ ደረጃና ቦታ በተመለከተ ያለን እምነት....................................................9

## ክፍል አንድ..........................................11

## ተውሂድ.................................................11

5. በአላህ ማመን................................................11
6. በመለኮታዊ አንድነት (ተውሂድ) ማመን...............14
7. የአላህ ባህሪያትን በተመለከተ ያለን እምነት..........18
8. የአላህ ፍትሃዊነትን በተመለከተ ያለን እምነት.......22
9. የአላህን ትዕዛዛት በተመለከተ ያለን እምነት..........27

10.ቀዳእና ቀደርን (ቅድመ-ውሳኔና መለኮታዊ
ፍርድን) በተመለከተ ያለን እምነት…………………..28
11.በደዕ («የሐሳብ ለውጥ») አስመልክቶ
ያለን እምነት…………………………………………33
12.ህግጋትን ወይም መመሪያዎችን
በተመለከተ ያለን እምነት………………………...37

**ክፍል ሁለት……………………………………40**

**ኑቡወህ (ነቢይነት)……………………………...40**

13. ነቢይነትን አስመልክቶ ያለን እምነት……………..40
14.ነቢይነት (ኑቡወህ) ከመለኮታዊ ፀጋ
(ሉጥፍ) ነው፡፡………………………………………..42
15.ነቢያዊ ተዓምራትን በተመለከተ
ያለን እምነት…………………………………………49
16.የነቢያትን እንከን-የለሽነት (ዕስማህ)
በተመለከተ ያለንእምነት…………………………….53
17.የነቢይን ባህሪያት አስመልክቶ ያለን እምነት……...56
18.ነቢያትንና መጽሐፍታቸውን
በተመለከተ ያለን እምነት…………………………...57
19.ኢስላምን በተመለከተ ያለን እምነት………………..58

20.የኢስላም ህግ ሰጭ (ሙሽሪዕ)
አስመልክቶ ያለን እምነት..............................65
21.በቁርአን ማመን..........................................66
22.ኢስላምንና ቀደምት ኃይማኖቶችን
የማረጋገጫ መንገድ......................................69

**ክፍል ሶስት..........................................79**

**አል-ኢማማህ (የነቢዩ ተተኪዎች መሪነት)......79**

23.የነቢዩ ተተኪዎች መሪነት (አል-ኢማማህ)
አስመልክቶ ያለን እምነት..............................79
24. የኢማም እንከን-የለሽነት (ዕሰማህ)
በተመለከተ ያለን እምነት...............................83
25.የኢማም ባህሪያትና ዕውቀትን በተመለከተ
ያለን እምነት................................................84
26.ለኢማሞች መታዘዝን አስመልክቶ ያለን
እምነት........................................................88
27.ለነቢዩ ቤተ-ዘሮች (አህለል ቤይት)
ውዴታን አስመልክቶ ያለን እምነት...................94
28.ስለ ኢማሞች ያለን እምነት...............................98
29.የመሪነት ስልጣን (ኢማማህ)
ከአላህ መሆን አለበት...................................99

30.የኢማሞችን ቁጥር (ብዛት)

አስመልክቶ ያለን እምነት..............................103

31.መህዲን አስመልክቶ ያለን እምነት...................105

32.ረጅዓህ (ሙታን ህይወት ዘርተው

ወደ ሕያውነት መመለስን)

አስመልክቶ ያለን እምነት..............................112

33.ተቂያ (ለአደጋ የሚያጋልጥ ነገር

ሲኖር ራስን ደብቆ የመኖር

ጥበብን) በተመለከተ ያለን እምነት...................122

**ክፍል አራት.........................................128**

**የነቢዩ ቤተ-ዘሮች አስተምህሮ**

**ለተከታዮቻቸው (ለሺዓዎቻቸው)................128**

**መግቢያ.....................................................128**

34.ዱዓን በተመለከተ ያለን እምነት......................130

35.ከአል-ሰሒፈህ አል-ሰጃዲያህ ዱዓዎች

የሚገኙ ዋና ዋና መልዕክቶች..........................143

36.የመቃብር ቦታዎችን መጎብኘት/ዚያራ

አስመልክቶ ያለን እምነት..............................167

37.የ«ሺዓ» ትርጉም በነቢዩ ቤተ-ዘሮች እይታ.........179

38.በደልና ጭቆናን አስመልክቶ ያለን እምነት.........187
39.ከጨቋኞች ጋር መተባበርን
አስመልክቶ ያለን እምነት..............................192
40.በጨቋኝ መንግስት ሐገር ውስጥ
መስራትን አስመልክቶ ያለን እምነት.................197
41.ለኢስላማዊ አንድነት መጣራትን
አስመልክቶ ያለን እምነት..............................200
42.ሙስሊም በሙስሊም ላይ ያለውን መብት
በተመለከተ ያለን እምነት (የሙስሊሞች
የወንድማማችነት መብትና ግዴታ)...................210
**ክፍል አምስት.......................................221**
**አል-መዓድ (ትንሳዔ)...............................221**
43.ከሞት መነሳት (ትንሳዔ) አስመልክቶ
ያለን እምነት..............................................221
44.አካላዊ ትንሳዔ (አል-መዓድ አል-ጂስማኒ)
በተመለከተ ያለን እምነት...............................222

## መግቢያ

### 1. ዕውቀት የመፈለግ ግዴታና አስፈላጊነት

በመላው ዩኒቨርስ ውስጥ የሚኙትን አጠቃላይ ፍጥረታትና በውስጣችን ያለውን ሥነ-ፍጥረት እንድንመረምር፣ የሀያሉ አላህ ኃይልና ክብር መገለጫ ምልክቶችን በጥንቃቄ እንድናጤንና እንድንረዳ ይረዳን ዘንድ ጥበበኛው አላህ ማሰቢያ አዕምሮ እንደለገሰን እናምናለን፡፡ በቁርአን ውስጥ እንደሚከተለው ተጠቅሷል፡፡

سَنُرِيهِمْ آيَاتِنَا فِي الْآفَاقِ وَفِي أَنْفُسِهِمْ حَتَّىٰ يَتَبَيَّنَ لَهُمْ أَنَّهُ الْحَقُّ أَوَلَمْ يَكْفِ بِرَبِّكَ أَنَّهُ عَلَىٰ كُلِّ شَيْءٍ شَهِيدٌ

«*እርሱም (ቁርአን) እውነት መሆኑ ለእነርሱ እስከሚገለፅላቸው ድረስ በአጽናፎቹ ውስጥና በነፍሶቻቸውም ውስጥ ያሉትን ተዓምራቶቻችንን በእርግጥ እናሳያቸዋለን፡፡ ጌታህም እርሱ በነገሩ ሁሉ ላይ ዐዋቂ መሆኑ አይበቃቸውምን?*» (41፡53)

የቀደምት አባቶችን መንገዶች በጭፍን የሚከተሉትን ትውልዶች አላህ እንደወቀሳቸውና ይህ ተግባራቸው ትክክል እንዳልሆነ በቁርአኑ ያሳየናል፡፡

وَإِذَا قِيلَ لَهُمُ اتَّبِعُوا مَا أَنْزَلَ اللَّهُ قَالُوا بَلْ نَتَّبِعُ مَا أَلْفَيْنَا عَلَيْهِ آبَاءَنَا أَوَلَوْ كَانَ آبَاؤُهُمْ لَا يَعْقِلُونَ شَيْئًا وَلَا يَهْتَدُونَ

«*ለእነርሱም «አላህ ያወረደውን ተከተሉ» በተባሉ ጊዜ «አይደለም አባቶቻችንን በርሱ ላይ ያገኘንበትን ነገር እንከተላለን» ይላሉ፡፡ አባቶቻቸው ምንም የማያውቁና (ወደ እውነት) የማይመሩም ቢሆኑ (ይከተሉዋቸዋልን?)*» (2፡170)

በተጨማሪም የራሳቸውን የግል ፍላጎትና ስሜት እንጂ ሌላ ምንም የማይከተሉ ሰዎችን ሲገልጽ አላህ በቁርአን እንዲህም ብሏል፡-

إِن يَتَّبِعُونَ إِلَّا الظَّنَّ

«*ጥርጣሬን እንጅ ሌላን አይከተሉም፡፡*» (6፡116)

ልክ የአንድን ነቢይ የነቢይቱን ተገቢነትና የተዓምራቱን ተዓማኒነት መመርመር እንዳለብን ሁሉ በእርግጥ የዩኒቨርስን ፈጣሪ ለማወቅ በፍጥረታት ላይ እንድንመራመር አዕምሮአችን ያስገድደናል፡፡ የአንድን ሰው ሐሳብና አስተሳሰብ ያለምንም ጥያቄና ትችት በደፈናው መቀበል አግባብነት የለውም፡፡ ይህ ሰው የመጠቀ የዕውቀት ስጦታ የተጎናጸፈ ቢሆንና እጅግ የተከበረ ቦታ የተሰጠው ሰው እንኳ ቢሆን ሐሳቡን ያለምንም ጥያቄ በጭፍን መቀበል የለብንም፡፡ ለአእምሮአችን ተገቢውን ቦታና ዋጋ መስጠት ግድ ይለናል፡፡

ቁርአን በፍጥረታት ላይ እንድንመራመርና ስለፍጥረተ ዓለሙ ዕውቀት እንዲኖረን አጥብቆ የሚናገረው የሰውን ልጅ ተፈጥሮአዊ የማሰብና የማወቅ ነፃነት ጋር እንዲጣጣምና የሰው ልጅ የመረዳትና የማሰብ ኃይልን በማደስ የተፈጠረለትን ዓላማ አውቆ ግቡን ለመምታት እንዲችል ለማነሳሳት ነው፡፡

ስለዚህ አንድ ሰው የእምነቱን መሠረቶች ወደ ኋላ ትቶ መምህራኖቹ ወይም ሌሎች ሰዎች በሚነግሩት ነገሮች ላይ ብቻ መተማመን ትክክል አይደለም፡፡ ይልቁንስ በቁርአን እንደተረጋገጠው አንድ ሰው የተፈጥሮ አዕምሮውን ተጠቅሞ በመመራመር፣ በመጠየቅና በማሰብ የኃይማኖት መሠረታዊያንን (ኡሱል አል-ዲን) በተመለከተ ግልጽ የሆነ መረዳት ላይ መድረስ አለበት፡፡ ከነዚህ መሠረታዊያን በኢስላም ውስጥ እጅግ አስፈላጊ የሆኑት ደግሞ፣ የአላህ አንድነት (ተውሂድ)፣ የነቢይ ሥርዓት (ኑቡወህ)፣ ኢማምነት/መሪነት (ኢማማህ) እና ትንሳኤ (መዕድ) ናቸው፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ የቀደምት ሰዎችንም ሆነ የሌሎች ሰዎችን አስተምሮ በጭፍን የሚከተል ሰው በትልቅ ስህተት ውስጥ የተዘፈቀና ከቀጥተኛው ጎዳና ያፈነገጠ ሰው ነው፡፡ ለእንዲህ ዓይነቱ ሰው ደግሞ ምንም ዓይነት ይቅርታ የለም፡፡

በአጭሩ ሁለት ነጥቦች እናገኛለን፡-

1. የእምነታችንን መሠረታውያን መመራመርና መረዳት እንዳለብንና ሌሎች የሚሉትን ፍጹም መከተል እንደሌለብን፡፡ ይህም ማለት ዐቂዳን በተመለከተ

ተቅሊድ ማድረግ እንደማይገባንና ማወቅና መመራመር እንዳለብን፣

2. ይህ ዕውቀት የግድ ከኃይማኖት መገኘት ሳይሆን ከአእምሮ የሚመነጭ መሆኑ (እንዲህ ዓይነቱ ዕውቀት ከኃይማኖት መጽሐፍት የሚገኝ ብቻ አይደለም፣ እንደሚታወቀው የኃይማኖት አስተምሮዎች ይህንኑ የሚያረጋግጡ ቢሆንም ይህ ዕውቀት የሚመነጨው ከአዕምሮአዊ ምርምርም ነው፡፡) "ከአእምሮ/ ምክንያታ-ዊነት የሚመነጭ መመዘኛ ነው" ማለት ይህንን ጉዳይ እራሳችን ተመራምረን ዕውቀቱን እንድናገኝ አዕምሮአችን ይረዳናል ለማለት ነው፡፡

## 2. የተለያዩ የኃይማኖት ቅርንጫፎችን (ፉሩእአል አል-ዲን) በተመለከተ ሌሎችን መከተል (ተቅሊድ) አስፈላጊ ስለመሆኑ

የኃይማኖት ቅርንጫፎች የሚባሉት ከተግባር ጋር የተያያዙ ኃይማኖታዊ ህግጋት (ሸሪዓ) ሲሆኑ ግለሰባዊ ምርምርና አመንክያዊ ገለጻ (ኢጅቲሃድ)

የማያስፈልጋቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህን በተመለከተ እያንዳንዱን ሰው ቀጥሎ የቀረቡትን ሦስት አማራጮች መውሰድ ይችላል፡፡

i. የሙጅተሂድ ደረጃ እስኪጎናጸፍ ድረስ ለፍቶና ግሮ ማጥናት

ii. ከቻለ ደግሞ ህጉን በተከተለ መልኩ በጥንቃቄ የተሻለውን አማራጭ በመውሰድ (ኢህቲያጥ) ማድረግ

iii. በሙጅተሂድነት የታወቀን ሰው መከተል፡፡ ሙጅተሂድ በጥበብ የተሞላና ፍትሃዊ ሰው መሆን ይኖርበታል፡፡ እራሱን ከኃጢአት የሚጠበቅ፣ የግል ስሜትና ፍላጎቱን የማይከተልና የአላህን ትዕዛዛትና መመሪያ የሚታዘዝ መሆን አለበት፡፡

ከዚህ የምንረዳው ታዲያ እራሱ ሙጅተሂድ ያልሆነ ወይም ደግሞ ኢህቲያጥን የማይተገብር፣ ካልሆነ ደግሞ ሙጅተሂድን የማይከተል ሰው ኃይማኖታዊ ተግባሩ ከንቱ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ህይወቱን በሙሉ እነዚህን ተግባራት በመፈጸም ያሳለፉ ቢሆን እንኳ ሰላቱም ሆነ ጾሙ አላህ ዘንድ ተቀባይነት አይኖራቸውም ማለት ነው፡፡ ሙጀተሂድን መከተል ሲጀምር ግን ከዚህ በፊት

ለአላህ ብሎ የሠራቸው ነገሮች ተቀባይነት ያገኛሉ፡፡ ሙጀተሂድን ሳይከተል ህይወቱን ሙሉ ቢለፋ ግን ተግባሩ ሁሉ ከንቱ ይሆናል፡፡

## 3. አመንክዮን በጠበቀ ሁኔታ በኃይማኖት ጉዳዮች ላይ ምክንያታዊ ፍርድ የመስጠት (የኢጅቲሃድ) አስፈላጊነት

ኢማም በሌለበት በኃይማኖት ጉዳዮች ላይ ኢጅቲሃድ ማድረግ በሁሉም ሙስሊሞች ላይ የወል ግዴታ (ዋጂብ አል-ኪፋኢ) መሆኑን እናምናለን፡፡ ይህም ማለት ከሙስሊሞቹ የሆነ አንድ ሰው የኢጅቲሃድ ደረጃን ተጎናጽፎ ሙጅተሂድ ለመሆን ከበቃ ሌሎቹ ሙስሊሞች በኃይማኖት ቅርንጫፎች ላይ ሙጅተሂዱን መከተል ይበቃል፡፡

ሁሉም ሙስሊሞች ዕውቀትን ለመገብየትና የሙጅተሂድ ደረጃን ለመቆናጠጥ በጽኑ መታገል አለባቸው፡፡ ይህ ካልተቻለ ደግሞ ከአባላቸው አንዱ ይህንን ደረጃ እንዲያገኝ የተቻለውን ሁሉ ድጋፍ መስጠትና

ማበረታታት ይኖርባቸዋል፡፡ በህይወት ያለ ሰው የሙጀተሂድን ቦታና ደረጃ መያዝ ካልቻለ በህይወት የሌለን ሰው ሙጀተሂድ አድርጎ መያዝና መከተል አይፈቀድም፡፡

ኢጅቲሃድ ማለት ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ያመጡት፣ጊዜና ሁኔታዎች የማይሽራቸው መመሪያዎችንና ትዕዛዛትን (አል-አህካም አል-ፈርዕያህ) በተመለከተ በቂ ዕውቀት ለማግኘት የሸሪዓ ምንጮችን ማጥናትና መፈተሽ ማለት ነው፡፡ የሚከተለው ሐዲስ ይህንኑን ያረጋግጣል፡-

"*ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ሐላል ያደረጉት እስከ ፍርድ ቀን (የውም አልቂያማ) ድረስ ሐላል ይሆናል፣ እሳቸው ሐራም ያደረጉትም እስከ ፍርድ ቀን ድረስ ሐራም ይሆናል፡፡*"

እነዚህ የሸሪዓ ምንጮች ቁርዓን፣ (የነቢዩ እና የኢማሞቹ) ሱና፣ ስምምነት (ኢጅማእ) እና ምክንነታዊ አስተሳሰብ (ዐቅል) ናቸው፡፡ እነዚህ በሙሉ በኡሱል አል-ፊቅህ መጽሐፍት ተጠቅሰዋል፡፡ የሙጅተሂድ ደረጃ ማግኘት የብዙ ዓመታት ትምህርትና ምርመር የሚያስፈልግ ሲሆን

እጅግ ታታሪና ጠንካራ ሰው ካልሆነ በስተቀር ልደረስበት የማይቻል ወሳኝ ቦታ ነው፡፡

## 4. የሙጅተሂድ ደረጃና ቦታ በተመለከተ ያለን እምነት

መስፈርቶቹን አሟልቶ የሙጀተሂድ ደረጃ የተቆናጠጠ ሰው *ሙጀተሂድ* የሚባል ሲሆን ኢማም በሌለበት የኢማሙ ተወካይ ሆኖ የሚሰራ ነው፡፡ ስለዚህ ሙጀተሂድ በመላው ሙስሊም ላይ ስልጣን ያለውና በሰዎች መካከል ያለውን የፍርድና የአስተዳደር ተግባራትን በተመለከተ በኢማሙ ቦታ ሆኖ ኃላፊነቱን የሚወጣ ሹም ነው ማለት ነው፡፡ በዚህ ምክንያት ኢማም ጀዕፈር አል-ሳዲቅ (ዐ.ሰ) ሲናገሩ፡-

*"የሙጅተሂድን ስልጣን መካድ ማለት የኢማምን ስልጣን መካድ ማለት ነው፣ የኢማሙን ስልጣን መካድ ማለት ደግሞ የአላህን ስልጣን መቃወም ማለት ነው፡፡ ይህ ደግሞ በሽርክ ውስጥ ከፍተኛውን ቦታ የያዘ ነው፡፡"*

ስለዚህ ሙጅተሂድ ፈትዋዎችን (ለኃይማኖታዊ ጥያቄዎች መልስ የሚሰጥ) የሚያደርግ ብቻ ሳይሆን በሙስሊሞች ላይ ሙሉ ስልጣን ያለውና ፍርድ-ነክ ጉዳዮችን በተመለከተ ሙስሊሙ በሙሉ ማማከር የሚገባው መሪ ነው፡፡

በመሆኑም ከሙጅተሂዱ ወይም ሙጅተሂዱ ከወከሉት ሰው በስተቀር ከሌላ ሰው ፍርድ መጠየቅም ሆነ ማግኘት ህገ-ወጥ ነው፡፡ ከሙጅተሂዱ ፈቃድ ውጭ ማንም ሰው ብይን መስጠት አይችልም፡፡ እንዲሁም ለኢማሙ መሰጠት የሚገባ ማንኛውም ነገር ለሙጅተሂዱ መሰጠት አለበት፡፡

እንዲህ ዓይነቱ ስልጣን በኢማሙ ለሙጅተሂዱ የተሰጠበት ምክንያት ሙጀተሂዱ ኢማሙ በሌሉበት ወኪል ሆኖ እንዲያገለግል ነው፡፡ ስለዚህም የኢማሙ ተወካይ (ናኢብ አል-ኢማም) በመባል ይታወቃል፡፡

# ክፍል አንድ

# ተውሂድ

## 5. በአላህ ማመን

አላህ አንድ (ዋሂድ)፣ ብቸኛ (አሀድ)፣ አምሳያ የሌለው (ለይሰ ከሚስሊሂ ሸይእ)፣ ዘለዓለማዊ (ቃዲም)፣ መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው መሆኑን እናምናለን፡፡ እሱ የመጀመሪያና የመጨረሻው (አል-አወል ወል አኺር) ነው፡፡ እሱ ሁሉን አዋቂ (አል-ዓሊም) ጥበበኛ ፣ፍትሃዊ (አል-ዓዲል)፣ ህያው (አል-ሐይ)፣ ሁሉን ቻይ (አል-ቃዲር)፣ ከሁሉም ነገር የተብቃቃ (አል-ገንይ)፣ ሁሉን ሰሚ (አስ-ሰሚዕ) ፣ ሁሉን የሚያይ (አል-በሲር) ነው፡፡

እርሱ በፍጥረታቱ አይመሰልም፣ ስለዚህ እሱ አካልም ሆነ ገጽታ፣ ግብአትም ሆነ ፎርም የለውም፣ ከባድ ወይም ቀለል አይባልም፣ ተንቀሳቃሽም ሆነ እንቅስቃሴ አልባ

ተብሎ አይገለጽም፣ በጊዜና ቦታ አይገደብም (ጊዜና ቦታ የለውም)፣ ማንም ወደ እሱ ሊያመላክት አይችልም፣ እሱን የሚመስል አንዳችም ነገር የለም፡፡ ከሱ ጋር የሚስተካከል አንዳችም ነገር የለም፣ የሚቃረነውም አንድም ነገር የለም፡፡ እሱ ሚስት የለውም፣ ልጅ የለውም፣ አጋር አያሻውም፣ ከሱ ጋር የሚወዳደርና የሚነጻጸር ምንም ነገር የለም፡፡ እርሱን ምንም እይታ ሊይዘው አይችልም፣ እርሱ ግን ሁሉንም ያያል፡፡

እሱን በፍጡራኑ የሚመስል ማንኛውም ሰው፣ ለምሳሌ አላህ ፊት አለው፣ እጆች አሉት፣ ዓይኖች አሉት ወይም ደግሞ ወደ ዝቅተኛው መሬት ይወርዳል፣ ወይም ደግሞ በጀነት ውስጥ ለህዝቡ እንደ ጨረቃ ይታያል ወዘተ… ብለው የሚያስቡ ሰዎች በአላህ የማያምኑና የአላህን ትክክለኛ ባህሪ ያልተረዱ ናቸው፡፡ አላህ ከሁሉም እንከን የላቀና የጠራ ጌታ ነው፡፡

በምናባችን የምንስለውና የምናስበው ነገር በሙሉ እንደኛው ስለሆኑ ፍጥረታት ብቻ ነው፡፡ ይህንን በሚመለከት ኢ.ማም ባቂር (ዐ.ሰ) ሲናገሩ፡-

*“እሱ ከጥበበኞች ገለጻ የላቀ፣ የረቀቀና የመጠቀ ዕውቀት (ዕልመል ደቂቅ) የማይደርስበት ነው፡፡”*

በተመሳሳይ መልኩ በፍርዱ ቀን በፍጥረታቱ ይታያል ብለው የሚያምኑ ሰዎች ኢ-አማንያን (ከሃዲዎች) ናቸው፡፡ አላህን በፍጡራን ባይመስሉ እንኳን እንዲህ በማሰባቸው ከ ከሃዲዎች ጎራ ይመደባሉ፡፡

እነዚህ አስመሳዮች የቁርአንን መልዕክትና የነቢዩን ሐዲስ አዕምሮአቸውን ሳይጠቀሙ በጭፍን የተቀበሉ መኃይማን ናቸው፡፡

እነዚህ በእርግጥ አዕምሮአቸውንና አቅላቸውን ላለመጠቀም የመረጡና በቋንቋ ተፈጥሮ ውስጥ አይቀሬ የሆነውን ምሳሌያዊ አነጋገርና ዘይቤን እንዲሁም አውደ ትርጉምን መረዳት አሻፈረን ያሉ ደካሞች ናቸው፡፡ በመሆኑም የቁርአንና ሐዲስን ትክክለኛ ትርጉም በተሳሳተ መልኩ የተረዱ ናቸው፡፡

## 6. በመለኮታዊ አንድነት (ተውሂድ) ማመን

የአላህ አንድነት (ተውሂድ) በሁሉም አቅጣጫና ሁናቴ መሆን እንዳለበት እናምናለን፡፡ በግኝቱ ወይም በማንነቱ አንድ እንደሆነ ሁሉ (ተውሂድ ዛቲ)፣ በህልውናውና በክሰቱም (ውጁብ አል-ውጁድ) አንድ እንደሆነ እናምናለን፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ቀጥሎ ለማብራራት እንተሞከረው አላህ በባህሪያቱም አንድ እንደሆነና ይህም አንድነቱ ከዛቱ ጋር አንድ እንደሆነ እናምናለን፡፡
እንደዚሁም በባህሪያቱ አንዳችም አምሳያ እንደሌለው እናምናለን፡፡

ለዕውቀቱና ችሎታው ወደር የለውም፣ ፍጥረታትን በማስገኘትም ሆነ ለፍጥረታቱ በመለገስ ረዳትና ሸሪካ የለውም፡፡ ስለዚህ በማናቸውም ሁኔታና እንከን የለሽነቱ የሚመስለው የለም፡፡ በሦስተኛ ደረጃ አንድነቱ በአምልኮ ረገድም መገኘት አለበት፡፡ በመሆኑም ከሱ ውጭ ለሌላ ለማንም ለምንም አምልኮ አይገባም፡፡ እንደ ፀሎት ወይም ዱአዕ ባሉ ግዴታ ባልሆኑ የአምልኮ ተግባራት

ከአላህ ውጭ ለማንም ማጋራት የለብንም፡፡ አላህን በአምልኮ ረገድ ከሌላ ነገር ጋር የሚያጋራ ሰው በብዙ አማልክት አማኝ (ሙሽሪክ) ነው፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ሰው አላህን የሚያመልክ እንደሆነ በማስመሰል አምልኮን ለሌላ ነገር ያካፈለ በአላህ የሚያጋራ ሰው ነው፡፡ በኢስላም እይታ እንዲህ ዓይነቱ ሰው ከጣዖት አምላኪዎች ጎራ የሚመደብ ነው፡፡

ነገር ግን አንዳንድ ሰዎች ያለምንም ኃይማኖታዊ ማስረጃ ሺዓዎችን ለመዋጋት ሐሰቱን እውነት አድርገው ለመቅጠፍ ቢሞክሩም፣ የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እና የኢማሞች (ዐ.ሰ) መካነ መቃብር የመሳሰሉ ቅዱሳን ቦታዎች መጎብኘት (መዘየር)ና በለቅሶ ሀዘንን መግለጽ ከሽርክ ተግባራት ውስጥ የሚመደብ አይደለም፡፡ እነዚህ ሰዎች ከጉብኝቱ ወይም ዚያራው ጀርባ ያለውን ምክንያት ያጤኑና የተረዱ አይመስልም፡፡

እነዚህ ተግባራት ወደ አላህ የመቃረቢያ መልካም ሥራዎች መሆናቸውን አልተረዱም፡፡ በሽተኛን በመጠየቅ፣ ሬሳን በመሸኘት፣ ወንድሞቻችንን በመጠየቅ/

በመዘየርና ደኃዎችን በመርዳትና በመሳሰሉት መልካም ተግባራት ወደ አላህ መቃረብ እንደምንችል ሁሉ ቅዱሳን ቦታዎችንም መጎብኘት ለተመሳሳይ ግብ መሆኑን በውል አልተረዱም፡፡ ለምሳሌ የታመመን ሰው መጠየቅ አንድ አማኝ ወደ አላህ የሚቃረብበት በጎ ተግባር ነው፡፡ የታመመውን ሰው ለማምለክና ለማክበር አይደለም፡፡ ስለዚህ የሽርክ ተግባር ሊሆን አይችልም ማለት ነው፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ እንደዚያራ (ጉብኝት)፣ ለቅሶ (ሐዘን)፣ በቀብር ሥነ-ሥርዓት ላይ መሳተፍና ከወንድሞቻችን ጋር መገናኘት… የመሳሰሉ ተግባራት በሽርክ ተግባራት ውስጥ ሊመደቡ አይችሉም፡፡ በተጨማሪም ከኃይማኖታዊ ህግጋት ትምህርት (ዕልም አል-ፊቂቅ) መረዳት እንደሚቻለው የመቃበር ሥፍራዎች መጎብኘትና በሐዘን ሥነ- ሥርአትን ላይ መገኘት ወይም ለቅሶ በኢስላም ውስጥ ከመልካም ተግባራት ጎራ እንደሚመደቡ ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ ሆኖም በዚህ ጉዳይ ላይ ወደ ዝርዝር ለመግባት ይህ ቦታው አይደለም፡፡

በአጭሩ አንዳንድ ሰዎች እንደሚያስቡት ሳይሆን እነዚህ ተግባራት የሽርክ ተግባራት አይደሉም፡፡ ከነዚህ

ተግባራት ጀርባ ያለው ዓላማ ኢማሞቹን ማምለክ አይደለም፡፡ ይልቁንስ ዓላማው የኢማሞቹ (ዐ.ሰ.) ድንቅ ተግባራትን በመዘከር ገድላቸው ህያው ሆኖ እንዲያንሰራራ፣ ታሪካቸውን በሰዎች አዕምሮ ውስጥ ቀርጾ ለማቆየትና የኃይማኖቱን መገለጫዎች/ምልክቶች ለማክበርና ለማላቅ ነው፡፡

ذَٰلِكَ وَمَنْ يُعَظِّمْ شَعَائِرَ اللَّهِ فَإِنَّهَا مِنْ تَقْوَى الْقُلُوبِ

«*(ነገሩ) ይህ ነው፡፡ የአላህንም የሃይማኖት ምልክቶች የሚያከብር ሰው እርሷ ከልቦች የሆነች ጥንቃቄ ናት፡፡*» (22፡32)

በኢስላማዊ ህግ (ሸሪዓ) ውስጥ እንደተገለጸው እነዚህ ተግባራት የሚወደዱና የሚበረታቱ (ሙስተሐብ) ናቸው፡፡ አንድ ሰው እነዚህን ተግባራት የሚፈጽመው ዓላማውን የአላህ ውዴታን ለማግኘት አደርጎ ከሆነ ለበጎ ሥራው ሽልማት ያገኝበታል፡፡

## 7. የአላህ ባህሪያትን በተመለከተ ያለን እምነት

ሁሉን አዋቂነት (ዒልም)፣ ሁሉን ቻይነት (ቁድረህ)፣ ተብቃቂነት(ጊና)፣ መለኮታዊ ፈቃድ(ኢራዳህ)፣ ዘለዓለማ-ዊነት (ሀያህ)እና የመሳሰሉ የውበትና የፍጹምነት ባህሪይ (ሲፈት አል ጀማል ወል ከማል) ብለን የምንጠራቸው የአላህ መሠረታዊ፣ አዎንታዊ ገዛዳዊ ባህሪያት (አስ-ሲፋት አስ-ሱቡቲያህ አል-ሐቂቅህ) ተጨማሪ ወይም ተደራቢ ባህሪያት ሲሆኑ ከኀልውናው (ዛት) ጋር አንድና አንድ ናቸው፡ ፡ ስለዚህ ባህሪያቱ ከህልውናው (ዛት) ተለይተው አይታዩም፡፡ ስለዚህ ሁሉን ቻይነቱ በዘለዓማዊነቱ ላይ የተመሰረተና ዘለዓለማዊነቱም በሁሉን ቻይነቱ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ሁሉን ቻይ ነው፣ ምክንያቱም ዘለዓለማዊ ነውና፤ ዘለዓለማዊ ነው፣ ምክንያቱም ሁሉን ቻይ ነውና፡፡ በእርግጥ በእሱና በባህሪያቱ መካከልም ሆነ በፍጹም ባህሪያቱ መካከል ጥንድነት ወይም ጣምራነት የለም፡፡ እንደ አንድነት /ውህደት መታየት አለባቸው፡፡ በትርጉማቸውና በሚሰጡት ስሜት ይለያያሉ፤ በምንነታቸውና ህልውናቸው አይለያዩም፡፡ በምንነታቸውና ህልውናቸው የተለያዩ ቢሆኑ ኖሮና ልክ እንደ አላህ ህልውና (ዛት) ቀዳሚና ኀያው ናቸው ተብሎ ቢታሰብ የአላህ መገኘት /ክስተት (ውጁብ አል-ውጁድ) ራሱ በቁጥር /ድግግሞሽ

የሚገለጽ በሆነ ነበር፡፡ ይህ ደግሞ የተውሂድን መሠረተ ሐሳብ ከመሰረቱ የሚያጠፋ አስተሳሰብ ነው፡፡

ነገር ግን ከፍጹምነት ባህሪይ ውጭ ያሉ አዎንታዊ ባህሪያት (እንደ ፈጣሪነት) (ኻሊቂያህ)፣ ለጋስነት (ራዚቂያህ)፣ መጀመሪያ-የለሽነት (ተቀዱም)፣ (የመጀመሪያ) አስገኚነት (ዒሊያህ) የመሳሰሉ በሁለተኛ ደረጃ ያሉ አዎንታዊ ባህሪያት (አስ- ሲፋት አስ-ሱቡቲያህ አል-ኢዷፊያህ) በአንድ ባህሪይ ውስጥ የሚጠቃለሉ ሲሆኑ ይኸውም በተብቃቂነት (ቀይዩሚያህ) ባህሪይ ውስጥ የሚዋጡ ናቸው፡፡

የዚህ ባህሪይ መገለጫና ምልክቶች የሆኑትን ሌሎች የተለያዩ ባህሪያትን ስናስተውል ከመሠረታዊ/አቢይ ባህሪው ውስጥ በማውጣት እንገልጻቸዋለን ማለት ነው (ለምሳሌ የተብቃቂነት ባህሪውን ከፈጣሪነት ረገድ ስናገኝ ፈጣሪ ብለን እንጠራዋለን ማለት ነው፡፡)

ከዚህ በተቃራኒው ደግሞ የልቅና ባህሪያት (ሲፈቱል ጀላል) ተብለው የሚጠሩት አሉታዊ ባህሪያት በሙሉ

በአንድ አቢይ አሉታዊ ባህሪይ ውስጥ የሚጠቃለሉ ሲሆኑ ይኸውም የአሉታዊ ባህሪያትን የመከሰት እድል (ኢ.ምካን) በመስለብ ውስጥ የሚካተቱ ናቸው፡፡ ይህም ማለት እሱ አላህ አካል የሌለው፣ ገጽታ የሌለው፣ እንቅስቃሴ አልባም ያልሆነ፣ ክብደትም ሆነ ቅለትም የሌለው ወዘተ... ነው፡፡ በእውነቱ ፍጹም ባልሆነ ነገር ወይም እንከን ባለው ነገር ስለማይገለጽ እነዚህ ባህሪያት የሉትም ማለትም ነው፡፡ እነዚህን ባህሪያት የመንሳት/የመስለብ ውጤቱ ዞሮ ዞሮ ወደ ህልውናው/ግኝቱ አስፈላጊነት (ውጁብ አል-ውጁድ) የሚመለስ ሲሆን ይህ ደግሞ ከአዎንታዊ የፍጹምነት ባህሪያት አንዱ ነው፡፡ ስለዚህ የልቅና አሉታዊ ባህሪያት በመጨረሻው ወደ አዎንታዊ የፍጹምነት ባህሪያት ስለሚያመሩ ዞሮ ዞሮ አላህ በሁሉም ሁናቴ አንድ ነው ማለት ነው፡፡ ቅዱስ ህልውናው በቁጥር አይገለጽም፣ በመገኘቱ ውስጥ ጥንድነት/ጣምራነትም የለም፡፡

አንዳንድ ሰዎች አዎንታዊ ባህሪያት በአሉታዊ ባህሪያት ውስጥ የሚንፀባረቁ መሆናቸውን ቢቀበሉም የአላህ ባህሪያት አንድነትን መረዳት ባለመቻላቸው፣ የአላህን አንድነት ለራሳቸው ለማረጋገጥ ሲሉ አዎንታዊ ባህሪያቱ በአሉታዊ ላይ የተመሰረቱ ናቸው ብለው ማሰባቸው

ብዙም የሚያስደንቅ አይደለም፡፡ ነገር ግን በዚህ አስተሳሰባቸው ትልቅ ስህተት ውስጥ ለመውደቅ በቅተዋል፡፡ ምክንያቱም የአላህ ኀልውና ፍጹምና ከእንከን ሁሉ የላቀ ሆኖ ሳለ በነሱ አስተሳሰብ መሰረት ግን ሁሉም ባህሪያት በአሉታዊ ባህሪይ ወይም በባህሪ አልባነት ስለሚገልጽ፣ ስለዚህም በየለምነት ወይም የለም የሚለው መደምደሚያ ላይ ይደርሳሉ፡፡

በተመሳሳይ መልኩ አንዳንድ ሰዎች ደግሞ አዎንታዊ ባህሪያቱ በግኝቱ (ዛቱ) ላይ ተጨማሪ (ኢዳፋህ) ናቸው ብለው በማሰብ በዚህም ደግሞ ባህሪያቱም እንደ ዛቱ ቀድመው ያሉ እንደሆኑ በማሰብ ባህሪያቱ ከህልውናው ጋራ የተጣመሩ/ሽርክ ናቸው ወደሚለው መደምደሚያ ይደርሳሉ፡፡ እንዲሁም ሌሎች ሰዎች ደግሞ አላህ የባህሪያቱ ውህድ ነው ብለው ያምናሉ፡፡ አላህ ግን ከዚህ ሁሉ መገለጫ የጠራና የላቀ ነው፡፡

የመጀመሪያው ኢማም አሚሩል ሙዕሚኒን ዓሊ ሲናገር፡-

*«የጥራቱ ፍጹምነት መገለጫው ከሱ ባህሪያትን ማክሰም ነው፡፡ ባህሪያት ሁሉ ባህሪውን ሊገልጹ አይችሉምና፡፡*

*በባህሪ ከሚገለጽ ነገር ሁሉ ጋር አይመሳሰልም፡፡ ማንኛውም ገላጭ ባህሪይ ከተገላጩ ይለያልና፡፡ ስለዚህ አላህን በባህሪያት የገለፀ ከሌላ ነገር ጋር አመሳሰለው፡፡ ያመሳሰለው ደግሞ አጣመረው/ ጥንድ አደረገው፣ ጥንድ ያደረገው ደግሞ ከፋፈለው፡፡ የከፋፈለው ደግሞ አላወቀውም፡፡»* (ነህጁል በላጋህ፣ ኹጥባ ቁጥር 1)

## 8. የአላህ ፍትሃዊነትን በተመለከተ ያለን እምነት

ከአላህ አዎንታዊ ባህሪያት አንዱ እሱ አላህ ከማንኛውም ኢ-ፍትሃዊነት የራቀ ፍጹም ፍትሃዊ (ዓዲል ገይር ዛሊም) መሆኑን እናምናለን፡፡ ፍጥረታቱን በፍትህ እንጂ አያስተናብርም፣ ያለ አግባብና በጭካኔ አይገዛቸውም፡፡ ታዛዥ አገልጋዮችን ሽልማት ያጎናጽፋል፣ ሐጢአተኞችን በሥራቸው ይቀጣል፡፡ አገልጋዮቹ ከአቅማቸው በላይ የሆነ ነገር እንዲያደርጉ አያስገድድም፡፡ ካጠፉት ጥፋታቸው በላይ በሆነ ቅጣትም አይቀጣቸውም፡፡

መልካም ነገርን ከማድረግ እንደማይቆጠብና እኩይ የሆነ ተግባር እንደማይሰራ እናምናለን፡፡ መልካም ነገር ግን

የማድረግም ሆነ ከመጥፎ ተግባር የመታቀብ ችሎታው በእጁ ነውና፡፡ የመልካም ነገርን መልካምነትም ሆነ የእኩይ ተግባራትን እርኩስነት ስለሚያውቅ መልካምን ከመስራት የሚከለክለውና መጥፎ ለመሥራት የሚያስገድደው ነገር የለም፡፡ እንዲሁም መልካም መስራቱ ሊጎዳው ስለማይችል መልካም ከመስራት የሚታቀብበት ምክንያት አይኖርም፡፡ በተጨማሪም መጥፎ የመስራት ግዴታ ሊኖርባት ስለማይችል መጥፎ በመስራት አይገደድም፡፡ ነገር ግን አላህ ጥበበኛ በመሆኑ ሥራዎቹ የጥበቡ መገለጫ መሆን አለባቸው፣ እጅግ ባማረ መልኩም መፈጸም አለባቸው፡፡

እስቲ ደግሞ አላህ በፍጡራኑ ላይ የጭካኔ እርምጃ በመውሰድ እኩይ ተግባር ይፈጸማል ብለን እናስብ፡፡ ይህ የሚሆን ከሆነ ደግሞ ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ምክንያት መሆን አለበት፡፡

1. ድርጊቱን አያውቅም፣ እኩይ ተግባር መሆኑንም አያውቅም ማለት ነው፣

2. የሚያደርገውን ያውቃል ነገር ግን ተገዶ ነው የሚያደርገው፣ ከማድረግ መታቀብ አይችልም ማለት ነው፡፡
3. መጥፎ ተግባር መሆኑን የሚያውቅ ቢሆንም ተግባሩን መፈጸሙ አስፈላጊ ሆኖ ነገር ግን ሳይገደድ ይፈጸማል ማለት ነው፡፡
4. ነገሩን ሳያውቅ ቀርቶ ሳይሆንም ሆነ ሳይገደድ እንዲሁ ስላሰኘው ብቻ፣ ማድረጉ አስፈላጊ ሆኖ ሳይሆን ያለ ምንም ምክንያት ያሻውን ያደርጋል ማለት ነው፡፡

እነዚህ አማራጮች እያንዳንዳቸው ጉድለት ስላላቸው ለአላህ በፍጹም የማይገቡና የማይቻል ነገር ነው፡፡ እሱ አላህ ሁለገብ ፍጹምነት የተላበሰ ጌታ ነው፡፡ ስለዚህ ከጭቆና ተግባርና መጥፎ ከመስራት የጠራና የላቀ ነው፡፡

ነገር ግን አላህ መጥፎ ይሰራል ብለው የሚናገሩ ሙስሊሞች አሉ፡፡ ታዛገሮችንንና መልካም ሰሪዎችን እንደሚቀጣና ኢ-አማኞችንንና መጥፎ ሠሪዎችን ጀነት ያስገባል በማለት ሲናገሩ ይደመጣሉ፡፡ በተመሳሳይ መልኩ አላህ ባሪያዎቹ መስራት የማይችሉት ነገር (ከአቅማቸውና ችሎታቸው በላይ የሆነን ነገር) እንዲሰሩ

የሚያስገድዳቸው እንደሆነና ይህንኑ ባለመሥራታቸው ለቅጣት እንደሚዳርጋቸውም ያምናሉ፡፡ በአጭሩ አላህ ጨቋኝ መሆን እንደሚችል አድርገው ይናገራሉ፡፡ አላህ ሥህተት እንደሚሰራ፣ አገልጋዮቹን እንደሚያታልልና ነገሮችን ያለ ዓላማ፣ ፍላጎትና ጥቅም በዘፈቀ እንደሚያደርግ ይናገራሉ፡፡ ለምክንያታቸውም የሚከተለውንና የመሳሰሉ የቁርአን አንቀፆችን ይጠቅሳሉ፡

لَا يُسْأَلُ عَمَّا يَفْعَلُ وَهُمْ يُسْأَلُونَ

«***እሱ በሚሰራው አይጠየቅም፣ እነሱ ግን ይጠየቃሉ፡፡***» (21፡23)

አላህን በተመለከተ እንዲህ ዓይነቱ አስተሳሰብ ኃይማኖትን ማንቋሸሽ እንደሆነ መታወቅ አለበት፡፡ አላህ በቁርአኑ እንዲህ ይላልና፡-

وَمَا اللَّهُ يُرِيدُ ظُلْمًا لِلْعِبَادِ

«***አላህ ለባሮቹ በደልን አይሻም፡፡***» (40፡31)

እንዲሁም፡-

وَاللَّهُ لَا يُحِبُّ الْفَسَادَ

«***አላህ ለባሮቹ በደልን አይወድም፡፡***» (2፡205)

እንዲሁም፡-

وَمَا خَلَقْنَا السَّمَاءَ وَالْأَرْضَ وَمَا بَيْنَهُمَا لَاعِبِينَ

«*ሰማያትና ምድርን እንዲሁም በመካከላቸው ያሉትን ነገሮች በሙሉ ለከንቱ አልፈጠርናቸውም፡፡*» (21፡16)

እንዲሁም፡-

وَمَا خَلَقْتُ الْجِنَّ وَالْإِنْسَ إِلَّا لِيَعْبُدُونِ

«***ጂኒዎችንም (ጋኔን) ሆነ የሰው ልጅን እንዲገዙኝ እንጂ ለሌላ አልፈጠርኳቸውም፡፡***» (51፡56)

በሌሎች በርካታ የቁርአን አንቀጾችም ተመሳሳይ ሐሳቦችን ጠቅሶልናል፡፡

رَبَّنَا مَا خَلَقْتَ هَٰذَا بَاطِلًا سُبْحَانَكَ فَقِنَا عَذَابَ النَّارِ

«...***ጌታችን ሆይ! ይህን በከንቱ አልፈጠርከውም፤ ጥራት ይገባህ፤ ከእሳትም ቅጣት ጠብቀን...*** » (3፡191)

## 9. የአላህን ትዕዛዛት በተመለከተ ያለን እምነት

አላህ ያለምክንያት ባሮችን እንደማያዝና ባሮቹ ማድረግ በማይችሉት ነገርም እንደማያዝ እናምናለን፡፡ ባሮቹ መገንዘብና መረዳት የማይችሉትን ነገርም እንዲያደርጉ አያዝም፡፡ ምክንያቱም አንድን ሰው በማይችለው ነገር ማዘዝም ሆነ ቀድሞ ማስጠንቀቂያ ባልተሰጠው ጉዳይ መቅጣት ኢ-ፍትሃዊነትን መሠረት ያደረገ ስለሆነ ነው፡፡ ነገር ግን ሳያውቅ ቀርቶ የአላህን ትዕዛዛት ተቀብሎ ኃላፊነቱን ባለመወጣቱ ጥፋተኛ በመሆኑ ይቀጣል፡፡ ምክንያቱም በሁሉም የሰው ልጅ ላይ አስፈላጊ የሆኑ የኃይማኖት መመሪያዎችን መማርና ማወቅ ግዴታ ስለሆነ ነው፡፡

አላህ ለአገልጋዮቹ ትዕዛዛትን እንዳስተላለፈ፣ በፍላጎታቸውና ማወቅ የሚቻላቸውን አጠቃላይ ህግጋት እንደሰጣቸውና ወደ ዘለዓለማዊ የደስታና የብልጽግና ጎዳናዎች እንደሚመራቸው፣ እንዲሁም ፍላጎታቸውን የሚጻረሩና ጉዳት የሚያስከትሉባቸውን ነገሮች እንዲፈሩና እንዲጠነቀቁ እንደሚያደርጋቸው እናምናለን፡፡

ይህ አብዛኛውን የሚጠቅማቸውንና የሚጎዳቸውን ነገር ለይተው ላላወቁ ባሮቹ አላህ የዋለላቸው የፀጋውና የምህረቱ (ሉጥፍ ወ ረህመህ) ምሳሌ ነው፡፡

አላህ በዛቱ ርህሩህና መሐሪ ነው፡፡ ምህረቱና ፀጋው የሁለገብ ፍጹምነት መገለጫ ሲሆን ከዛቱ ጋር አንድ ነው፡፡ እነዚህ ባህሪያቱ ከዛቱ ተነጥለው ሊታዩ አይችሉም፡፡ የአመጸኞችና የአፈንጋጮች አመጽና ማፈንገጥ ፀጋውንና ምህረቱን ከፍጡራኑ ላይ እንዲያነሳ አያደርጉትም፡፡

## 10. ቀዳእና ቀደርን (ቅድመ-ውሳኔና መለኮታዊ ፍርድን) በተመለከተ ያለን እምነት

የሙጀብቢራህ አስተምሮ አቀንቃኞች አላህ ለፍጡራኑ ተግባራት በሙሉ ኃላፊነቱ የሱ (የአላህ) ነው በማለት ያምናሉ፡፡ ይኸውም ፍጡራኑ መጥፎ እንዲሰሩ ካስገደዳቸው በኃላ በሥራቸው እንደሚቀጣቸውና መልካም እንዲሰሩ ካስገደዳቸው በኃላ በስራቸው እንደሚሸልማቸው ይናገራሉ፡፡ የሰዎች ድርጊት/ተግባራት በመሰረቱ የአላህ ድርጊት/ተግባራት እንደሆኑና የሰው

ልጆች የአላህ ሥራዎች አድራሻ በመሆናቸው፣ በተዘዋዋሪ ወይም በምሳሌያዊ አነጋገር ዘይቤ በሰው ልጅ የሚገለጽ ሆኖ እንጂ ድርጊቶች በሙሉ የአላህ ውጤት ናቸው ብለው ያምናሉ፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት ሙጀብቢራዎች በነገሮች መካከል ያለውን የተፈጥሮ መንስኤ (አስ-ሰበቢያህ አት-ጠቢዒያህ) በመካዳቸውና አላህ እውነተኛው ብቸኛ መንስኤ (አስ-ሰበብ አል-ሐቂቂይ) አድርገው በማሰባቸውና ከአላህ ውጭ ሌሎች መንስኤዎች እንደሌሉ በማመናቸው ነው፡፡

በነገሮች መካከል የሚገኙትን የተፈጥሮ መንስኤዎች ያመከኑበት ምክንያት ደግሞ አላህ ያለ ምንም አጋርና ሸሪካ ነገሮችን ሁሉ ያስገኘ ፈጣሪ መሆኑን ከማመን ግዴታ የሚመነጭ ብለው ስለሚያስቡ ነው፡፡

ነገር ግን እንዲህ ዓይነቱን አስተሳሰብ የሚያራምድ ሰው በእውነቱ አላህን በኢ-ፍትሓዊነት (ዙልም) የፈረጀ ነው፡፡ ሌላው ሙፈዊዳህ የሚባለው ቡድን ደግሞ አላህ ለፍጥረታቱ በተግባሮቻቸው ላይ ሙሉ ኃይልና ስልጣን እንደሰጣቸውና የአላህ ኃይልና ፍርድ ምንም

የሚጫወተው ሚና እንደሌለ አድርገው ያምናሉ፡፡ ይህ ቡድን ለዚህ አስተሳሰባቸው የሚያስቀምጡት ምክንያት ደግሞ የሰው ልጆችን ተግባራት ወደ አላህ ማስጠጋት አላህን በእንከን መግለፅን ያስከትላል ብለው በማሰብ ነገሮች ሁሉ የተለየ/የተወሰነ መንስኤዎች (አስባብ አል-ኻስሰህ) እንዳላቸውና ይህ ደግሞ ወደ መንስኤዎቹ መንስኤ እንደሚመለስ በማተት የመጀመሪያውና መነሻ መንስዔ አላህ ነው ብለው ያምኑ ነበር፡፡ ነገር ግን ይህን አስተሳሰብ የሚያራምዱ ሰዎች አላህን ከኃይሉ በመነጠል በፈጣሪነቱ ውስጥ ሸሪኮችን ያደረጉለት ናቸው፡፡

እንግዲህ ይህንን ጉዳይ አስመልክቶ የኛ እምነት የኢማሞቻችን አስተምህሮ መሠረት ያደረገ ነው፡፡ እውነታው ያለው ቀደም ሲል በተጠቀሱት ሁለቱ ጽንፎች መሐከል ነው፡፡ እውነታው ያለው እነዚህ የሥነ-መለኮት ጠበብት ተከራከሪዎች ሊረዱት የማይችሉት በሁለቱ ንድፈ ሐሳቦች አማካይ ላይ ነው፡፡ ዕውቀትና ፍልስፍና ከብዙ ምዕተ-ዓመታት በኋላ እንጂ ይህን ጉዳይ ማብራራት አልቻሉም ነበር፡፡ ስለዚህ ለኢማሞቻችን ጥበብ እንግዳ የሆኑ ሰዎች እምነታችን የተገኘው በቅርብ

ጊዜ የምዕራባውያን ፈላስፋዎች ምርምርና ግኝት ነው ብለው ቢያስቡ የሚያስደንቅ አይደለም፡፡ ነገር ግን እውነታው ኢማሞቻችን በዚህ ጉዳይ ላይ በአስር ምዕተ ዓመታት ይቀድሟቸው ነበር፡፡

ኢማም ሳዲቅ (ዐ.ሰ) በሁለቱ ጽንፎች መካከል ያለውን አማካይ ቦታ ሺገለጹ እንደሚከተለው ያስቀምጡታል፡-
«*ማስገደድ (ጀብር) የለም፣ (ከአላህ ለሰው የተሰጠ) አጠቃላይና ፍጹም የሆነ ኃይልም (ተፍዊድ) የለም፡፡ ትክክለኛው ቦታ በነዚህ ሁለቱ ጽንፎች መካከል ነው ያለው፡፡*»

ምንኛ ድንቅ ጥበብ በዚህ አባባል ውስጥ እናገኛለን! ትርጉምስ ምንኛ ግሩም ነው! ተግባሮቻችን በአንድ በኩል የራሳችን ተግባራት መሆናቸውንና የተፈጥሮ መንስኤያቸው እንደመሆናችን በቁጥጥራችን ሥር ያሉ በነፃ ፈቃዳችን የሚከሰቱ መሆናቸውንና በሌላው በኩል ደግሞ ህይወት የሚሰጥና ነገሮችን የሚያስገኝ እሱ አላህ በመሆኑ በሱ ፍርድና ኃይል ስር እንደሆኑ ይጠቁማል፡፡ በምናደርጋቸው ነገሮች ላይ ኃይል/ችሎታና ምርጫ

ስላለን በመጥፎ ተግባራችን ለቅጣት በመዳረግ በሚበድለን መልኩ ምንም እንድናደርግ አያስገድደንም፡፡ ነገር ግን የተግባሮቻችን ፈጣሪ እንሆን ዘንድ ከኃይሉ በላይ የሆነ የመፍጠር ኃይልም አልሰጠንም፡፡ ፈጣሪነት፣ ፍርድና ትዕዛዝ የሱ ነውና፡፡ እሱ አላህ በሁሉም ነገር ኃይልና ችሎታ አለው፣ በሰው ልጆች ላይ ሙሉና ፍጹም የሆነ ስልጣንና ኃይል አለው፡፡

ያም ሆነ ይህ እንደኛ እምነት ቀዳ እና ቀደር ከአላህ ሚስጢሮች አንዱ በመሆናቸው፣ ወደ ሁለቱ ጽንፍ ሐሳቦች ሳይገባ መረዳት በሚገባቸው ሁኔታ የተረዳ ሰው ትክክለኛ ሰው ነው፡፡ አለበለዚያ አንድ ሰው በትክክል ለመረዳት እራሱን ማስገደድ መሞከሩ አስፈላጊ አይደለም፡፡ ይህ ካልሆነ ግን ፈር ሊስትና እምነቱም ሊበከል ይችላል፡፡ ይህ ጉዳይ ጥቂት ሰዎች ብቻ ሊረዱት የሚችሉት አስቸጋሪ የፍልስፍና ርዕስ ነው፡፡

በዚህ ምክንያት በርካታ የሥነ-መለኮት ጠበብት (ሙተከልሊሙን) ለስህተት ተደርገዋል፡፡ በዚህ ጉዳይ

ላይ ትክክለኛ ግንዛቤ ላይ የመድረስ ግዴታና ኃላፊነት ተራ ለሆነ ሰው እጅግ የከበደ ኃላፊነት ነው፡፡

የኢማሞቻችን (ዐ.ሰ) አባባል በመከተል አጠቃላይ በሆነ መልኩ መረዳት መቻል በቂ ነው፡፡ ይኸውም እውነታው በሁለቱ ጽንፍ ሐሳቦች መካከል መሆኑን፣ ማለትም መገደድም/ግዴታም ሆነ ገደብ የለሽ ነፃ ፈቃድ ወይም ምርጫ የሌለ መሆኑን ማወቁ በቂ ነው፡፡ ዞሮ ዞሮ ይህ ጉዳይ በምርምርና ጥልቅ ሐሳብ ላይ በመመስረት እምነት ማግኘት መሞከር አላስፈላጊ የሆነበት ርዕስ ነው፡፡

## 11. በደዕ («የሐሳብ ለውጥ») አስመልክቶ ያለን እምነት

የሰው ልጅን በተመለከተ የበደዕ ትርጉም እንዲህ ነው፡-

አንድ ሰው አንድ ነገር ማድረግ ካሰበ በኋላ ሐሳቡን የሚያስለውጥ ቀደም ሲል ያላሰበው ሐሳብ ሲመጣለት ቀድሞ ያሰበውን ተግባር ላለማድረግ መወሰን ማለት ነው፡፡ ይህም ማለት አንድ ሰው አንድ ነገር መስራት ካሰበ በኋላ ስለዛ ተግባር የነበረውን ዕውቀትና ግንዛቤ የሚያስለውጥ ነገር በመከሰቱ ቀደም ሲል ለማድረግ

ያሰበውን ነገር መተው ማለት ነው፡፡ ይህ የሰው ልጅ የሚጠቅመውን ነገር ካለማወቅ የተነሳ የሚከሰትና ያሰበውን በመስራቱና መሥራት እንዳለበት ፀፀት ሊገጥመው ይችላልና ነው፡፡

በደዕ በእንዲህ ዓይነቱ እይታ ወይም አተረጓጎም ለአላህ የማይታሰብና የማይሆን ነው፡፡ ምክንያቱም አለማወቅና ጎደሎነት/እንከን መንስኤው ሲሆኑ አላህ ደግሞ ከዚህ የጠራና የላቀ ነው፡፡ የኢማሚያህ እምነት ተከታዮች በዚህ አያምኑም፡፡ ኢማም ሳዲቅ (ዐ.ሰ) እንዲህ ብለዋል፡-

«*አንድን ጉዳይ በተመለከተ አላህን እንዲፀፀት በሚያደርግ መልኩ በደዕ ይገጥመዋል ብለው የሚያስቡ ሰዎች በኛ እምነት በአላህ ያላመኑ ከሃዲዎች (ካፊሮች) ናቸው፡፡*»

በተጨማሪም እንዲህ ብለዋል፡-

«*አንድን ጉዳይ በተመለከተ አላህ ቀድሞ ያላስተዋለው ሐሳብ የሚያስለውጥ ነገር (በደዕ) ይገጥመዋል ብለው ከሚያስቡ ሰዎች ርቄ እኖራለሁ፡፡*»

አንዳንድ ሰዎች እላይ በተጠቀሰው መልኩ/ትርጉም በበደዕ እንደምናምን አድርገው እንዲያስቡ ያደረጓቸው ከኢማሞቻችን የተነገሩ አንዳንድ ሐዲሶች አሉ፡፡ ለምሳሌ ኢማም ሳዲቅ (ዐ.ሰ) እንዲህ ብለዋል፡-

«*ልጄ ኢስማኢልን በተመለከተ የነበረው በደዕ ዓይነት ለአላህ አልነበረም፡፡*»

በእንዲህ ዓይነቶቹ ሐዲሶች የተነሳ አንዳንድ የኢስላም ቡድኖች የኢማሚያ መዝሐብ ተከታዮች በበደዕ ያምናሉ እያሉ በመወንጀል ጀመዓችንንና የነቢዩ ቤተ-ዘሮችን (አህለል ቤይት) ጎዳና ለማጥቃት ሲሞክሩና እራሳቸው በፈጠሩት ይህ እምነት ሺዓዎችን ሲያንቋሽሹ ይስተዋላሉ፡፡

የዚህ ጥያቄ ትክክለኛ ጎኑ አላህ በቁርአኑ ያወረደው አያህ መሠረት ነው፡-

يَمْحُو اللَّهُ مَا يَشَاءُ وَيُثْبِتُ وَعِنْدَهُ أُمُّ الْكِتَابِ

«***አላህ የሚሻውን ያብሳል፤ ያጸድቃልም፡፡ የመጽሐፉ መሠረትም እርሱ ዘንድ ነው፡፡***» (13፡39)

የዚህ ትርጉም ደግሞ እንዲህ ነው፡፡ ይኸውም አላህ በነቢዩ ምላስ ላይ ወይም በነቢዩ ተወካይ (ዋሊ) ላይ ወይም በሌላ መንገድ አንድ ነገር እንደ ነባራዊ ሁኔታው ለተወሰነ ጥቅም እንዲገለጥ ካደረገ በኋላ ቀደም ሲል የነበረውም መገለጥ ያስቀርና ጉዳዩን መጀመሪያውኑ የሚያውቅ ቢሆንም ቀደም ሲል ከነበረው በሌላ አኳኋን እንዲሆን ያደርጋል፡፡

የዚህን ምሳሌ የምናየው በኢስማኢል ጉዳይ ሲሆን አባቱ ኢብራሂም ልጁን በህልሙ እያረደ ያየበት ሁኔታ ነው፡፡ የኢማም ሳዲቅ (ዐ.ሰ) አባባል ትርጉም ደግሞ አላህ ኢስማኢልን (የኢማም ሳዲቅ ልጅ) በተመለከተ የአባቱን ነፍስ ከመውሰዱ በፊት የልጁን ነፍስ በመውሰድ የገለጠውን ጉዳይ ዓይነት በሌላ በምንም ጉዳይ ላይ አልገለጠም ለማለት ነው፡፡ በዚህ መልኩ ኢስማኢል ታላቅ ልጅ በመሆኑ ነባራዊው ሁኔታ ኢማም እንደሆነ ቢያስመስልም በእውነቱ ግን ኢማም እንዳልነበረ ሕዝቡ እንዲረዳ ለማድረግ የተናገሩት አባባል ነበር፡፡

ሌላው ተመሳሳይ የበደዕ ትርጉም ደግሞ ቀደምት ህግጋትን (ሽራኢዕ - የሽሪዓ ብዙ ቁጥር) በቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) በመጣው ሽሪዓ መሻርና እንዲያውም ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ያመጧቸውን አንዳንድ ትዕዛዛትን መሻርም ይመለከታል፡፡

## 12. ህግጋትን ወይም መመሪያዎችን በተመለከተ ያለን እምነት

አላህ የባሮቹን ፍላጎት ያገናዘበ መመሪያዎች እንደላከ እናምናለን፡፡ ይኸውም ለሰው ልጆች በከፍተኛ ደረጃ ጠቃሚ የሆኑ ነገሮች በኛ ላይ ግዴታ (ዋጂብ) አደረገ፣ ለኛ ጎጂ የሁኑ ነገሮች ደግሞ የተከለከለ (ሐራም) አደረግልን፣ ጥቅም የሚያስገኝልን ነገር ሆኖ ጥቅሙ ግን ብዙ የማይባልለት የሆነን ነገር ደግሞ የሚመከር (ሙስተሐብ) አድርጎልን እንድንሰራው አበረታታን፡፡ ይህ ደግሞ ከፍትሃዊነቱና ምህረቱ የመነጨ ነው፡፡

በግልጽ ለመረዳት አቅማችን ባይፈቅድም አላህ መመሪያዎችን መስጠት ያለበት ሁሉንም ሁኔታዎችና ክስተቶችን በሚያቅፍ መልኩ መሆን እንዳለበት ግልጽ

ነው፡፡ ይኸውም ማንኛውም ነገር ከትዕዛዛቱ ድንበር ውጭ ሊሆን አይችልም ማለት ነው፡፡

በተጨማሪም ከፊሉ መጥፎ በሆነ ተግባር ማዘዝም ሆነ ከፊሉ በጎ ከሆነ ነገር መከልከል ለአላህ የማይገባ ነገር ነው እንላለን፡፡ አንዳንድ ሙስሊሞች ግን እኩይ ተግባር ማለት አላህ የከለከለው ነገር ነው፣ በጎ ነገር ማለት ደግሞ አላህ ያዘዘው ነገር ነው በማለት ተግባራቱ በራሳቸው እኩይነትም ሆነ በጎነት የላቸውም እያሉ ይናገራሉ፡፡

ነገር ግን ይህ ከምክንያታዊ አስተሳሰብ ጋር የሚጣጣም አይደለም፡፡ እነዚሁ ሰዎች ደግሞ አላህ መጥፎ ተግባራትንም ይፈጽማል፣ እንዲሁም መጥፎ ነገር ባለባቸው ነገሮችም ያዛል፣ በጎ ከሆኑ ነገሮችም ሊከለከል ይችላል ብለው ያምናሉ፡፡ ቀደም ሲል እንተገለጸው እንዲህ ዓይነቱ አስተሳሰብ የተሳሰተና ከእውነት የራቀ ነው፡፡ ምክንያቱም አላህ አላዋቂ እንደሆነና አንዳንድ ነገሮችን ማድረግ እንደማይችል ተደርጎ መታሰብን ያስከትላልና፡፡ አላህ ከምንለውና ከምናስበው ነገር የጠራና የላቀ ሁሉን ቻይ ጌታ ነው!

በአጭሩ ትክክለኛ እምነት መሆን ያለበት አላህ እኛን በማዘዙ ውስጥ ምንም ፍላጎትም ሆነ ጥቅም ኖሮት ሳይሆን ፍላጎትም ሆነ ጥቅሙ በሙሉ ለራሳችን እንደሆነ ማወቅ ይኖርብናል፡፡ አላህ ምንም ጥቅምና ዓላማ በሌላው ነገር ያዛል ማለት የማይሆን ነገር ነው፡፡ ጉዳት ከሌለው ነገር ይከለክላል ብሎ ማሰብም የማይመስል ነው፡፡ ያለ ዓላማ የሆነ የአላህ ህግጋት የለም፣ አላህ ከባሮቹ የሚፈልገው ነገርም የለም፡፡

# ክፍል ሁለት

# ኑቡወህ (ነቢይነት)

## 13. ነቢይነትን አስመልክቶ ያለን እምነት

ነቢይነት መለኮታዊ ተግባርና ከአላህ የሆነ ተልዕኮ መሆኑን እናምናለን፡፡ ከደጋግ ባሮቹ መካከል ለመረጠው ሰው የሚሰጥ ሹመት ነው፡፡ ከሰው ልጆች የተከበረውን ቦታ ለተቀናጠጡና ለተከበሩ ሰዎች የሚሰጥ ኃላፊነት ነው፡፡ የሰው ልጆችን ወደ ቅን መንገድና በዚህች ምድርም ሆነ በወዲያኛው ዓለም ወደሚጠቅማቸው ጎዳና ይመሩ ዘንድ ከአላህ ወደ ሰው ልጆች የሚላኩ ናቸው፡፡ የሰው ልጆችን ከመጥፎ ስብዕና እንዲያጠሩ፣ ከእኩይ ተግባራትና ጎጂ ልማዶች እንዲጠብቁ፣ ሰዎችን ዕውቀትና ጥበብ እንዲያስተምሩ፣ ሰዎች ለተፈጠሩለት የፍጹምነት ደረጃና በሁለቱም ዓለማት የተከበረ ቦታ እንዲጎናጸፉ ለመጠቆም፣ የደስታና የበጎ ተግባራት ጎዳናዎችን እንዲያመለክቱ ከአላህ የተላኩ ናቸው፡፡

የአላህ ፀጋና ርህራሄ (ሉጥፍ) መልክዕተኞችን ወደ ሰዎች በመላክ ህዝቡን ቅኑን መንገድ እንዲመሩ፣ የተሃድሶ ሥራ እንዲሰሩና በአላህና በኹለፋዎቹ መካከል አምባሳደሮች (ሱፈራእ) እንዲሆኑ ማድረግን ይጠይቃል፡፡ አላህ ለሰው ልጆች ነብይን የመጠቆም፣ የመምረጥ ወይም የመሾም መብት ስላልሰጣቸው፣ አንድን ሰው ነቢይ አድርጎ የሚመርጥና የሚሾም አላህ ብቻ መሆኑን እናምናለን፡፡ ምክንያቱም፡-

اللَّهُ أَعْلَمُ حَيْثُ يَجْعَلُ رِسَالَتَهُ

«***አላህ መልዕክቱን የት ማድረግ (ለማን መስጠት) እንዳለበት እጅጉን ያውቃልና፡፡***» (6፡124)

ከዚህ መረዳት እንደምንችለው አላህ መልካሙን ዜና አብሳሪዎችና ከሚመጡ ክስተቶች አስጠንቃቂ አድርጎ የሚልካቸው መሪዎችን በተመለከተ የሰው ልጆች የመከራከር መብት እንደሌላቸው ነው፡፡

እንዲሁም መሪዎቹ የሚያመጡዋቸውን ኃይማኖታዊ ህግጋት ከመቀበል ውጭ አማራጭ የሌላቸው መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

## 14. ነቢይነት (ኑቡወህ) ከመለኮታዊ ፀጋ (ሉጥፍ) ነው፡፡

የሰው ልጆች ተለዋዋጭ ፍጡር ነው፣ ማንነቱን (ህልውናውን)፣ ተፈጥሮውን፣ ነፍሱንና አዕምሮውን ያካተተ የውስብስብ ቅንብር ውጤት ነው፡፡ እያንዳንዱ ግለሰበዊ ስብዕና መጥፎና በጎ መንስዔዎችን ያካተተ ተመሳሳይ ውስብስብ ተፈጥሮ አለው፡፡ በሌላ መልኩ ደግሞ የሰው ልጅ የተፈጠረው እንደ ራስ ወዳድነት፣ ፍላጎት፣ ኩራት፣ የመሳሰሉ ውስጣዊ ስሜቶች ጋር ነው፣ ለውስጥ ፍላጎቱ ጥሪ ምላሽ የሚሰጥ፣ በሌሎች ላይ የበላይነቱን ለማሳየት የተፈጥሮ አቋም ያለው፣ ነገሮችን በንብረትነት የመያዝ ሞኞት ያለው፣ የሌሎች ንብረትን ለራስ ለማድረግ የሚኳትን፣ ለዚህች ዓለም ዕቃና ጌጣጌጥ ሳይታክት የሚሮጥ ፍጡር ነው፡፡

**አላህ እንዲህ ይላል፡-**

إِنَّ الْإِنْسَانَ لَفِي خُسْرٍ

«***እነሆ የሰው ልጅ በኪሳራ ላይ ነው፡፡***» (103፡2)

**በተጨማሪም፡-**

كَلَّا إِنَّ الْإِنْسَانَ لَيَطْغَىٰ. أَنْ رَآهُ اسْتَغْنَىٰ

«***በእውነቱ ሰው ወሰንን ያልፋል፡፡ ራሱን የተብቃቃ (ባለ ሀብት) ሆኖ ለማየቱ፡፡***» (96፡6-7)

**እንዲሁም፡-**

إِنَّ النَّفْسَ لَأَمَّارَةٌ بِالسُّوءِ

«***...ነፍስ ሁሉ በእርግጥ በመጥፎ ነገር አዛዥ ናት፡፡...***» (12፡53)

**ከሰው ልጅ ጋር አብሮ ስለተፈጠሩ ስሜቱና ፍላጎቱ የሚያወሩና የሚያመለክቱ ሌሎች በርካታ የቁርአን አንቀጾች አሉ፡፡**

በአንፃሩ ደግሞ አላህ ለሰው ልጅ ማሰቢያ አዕምሮ ሰጥቶታል፡፡ በዚህ አዕምሮው (ዐቅል) የሰው ልጅ ወደሚጠቅመውና በጎ ነገር እንዲመራ ያደርጋል፡፡ ከእኩይ ተግባርና ሌሎችን ከመጨቆን የሚታቀብበት ህሊናም ተሰጥቶታል፡፡ ሀጢአት ሲሰራ የሚቆረቆርበትና የሚቆጭበት ህሊናም ተሰጥቶታል፡

በሰው ልጅ ምኞት/ፍላጎትና በአዕምሮው መካከል የማያቋርጥ ትግል አለ፡፡ አዕምሮአቸው ፍላጎታቸውን ያሸነፈ ሰዎች ከሰው ልጆች መካከል ከፍተኛውንና የተከበረውን ቦታ የሚጎናጸፉና ፍጹም የሆነ መንፈሳዊ ደረጃ የሚደርሱ ሲሆኑ ፍላጎታቸው አዕምሮአቸውን እንዲቆጣጠር የፈቀዱ ሰዎች ግን በታላቅ ኪሳራ ውስጥ ያሉና ዝቅተኛውን የሰው ልጅ ደረጃ በመያዝ ከአውሬዎች ተፈጥሮ ጋር የሚመሳሰሉበት ሁኔታ ውስጥ ይሆናሉ፡፡

ሥጋዊ ምኞታቸውና ቁሳዊ ፍላጎታቸው ከአእምሮአቸው በላይ ይበረታል፡፡ ለዚህም ነው ብዙ ሰዎች ፍላጎታቸውን እና ምኞታቸውን ብቻ በመታዘዝ ከቀናው መንገድ አፈንግጠው የሚገኙት፡፡ እነዚህ ሰዎች ከአዕምሮአቸው

ጥሪ ይልቅ ለሥጋዊ ፍላጎታቸው ጥሪ ምላሽ የሰጡ ናቸው፡፡ ቁርአን ይህንን ሁኔታ ሊገልጽ፡-

وَمَا أَكْثَرُ النَّاسِ وَلَوْ حَرَصْتَ بِمُؤْمِنِينَ

«***አብዛኛዎቹም ሰዎች (ለማመናቸው) ብትጓጓም የሚያምኑ አይደሉም፡፡***» (12፡103)

በተጨማሪም የሰው ልጅ በአካባቢው የሚገኙትን እውነታዎችና ሚስጥሮች ለማወቅ ያለው ጉጉት አነስተኛ በመሆኑ ግንዛቤው አናሳ ነው፡፡ የሰው ልጅ ስለ ራሱ እንኳን የማያውቅ በሆነበት ሁኔታ የሚጠቅመውንና የሚጎዳውን ለይቶ ማወቅ እንዴት ይቻለዋል? ለብልጽግና የሚያበቃውን ጎዳናና ለጥፋት የሚዳርገውን መንገድ እንዴት ይለያል?

ለራሱ የሚጠቅመውንም ሆነ በአጠቃላይ ለመላው የሰው ልጅ የሚፈይድ እያንዳንዱ ነገር እንዴት ማወቅ ይችላል? በህይወቱ ውስጥ አዲስ ግኝቶች በሚያጋጥሙበት ጊዜ አላዋቂነቱ ይታየውና ምንም እንደማያውቅ እየተረዳ ይመጣል፡፡ ይህ የሆነበት

ምክንያት የሰው ልጅ ወደ ብልጽግና የሚያመራውን ቀጥተኛና እውነተኛ ጎዳና የሚጠቁመው ሰው ሁሌም ስለሚያስፈልገው ነው፡፡ አደገኛና ሁሌም የሚከታተለውን ጠላቱን ያሸንፍ ዘንድ ለአዕምሮው ድጋፍ የሚሆንለትና ስሜቱን ለመዋጋትና ለመቆጣጠር እንዲዘጋጅ የሚረዳው ሰው ይፈልጋል፡፡

የሰው ልጅ በስሜቱ ተታሎ፣ እኩይ ተግባራቱ እንደመልካም ሥራ፣ በጎ ሥራው ደግሞ እንደ መጥፎ ሥራ ታይቶት፣ በዚህም ምክንያት አዕምሮው ሲምታታና ሲወናበድ፣ እንዲሁም ትክክለኛውን በጎ ሥራ ከትክክለኛው መጥፎ ተግባር መለየት ሲያቅተውና እውነተኛውን የብልጽግና ጎዳና ለማወቅ ሲቸገር፣ ወደ መልካምነትና የደስታ መንገድ የሚመራው ሰው የግድ ይፈልጋል፡፡ አላህ ከጠበቀው ሰው በስተቀር እያንዳንዳችን አወቅንም አላወቅንም በዚህ የትግል ሜዳ ውስጥ ተሰልፈናል፡፡ ለተማረና ለሰለጠነ ሰው እንኳ መልካሙንና የደስታ መንገዱን ማግኘት አልተቻለውም፡፡ መሀይምና ላልተማረ ሰው ደግሞ ምን ያህል አስቸጋሪ እንደሚሆን አስቡት፡፡

ሰዎች ሁሉ ቢተባበሩ፣ እርስ በርሳቸው ቢመካከሩና በጋራ ቢረባረቡም ለራሳቸውም ሆነ ለህብረተሰቡ የሚጠቅመውን እና የሚጎዳውን ነገር ማወቅ አልቻሉም፡፡ ስለዚህ አላህ በፀጋውም በምህረቱ ለሰው ልጆች መልዕክተኛ ይልካል፡፡ ቁርአን እንዲህ ይላል፡-

هُوَ الَّذِي بَعَثَ فِي الْأُمِّيِّينَ رَسُولًا مِنْهُمْ يَتْلُو عَلَيْهِمْ آيَاتِهِ وَيُزَكِّيهِمْ وَيُعَلِّمُهُمُ الْكِتَابَ وَالْحِكْمَةَ وَإِنْ كَانُوا مِنْ قَبْلُ لَفِي ضَلَالٍ مُبِينٍ

«*እርሱ ያ በመሃይሞቹ ውስጥ አንቀጾቹን (ቁርኣንን) በእነርሱ ላይ የሚያነብላቸው፣ (ከማጋራት) የሚያጠራቸውም፣ መጽሐፍንና ጥበብን የሚያስተምራቸውም የሆነን መልዕክተኛ (ሙሐመድን) ከእነርሱው ውስጥ የላከ ነው፡፡ እነርሱም ከእርሱ በፊት በግልጽ ስሕተት ውስጥ ነበሩ፡፡*» (62፡2)

እናም መልዕክተኛው እኩይ ተግባራትን በሚመለከት ማስጠንቀቂያ ይሰጣል፣ ለሰው ልጆች ህይወት መልካም ስለሆኑ ነገሮች ደግሞ መልካሙን ዜናና ብስራት ይሰጣል፡፡

ይህንን ፀጋ መስጠቱ ለአላህ አስፈላጊ ነው፡፡ ምክንያቱም ይህ የፍጹምነቱ መገለጫ ነውና፡፡ እንዲሁም እሱ አላህ ለባሮቹ አዛኝና ርህሩህ የሆነ ጌታ ነውና፡፡

የሰው ልጅ የአላህ ፀጋና ምህረት የሚገባው ሲሆን አላህ ፀጋና ምህረቱን ሊለግሰው ይገባል፣ ምክንያቱም በአላህነቱ ውስጥ እንከን/ጎደሎነትና ንፍገት የለምና፡፡ «ለአላህ አስፈላጊ ነው»፣ ወይም «ይገባል» ወይም «ግዴታ ነው» ስንል አላህ የሆነ ነገር እንዲያደርግ የሚያስገድደው ነገር ወይም አላህ መታዘዝ ያለበት ነገር አለ ማለት ሳይሆን፣ ፀጋና ምህረት ከአላህ የማይነጠሉ ቅዱስ ባህሪያቱ ናቸው ማለታችን ነው፡፡ ይህም ማለት ቀደም ሲል ህልውናው ወይም መገኘቱ ከማንነቱ ተለይቶ አይታይም ወይም ደግሞ «የመኖሩ ግዴታነት» ስንል ህልውናው/መገኘቱ ከርሱ ጋር አንድ ላይ ያለና ተለይቶ መታየት የማይችል

መሆኑ እንደተነገረ ሁሉ ምህረቱና ፀጋውም ከራሱ (ከዛቱ) ወይም ህልውናው ተነጥሎ የሚታይ አይደለም ለማለት ነው፡፡

## 15. ነቢያዊ ተዓምራትን በተመለከተ ያለን እምነት

አላህ አንድን ሰው ለፍጥረታቱ መሪና መልዕክተኛ አድርጎ ሲመርጥ፣ የመረጠውን ሰው ለይቶ ለሕዝቡ ማሳወቅ አለበት ብለን እናምናለን፡፡ ከወደር-የለሽ ፀጋውና ትሩፋቱ ፍጹምነት መገለጫ አላህ ለመልክተኛው ወይም ለነቢዩ ከአላህ ስለመልላኩ ማስረጃና ምስክር ይሆን ዘንድ ለህዝቡ የሚታይ የተለየ ምልክት ወይም ማስረጃ መስጠት አለበት፡፡ ይህ ደግሞ ከሰዎች ችሎታ ውጭ የሆነ የመላው ፍጥረታት ፈጣሪና ለጋስ ጌታ ኃይልና ችሎታ ብቻ የሆነ የተለየ ነገር መሆን አለበት፡፡ ይህንን ማስረጃ ለመልክተኛው በመስጠት ለሰው ልጆች ያስተዋውቀዋል ማለት ነው፡፡ ይህንን ማስረጃ ተዓምር እንለዋለን፡፡ ነቢዩ ህዝቡን ወደ ነቢይነቱ በሚጠራበት ወቅት ተዓምሩን ማሳየት መቻል አለበት፡፡ የሚያሳየው

ተዓምርም ግልጽ መሆን አለበት፡፡ ይኸውም ተዓምሩ ከሰዎች ችሎታ በላይ መሆኑን ሁሉም ሰው ማወቅ አለበት፡፡ እንዲሁም ተራው ህዝብ ብቻ ሳይሆን በጊዜው ከሚኖሩ የዕውቀት ባለቤቶችም ሆኑ ከሁሉም መስክ ጠበብቶች አቅምና ችሎታ ውጭ የሆነ ነገር መሆን አለበት፡፡ በተጨማሪም ለነቢይነቱ ማስረጃ ይሆን ዘንድ ተዓምሩን የማሳያ ጊዜና ህዝቡን ወደ ነቢይነት የመጥራት ጊዜ መገናኘት አለበት፡፡

የዕውቀት ባለቤቶች ጠበብቶች ተዓምራቱን ደግመው ማሳየት ሲያቅታቸው ነገሩ ከሰው ችሎታ በላይ መሆኑና ከመለኮታዊ ኃይል የተሰጠ መሆኑን መረዳት ይችላሉ ማለት ነው፡፡ በዚህ መልኩ ነቢዩ ከዓለማት ፈጣሪ ጋር ባለው መንፈሳዊ ግንኙነት የተነሳ ከሰው ልጆች በላይና የላቀ መሆኑን ያስረግጣሉ፡፡ በመሆኑም እንዲህ ዓይነቱ ነቢይ ተዓምራቱን ለህዝቡ አሳይቶ ወደ ነቢይነቱ ጥሪ ሲያደርግ ጥሪውን መቀበል፣ መልዕክቱን ማመንና ትዕዛዛቱን መታዘዝ በሁሉም ላይ ግዴታ ይሆናል፡፡

ስለዚህ የእያንዳንዱ ነቢይ ተዓምራት ከጊዜው አስፈላጊና ወቅታዊ ጥበባትና ሳይንሶችን ያገናዘበ መሆን አለበት፡፡ ለምሳሌ የሙሳ (ዐ.ሰ) ተዓምር የድግምተኞችን ቅጥፈት በሙሉ ለመዋጥ የበቃ በትር ነበር፡፡ ይኸውም አስማት ወይም ድግምት በጊዜው ትልቅ ቦታ የተሰጠው ጥበብ ስለነበረ ነው፡፡ የሙሳ (ዐ.ሰ.) በትር አስማተኞቹ የሰሩትን ነገር አወደመባቸው፡፡ በዚህ ጊዜ ሙሳ (ዐ.ሰ) ያደረገው ነገር ከችሎታቸውና ክህሎታቸው በላይ እንደሆነ፣ በሰው ልጅ አቅም የማይቻል ነገርና ጊዜው ጥበብና ሳይንስ ከሙሳ (ዐ.ሰ) ተዓምር ጋር ሲነፃፀር ዋጋ-ቢስ እንደሆነ ተረዱ፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የነቢዩ ዒሳ (ኢየሱስ) (ዐ.ሰ) ተዓምር ደግሞ ማየት የተሳናቸውን/ዓይን የሌላቸውንና የለምጽ በሽታ የነበረባቸው ሰዎች መፈወስና የሞቱ ሰዎችን ከሞት ማስነሳት ነበር፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት የዒሳ (ዐ.ሰ) ዘመን የህክምና ሳይንስ በህዝቡ ውስጥ የተከበረ ቦታ የያዘበት ጊዜና ሳይንቲስቶችና ሐኪሞች በህብረተሰቡ ውስጥ ከፍተኛ ክብር የነበራቸው ዘመን ነበር፡፡ ነገር ግን ሳይንሳቸውና ጥበባቸው በሙሉ ከተዓምሩ ጋር ሊስተካከሉ አልቻሉም ነበር፡፡

የነቢያችን ሙሀመድ (ሰ.ዐ.ወ) ተዓምር ደግሞ የተከበረው ቁርአን ነው፡፡ የመጠቀና የተዋበ ቋንቋን መጠቀም የጊዜው ጥበብ በነበረበት ጊዜና በንግግር ችሎታቸው የመጠቁ ሰዎች (ኦራተሮች) ከፍተኛ ክብር በተጎናጸፉበት ዘመን ታላቁ ቁርአን በረቀቀና በመጠቀ ውብ ቋንቋውና ዘይቤው የዘመኑን ተናጋሪዎችና ጸሐፍትን ፀጥ አሰኛቸው፡፡ ይህን የመሰለ ነገር ማስገኘት እንደማይችሉ በማስጠንቀቅ ቁርአን አዋረዳቸው፡፡ እጅጉንም አስደነገጣቸው፡፡ እነርሱም እጅ ለመስጠት ተገደዱ፡፡ ችሎታቸው የተፈተነበትና አቅመ-ቢስነታቸው የተረጋገጠበት ሁኔታ የነበረው የቁርአን ተመሳሳይ የሆኑ አሥር ሱራዎች (የቁርአን ምዕራፎች) እንዲያቀርቡ ሲጠየቁ ማቅረብ አለመቻላቸው ነበር፡፡ እንዲሁም አንዲት ተመሳሳይ ሱራህ እንኳ እንዲያቀርቡ ሲጠየቁ ይህንንም አልቻሉም ነበር፡፡ በቁርአን ውስጥ እንዳሉት ሱራዎች አንዱንም ማቅረብ ስለተሳናቸው ጥያቄውን መጋፈጥ እንዳልቻሉ እናውቃለን፡፡ ስለዚህም ከምላስ ይልቅ በሰይፍ መዋጋት እንዳለባቸው ወሰኑ፡፡ ቁርአን ተአምር እነደሆናና ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) እንዳመጣውና ወደ መልዕክቱ ጥሪ እንዳደረገ እንረዳለን፡፡ ስለዚህ የአላህ

መልዕክተኛ መሆኑንና እውነት ይዞ የመጣ መሆኑን እናውቃለን፡፡

## 16. የነቢያትን እንከን-የለሽነት (ዕስማህ) በተመለከተ ያለን እምነት

ሁሉም ነቢያት፣ እንዲሁም ኢማሞች (የነቢዩ ተተኪዎች) እንከን-የለሽ (መዕሱም) መሆናቸውን እናምናለን፡፡ ነገር ግን አንዳንድ ሺዓ ያልሆኑ ሙስሊሞች የኢማሞቹ ይቅርና በነቢያት እንከን-የለሽነት እንኳ አያምኑም፡፡ እንከን-የለሽነት ማለት ከማንኛውም ኃጢአት - ከትላልቅ ኃጢአቶችም ሆነ ከትናንሾቹ - መጥራት፣ ከማንኛውም ስህተትና ከመርሳት ችግሮች መጽዳት ማለት ነው፡፡

(ትላልቅ ኃጢአቶች (ከባኢር) ከኢስላም እይታ አንጻር በአንዳንድ ምሁራን መሰረት ሰባት ሲሆኑ በሌሎች መሰረት ደግሞ ቁጥር የላቸውም፡፡ የመጀመሪያዎቹ እንደየክብደታቸውና ደረጃቸው ተዘርዝረዋል ይላሉ፡፡ ከነዚህም ሽርክ (በአላህ ውጭ አምልከን ለማንም ለምንም ማጋራት) የመጀመሪያው ሲሆን አላህ ይቅር የማይለው ታላቅ ኃጢአት ነው (ቁርአን (4፡48) እና 116

ይመልከቱ)፡፡ ከዚያም ሙዕሚን (አማኝ) የሆነን ሰው ያለአግባብ መግደል፣ ከጂሃድ ተግባር መሸሽ፣ ወላጆችን መበደል፣ ሴት ልጅን ያለአግባብ በዝሙት መወንጀል፣ ሙስና፣ የየቲም (ወላጅ-አልባ ህፃናት) ንብረት ያለ አግባብ መጠቀም/መውሰድ ናቸው፡፡ የነዚህ እኩይ ተግባራት ቅጣት በቁርአን ውስጥ ተጠቅሷል፡፡)

አንድ ነቢይ ከማንኛውም መልካም ስነ-ምግባር የሚጻረር ነገር መታቀብ አስፈላጊ ነው፡፡ ይኸውም ለምሳሌ መንገድ ላይ በመብላት፣ ድምጹን ከፍ አድርጎ በመሳቅና በህዝቡ አስተሳሰብ መሰረት ተቀባይነት የሌለውን ማንኛውንም ነገር በማድረግ አግባብ በሌለው መልኩ መታየት የለበትም፡፡

አንድ ነቢይ እንከን-የለሽ (መዕሱም) መሆን አስፈላጊ የሆነበት ምክንያት ነቢዩ ሐጢአት ወይም ስህተት የሚሰራ ከሆነ፣ ወይም ደግሞ የመርሳት ወይም ችላ የማለትና ሌሎች ተመሳሳይ ባህሪያት የሚያጠቁት ከሆነ ሁለት አማራጮች አሉን፡- አንድም ኃጢአቱንና ስህተቱን መታዘዝ አለብን፣ ይህ ደግሞ በኢስላም እይታ ትክክል

ስላልሆነና ለስህተት ስለሚዳርገን በኃጢአትና ስህተት በፍጹም መታዘዝ እንደሌለብን እናውቃለን፡፡ ሌላው አማራጭ ደግሞ ኃጢአቱንና ስህተቱን ያለመቀበልና ያለመታዘዝ ነው፣ ይህም ደግሞ ትክክል አይደለም፡፡ ምክንያቱም ይህ የነቢይነትን መሠረትና ነቢይን የመታዘዝ ግዴታን የሚጻረር ነውና፡፡ በተጨማሪም አንድ ነቢይ የሚናገረውም ሆነ የሚያደርገው ነገር ትክክል ወይም ስህተት የመሆን ዕድል የሚኖረው ከሆነ እንዲህ ዓይነቱን 'ነቢይ' መታዘዝና መከተል አይፈቀድም፣ አይቻልም፡፡ የዚህ ውጤት ደግሞ የተልዕኮው ጥቅም አልባነትና አላስፈላጊነት ነው፡፡ እናም ነቢይ ማለት ቃልና ተግባሩ የሚፈለገውን የላቀ ደረጃና ዋጋ የሌለው እንደ ማንኛውም ተራ ሰው ይሆናል ማለት ነው፡፡ በመሆኑም መታዘዝም አይኖርም፣ ድርጊቱም ተዓማኒነትና ዋጋ አይኖረውም ማለት ነው፡፡

ኢማሞቹንም (ዐ.ሰ) በተመለከተ ተመሳሳይ ምክንያት ማቅረብ ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ኢማም የነቢዩ ተወካይ (ኸሊፋ) ሆኖ ሰዎችን ለመምራት በአላህ የተመረጠ መሆኑና እናምናለንና፡፡ ይህ ጉዳይ ስለ ኢማምነት

(ኢ.ማማህ) በሚያወሳው ክፍል ውስጥ በዝርዝር ይቀርባል፡፡

## 17. የነቢይን ባህሪያት አስመልክቶ ያለን እምነት

አንድ ነቢይ እንከን-የለሽ (መዕሱም) እንደሆነ እንደምናምን ሁሉ ፍጹም የሆኑ መልካም ባህሪያትን መላበስ እንዳለበትም እናምናለን፡፡ ከነዚህም ውስጥ ጀግንነት (አሽ-ሽጃዓህ)፣ ዲፕሎማሲ (አስ-ሲያሳህ)፣ ጥበብ (አት-ተድቢር)፣ ትዕግስት (አስ-ሰብር)፣ ጉብዝናና ንቃት (አል-ፈጥናህ) ፈጣን አዕምሮ (አዝ-ዘካእ) እና የመሳሰሉት ሲጠቀሱ በነዚህ ባህሪያት ማንም ሰው ሊበልጣቸው አይገባም፡፡ ይህ ካልሆነ ህዝቦችን ለመምራትና የመላውን ዓለም ጉዳዮች የማስተዳደር ብቃት ሊኖረው አይችልም፡፡ ከታወቀና መልካም ከሆነ ዘር የተገኘ፣ ቀናና ታማኝ መሆን አለበት፡፡ በነቢይነት ተልዕኮ ከመሾሙ በፊት ጀምሮ ህይወቱን በሙሉ ከእንከን የጠራና ይህ መለኮታዊ ትልቅ ቦታና ሹመት እንደሚገባው ህዝቡ እምነት እንዲኖረውና እንዲተማመኑበት እነዚህን መልካም

ባህሪያት የተላበሰና በህብረተሰቡ ውስጥ ቁንጮ ቦታ የያዘ መሆን አለበት፡፡

## 18. ነቢያትንና መጽሐፍታቸውን በተመለከተ ያለን እምነት

በአጠቃላይ ሁሉም ነቢያት ትክክለኛውን መንገድ እንደሚከተሉ፣ እንከን-የለሽና ስህተት አልባ እንደሆኑና ንጹኃን እንደሆኑ እናምለን፡፡ ነቢይነታቸውን መካድ፣ በነሱ ማሾፍ ወይም ማፌዝና ክብር መንፈግ እምነት ማጣትንና ለእምነቱ ታማኝነት ማጣትን ያስከትላል፡፡ ይኸውም ነቢይነታቸውን መካድ ማለት ስለ ነቢያት ያስተማሩትንና ያረጋገጡትን ነቢያችን ሙሐመድን (ሰ.ዐ.ወ) መካድና ማስተባበል ማለት ነው፡፡

ስማቸውና ሸሪዓቸው (መለኮታዊ ህጋቸው) በሚገባ የታወቁት እንደ አደም፣ ኑህ፣ ኢብራሂም፣ ዳውድ፣ ሱለይማን፣ ሙሳ፣ ኢሳና ሌሎች በቁርአን የተጠቀሱ ነቢያት በሙሉ ማመን አለብን፡፡ የአንዳቸውንም ነብይነት የሚክድ ሰው በርግጥ የሁላቸውንም ነቢይነት

የካደ ነው፡፡ በተለይም ደግሞ የነቢያችንን (ሰ.ዐ.ወ) ነብይነት ያስተባበለ ነው፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ በመጽሐፍታቸውና በተገለጠላቸው መለኮታዊ መልዕክት ማመን አለብን፡፡ ነገር ግን አሁን በእጃችን ውስጥ የሚገኙት ተውራህ (የሙሳ (ዐ.ሰ) መጽሐፍት) እና የወንጌል መጽሐፍት በሙሳና ዒሳ ላይ የወረዱ (የተገለጡ) መጽሐፍት እንዳልሆኑ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በግል ፍላጎታቸውና በስግብግብነታቸው የታወሩ አንዳንድ ሰዎች የራሳቸውን አስተሳሰብ በመጨመር ለመለወጥና ለመበረዝ በቅተዋል፡፡ ስለዚህም አብዛኞቹ ወይም ሁሉም የተሰበሰቡትና የተጠናቀሩት ከሙሳና ዒሳ ዘመናት በኋላ በአንዳንድ ተከታዮቻቸው አማካይነት ነው፡፡

## 19. ኢስላምን በተመለከተ ያለን እምነት

إِنَّ الدِّينَ عِنْدَ اللَّهِ الْإِسْلَامُ

«***አላህ ዘንድ እውነተኛውና ትክክለኛው ኃይማኖት ኢስላም***» መሆኑንና (3፡19) ቀደምት መለኮታዊ ህግጋትን (ሸሪዓዎችን) የሻረ እውነተኛ መለኮታዊ ህግ (ሸሪዓ)

መሆኑን እናምናለን፡፡ የሰው ልጆችን ፍላጎትና ደስታ ያገናዘበና በዚህ ዓለምም ሆነ በቀጣዩ ዓለም የሚፈልጉትን ነገር ያካተተ ፍጹም የሆነ ሸሪዓ ነው፡፡ ፍጹም ጊዜ የማያልፈበትና ለዘለዓለም የሚቆይ ነው፤ የማይቀየርና በምንም መልኩ የማይለወጥ ነው፤ ለሰው ልጅ የሚያስፈልጉ ግለሰባዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ መመሪያዎችንና ህግጋትን በሙሉ የያዘ ነው፡፡ የመጨረሻው ሸሪዓ በመሆኑ በጭቆናና በሙስና ውስጥ እየተፈዘቀ ያለውን ሰብዓዊነት ለማደስና ለማንሰራራት የሚመጣ ሌላ ኃይማኖት የመጠበቅ ተስፋ ሊኖር አይችልም፡፡ ስለዚህ ኢስላማዊ ኃይማኖት ጠንካራ የሚሆንበት ዘመንና ፍትህና ህግጋቱ በመላው ዓለም ላይ የሚሰራጭበት ቀን መምጣቱ አይቀሬ እንደሆነ መታሰብ አለበት፡፡ የዓለም ህዝቦች በሙሉ በኢስላም ህግጋት መሠረት በትክክል መኖር ሲጀምሩ ሰላምና ብልጽግና አድጎ በሰው ልጆች መካከል ይንሰራፋል፡፡ የሰው ልጅ ማሰብ የሚችለውን ከፍተኛን ጣራ ይቆናጠጣል፡፤ ደህንነት፣ ክብር፣ ብልጽግና፣ እርካታና እጹብ ስብዕና ያድጋል፣ ይለመልማል፡፡ ጭቆና፣ ድህነትና ችግር

ከመሬት ገጽ ላይ ጠፍተው በሰው ልጆች መካከል ወንድማማችነትና ፍቅር ይሰፍናል፡፡

በአሁኑ ወቅት እራሳቸውን ሙስሊም ብለው በሚጠሩ ህዝቦች ውስጥ የሚታየው አሳፋሪ ሁኔታ የተፈጠረበት ምክንያት ከጅምሩም ባህሪያቸውና ተግባራቸው በኢስላማዊ ህግጋት ያልታነጸና ህይወታቸው ኢስላምን መሠረት ያደረገ ባለመሆኑ ነው፡፡ ይህ አሳፋሪ ሁኔታ ለዘመናት እየቀጠለና በየጊዜው እየተባባሰ መጥቷል፡፤ ኢስላምን መቀበላቸው ለዚህ ውርደትና ኋላ-ቀርነት መንስኤ ሆኖ አያውቅም፣ ሊሆንም አይችልም፡፡ በተቃራኒው ለዚህ ያበቃቸው አስተምህሮዎቹን ያለመታዘዛቸው፣ ኢስላማዊ ህግጋትን ችላ በማለታቸው፣ መሪዎቻቸው በደኃው ህብረተሰብ ላይ ያደረሱት ጭቆናና ያላቸው ጥላቻ ማየሉና በህዝቡ ላይ የሚደርሰው ግፍ በመብዛቱ፣ እነዚህ እኩይ ተግባራት ዕድገታቸውን ሽባ አደረገው፣ ጉልበታቸው ተሰለበ፣ መንፈሳቸው ታወከ፣ ለአደጋና ሰቆቃ ዳረጋቸው፡፡ አላህ በጥፋታቸውና በኃጢአታቸው አጠፋቸው፡-

ذَٰلِكَ بِأَنَّ اللَّهَ لَمْ يَكُ مُغَيِّرًا نِعْمَةً أَنْعَمَهَا عَلَىٰ قَوْمٍ حَتَّىٰ يُغَيِّرُوا مَا بِأَنْفُسِهِمْ وَأَنَّ اللَّهَ سَمِيعٌ عَلِيمٌ

«*ይህ (ቅጣት) አላህ በሕዝቦች ላይ የለገሰውን ጸጋ በነፍሶቻቸው ያለውን ነገር እስከሚለውጡ ድረስ የማይለውጥ በመሆኑ ምክንያት ነው፡፡ አላህም ሰሚ ዐዋቂ ነው፡፡*» (8፡53)

እንዲሁም፡-

لَا يُفْلِحُ الْمُجْرِمُونَ

«...*እነሆ አመጸኞች አይድኑም፡፡*» (10፡17)

እንዲሁም፡-

وَمَا كَانَ رَبُّكَ لِيُهْلِكَ الْقُرَىٰ بِظُلْمٍ وَأَهْلُهَا مُصْلِحُونَ

«*ጌታህም ከተሞችን ባለቤቶቻቸው መልካም ሠሪዎች ሆነው ሳሉ በመበደል የሚያጠፋቸው አልነበረም፡፡*» (11፡117)

በሌላም ቦታ፡-

وَكَذَٰلِكَ أَخْذُ رَبِّكَ إِذَا أَخَذَ الْقُرَىٰ وَهِيَ ظَالِمَةٌ إِنَّ أَخْذَهُ أَلِيمٌ شَدِيدٌ

«***የጌታህም ቅጣት የከተሞችን ሰዎች እነሱ በዳዮች ሲሆኑ በቀጣቸው ጊዜ እንደዚህ ነው፡፡ ቅጣቱ በእርግጥ አሳማሚ ብርቱ ነው፡፡***» (11፡102)

የኃይማኖቱ ህግጋትና አስተምህሮዎች በወረቀት ላይ የሰፈረ ቀለም ብቻ ሆኖ የቀረበት ሁኔታና ህዝቡ ትንሽም እንኳ ብትሆን በህግጋቱ መሠረት መኖር ባልቻለበት ሁኔታ ኃይማኖቱ ይህንን ህዝብ ካለበት ጥልቅ አረንቋና የዘለዓለም ቅጣት ያድነዋል ብሎ ማሰብ ከቶ እንዴት ይቻላል?

የኢስላም አበይት መሠረቶች፡- በአላህ ማመን፣ ቅንነት፣ እውነተኛነት፣ ታማኝነት፣ መልካም ስብዕና፣ ርህሩህነትና ለጋስነት እንዲሁም አንድ ሙስሊም ለራሱ የወደደውን ነገር ለወንድም መውደድ እንዳለበት ወዘተ... ናቸው፡፡

ነገር ግን ሙስሊሞች እነዚህን ወደ ኋላ ከተዉ ዘመናት አልፈዋል፡፡

ሙስሊሞች በየጊዜው በተለያዩ አንጃዎችና ቡድኖች ሲከፋፈሉና ሲናቆሩ እናያለን፡፡ ኢስላምን ወደ ኋላ ትተው፣ የራሳቸውንም ሆነ የኅብረተሰቡን ፍላጎት ችላ ብለው ለዓለማዊ ጥቅም ሲሽቀዳደሙ፣ ሲፎካከሩና ባልታወቁ ወይም በተፈበረኩ አጉል ምክንያቶች በማይረባ ነገር አንዱ ሌላውን ሲወነጅልና ሲያከፍር (በከሃዲነት ሲፈርጅ) እናያለን፡፡ እንዲህም እያሉ ይጨቃጨቃሉ፡- ቁርአን ፍጡር ነው ወይስ አይደለም? ጀነትና ጀሀነም ተፈጥረዋል ወይስ ገና ወደፊት የሚፈጥ ናቸው? ሌሎች ብዙ ምሳሌዎች ማንሳት ይቻላል፡፡ እንደዚህ ዓይነቶቹ ክርክሮች የሚያሳዩት እነዚህ ሰዎች በግልጽ የተነገራቸውን ቀጥተኛውን መንገድ ትተው ወደ ጥፋትና ውድመት እያመሩ መሆናቸውና በየቀኑ የባሰ እየጠመሙና እያፈነገጡ የሚሄዱ መሆናቸውን ነው፡፡ መኃይምነትና ድርቅና የተጠናወታቸው ትምክህተኞች ናቸው፡፡ በማይረቡና በአጉል ጉዳዮች እራሳቸውን የጠመዱና የሌሉ ልበ-ወለዳዊ ነገሮችን በመዘባረቅ ጊዜ

የሚያጠፉ የህብረተሰብ ጠንቆች ናቸው፡፡ መጨቃጨቅና መዋጋት፣ በማይረቡ ነገሮች ላይ ክርክርና ሁካታ መፍጠር መጨረሻ የሌለው አረንቋ ውስጥ ይባስ እንዲዘፈቁ አደረጋቸው፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ ምንጊዜም ጥንቁቅና ንቁ የሆኑትና ነገር ግን የኢስላም ቀንደኛ ጠላት የሆኑትን ምዕራባዊያን ሙስሊሙ የተዘናጋና እያንቀላፋ ባለበት ሁኔታ ኃይለኛ ሆነው ኢስላማዊውን መሬት በቅኝ ግዛት ሊቆጣጠሩ ቻሉ፡፡ ይህ አሳዛኝ ሁኔታ ምን ያህል እንደሆነና መቼ እንደሚያበቃ አላህ ብቻ ነው የሚያውቀው፡፡

አላህ በቁርአኑ ሊናገር፡-

وَمَا كَانَ رَبُّكَ لِيُهْلِكَ الْقُرَىٰ بِظُلْمٍ وَأَهْلُهَا مُصْلِحُونَ

«***ጌታህም ከተሞችን ባለቤቶቻቸው መልካም ሠሪዎች ሆነው ሳሉ በመበደል የሚያጠፋቸው አልነበረም፡፡***»
(11፡117)

ሙስሊሞች ከእንቅልፋቸው ካልባነኑና ካልነቁ፣ ተግባሮቻቸውን በደንብ ካላጤኑና እራሳቸውንና ትውልዳቸውን በትክክለኛው ኢስላማዊ አስተምህሮ

በማነጽ ጭቆናና በደልን ማስወገድ ካልቻሉ ዛሬም ሆነ ነገ የሙስሊሙን ስኬት የሚያረጋግጥ አማራጭ የለም፡፡ በዚህ መልኩ ብቻ ነው ከዚህ ታላቅ አደጋ መዳን የሚችሉት፡፡ በአላህና በመልዕክተኛው እንደተረጋገጠው ጭቆናንና ጭካኔን በማጥፋት በመላው ዓለም ላይ ፍትህ የማስፈን ኃላፊነት አለባቸው፡፡ ኃይማኖታቸው የመጨረሻው ኃይማኖት በመሆኑ ያለዚህ ኃይማኖት ዓለም ዳግም ልትስተካከልና ልትቃና አትችልም፡፡ በእርግጥ ፈጠራዎችንና ከኢስላም ማፈንገጥን ለመከላከልና አጉል አስተሳሰቦችን ለማጥፋት፣ የሰው ልጆችን ለማዳንና ከጥፋትና ሙስና ለመጠበቅ፣ ከተከታታይ ጭቆናና የጠላትነት መንፈስ ለማጽዳት፣ ለስብዕናና ለሰው ልጅ ህይወት ክብር እንዲሰጥ ለማድረግ ህዝቡ ኢማም (መሪ) የግድ ያስፈልገዋል፡፡ አላህ የመገለጡን ጊዜ ያፋጥንልን ዘንድ እንለምናለን፡፡

## 20. የኢስላም ህግ ሰጭ (ሙሸሪዕ) አስመልክቶ ያለን እምነት

የኢስላም መልዕክት በሙሐመድ ኢብን አብደላህ (ሰ.ዐ.ወ) ማንነት፣ ስብዕናና ህይወት ውስጥ የታቀፈ

መሆኑና ነቢያችን የመጨረሻውና የነቢያት መደምደሚያ መሆናቸውን እናምናለን፡፡ የመልዕክተኞች ሁሉ አለቃና የበላይ እንደሆኑ፣ የመልዕክተኞችና የነቢያት ሁሉ ምርጥ እንደሆኑ፣ የሰብአዊ ፍጡራን ሁሉ ቁንጮና የመጨረሻውን ከፍተኛ ቦታ የያዙ፣ በሞገስና በዕውቀት፣ በለጋስነትና አዕምሮ፣ በጽድቅና በአጠቃላይ መልካም ባህሪያት የሚወዳደራቸው ማንም እንደሌለ እናምናለን፡፡ በእውነቱ የመጠቀ መልካም ስብዕናና ድንቅ ባህሪይ የተላበሱ ለዘለዓለም ምትክና አምሳያ የማይገኝላቸው ሰው ናቸው፡፡

## 21. በቁርአን ማመን

ቁርአን መለኮታዊ እንደሆነ፣ ከኃያሉ አላህ በተከበረው ነቢይ ምላስ ላይ የተገለጠ እንደሆነ፣ አላህ ሁሉን ነገር ግልጽ ያደረገበት ዘለዓለማዊ ተዓምር መሆኑን እናምናለን፡፡ በምጥቀቱ፣ በግልጽነቱ፣ በእውነታውና እውቀት የላቀና የተለየ በመሆኑ ከቁርአን ጋር የሚመሳሰልና የሚወዳደር ነገር ማንም ፍጡር ሊጽፍ አይችልም፡፡ ሊለወጥና ሊበረዝም አይችልም፡፡ ዛሬ በእጃችን ላይ ያለው ቁርአን በነቢዩ ላይ የወረደው ቁርአን

እራሱ ነው፡፡ ከዚህ ውጭ ያለውን ሐሳብ የሚያቀነቅን ሰው አንድም የጥፋትና የእኩይ ተግባርን መንገድ የመረጠ ነው፣ ወይም አጉል ፈላስፋ ነው፣ ወይም ስህተት ውስጥ የተዘፈቀ ሰው ነው፡፡ ሁላቸውም ያፈነገጡና ፈር የለቀቁ ናቸው፡፡ ምክንያቱም አላህ በቅዱስ ቃሉ እንዲህ ይላልና፡-

لَا يَأْتِيهِ الْبَاطِلُ مِنْ بَيْنِ يَدَيْهِ وَلَا مِنْ خَلْفِهِ تَنْزِيلٌ مِنْ حَكِيمٍ حَمِيدٍ

«*ከኋላውም ከፊቱም ውሸት አይመጣበትም፡፡ ጥበበኛ ምስጉን ከሆነው ጌታ የተወረደ ነው፡፡*» (41፡42)

ከቁርአን ተዓምራዊ ተፈጥሮዎች ማስረጃዎችና ምስክርነት አንዱ ዘመናት ባለፉ ጊዜና ጥበባትና ሳይንሶች ባደጉ ቁጥር ቁርአን በመጠቀ ዓላማውና ፍጹምነቱ ምንጊዜም አዲስና የማይዛባ፣ ጊዜ የማያልፍበትና ትኩስ ሆኖ ለዘለዓለም መኖሩ ነው፡፡ ቁርአን ለጭቅጭቅ የሚፈጥረው መድረክ የለም፣ ከሱ ጋር ለመጋፈጥ የሚያስችል መሠረትም አይኖርም፡፡ ቁርአን ሳይንሳዊ እውነታዎችን አይጻረርም፡፡

አዎንታዊ ፍልስፍናዊ አስተሳሰብንም አይቃረንም፡፡ እንዲያውም በተቃራኒው የሚቃረኑና የሚጋጩ ሐሳቦችን የያዙና ከዚህም አልፎ የተሳሳተ መደምደሚያዎች የሚገኙባቸው መጽሐፍት በትምህርቱ ዓለም እንደ ዋና ምንጭነት የሚታዩ የሳይንቲስቶችና የታላላቅ ፈላስፋዎች መጽሐፈት ናቸው፡፡ በተጨማሪም ሳይንሳዊ ምርምሮችና ዘመናዊ ሳይንሳዊ ቲዮሪዎች እያደጉ በመጡ ቁጥር ዓለም ያወቃቸውና ከነሱ በኋላ የመጣው ትውልድ ሁሉ የሳይንስና የዕውቀት አባቶች እንደሆኑ የመሰከሩላቸው እንደ ሶቅራጥስ፣ ፕሌቶና አሪስቶትል ያሉ ታላላቅ የግሪክ ፈላስፎች እንኳ አንዳንድ ስህተቶች እንደሰሩ/እንደተሳሳቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ለታላቁ ቁርአን በቃልም ሆነ በተግባር ትልቅ ክብር መስጠት እንዳለብን እናምናለን፡፡ ስለዚህ አንዷን ፊደል እንኳ ቢሆን እያወቅን ማንቋሸሽና ያለአግባብ መጠቀም የለብንም፡፡ ጣሂር(ንጹህ) ባልሆነ ሰው መነካት የለበትም፡፡ በቁርአን ውስጥ እንዲህ ተብሏል፡-

لَا يَمَسُّهُ إِلَّا الْمُطَهَّرُونَ

«*የተጥራሩት (ሙጠሐሩን) እንጅ ሌላ አይነካውም፡፡*» (56፡79)

*ይህ ጉዳይ በኢስላማዊ ህግ መጽሐፍት ውስጥ በዝርዝር ቀርቧል፡፡*

ቁርአን ማቃጠልም ሆነ በማንቋሸሽ መልክ መወርወር፣ ማቆሸሽ፣ በእግር መርገጥና በቆሻሻ ቦታዎች ማስቀመጥ ፍጹም የተከለከለና የተወገዘ ነው፡፡ ከነዚህ ተግባራት ውስጥ እያወቀ በድፍረት አንዱንም የፈጸመ ሰው በቁርአንና በቅድስናው ያላመነ ሰው በመሆኑ ከከሃዲዎች (ካፊሮች) ጎራ ይመደባል፡፡ በእርግጥ ይህ ሰው በዓለማት ጌታ በአላህ የካደ ነው፡፡

## 22. ኢስላምንና ቀደምት ኃይማኖቶችን የማረጋገጫ መንገድ

አንድ ሙስሊም ያልሆነ ሰው ከተከራከረንና የኢስላምን እውነተኛነት ለማረጋገጥ ማስረጃ እንድናቀርብ ቢጠይቀን ቀደም ሲል እንደተገለጸው በቁርአንን ዘለዓለማዊ

ተዓምራዊነትና ተዓምራዊ ተፈጥሮውን መሠረት በማድረግ ልናረጋግጥለት እንችላለን፡፡

ነገር ግን እዚህ ላይ ዓለማችን የራሳችንን አዕምሮ ለማርካትና የኢስላምን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ያለንን ምኞት ለማሟላት ነው፡፡ ምክንያቱም አንዳንዴ መሰል ጥያቄዎች ነፃ በሆነ አዕምሮ በሚያስብ ሰው ጭንቅላት ውስጥ መመላለሳቸው ስለማይቀር ነው፡፡ ይህንንም የሚያደርገው እምነቱን ለማጠንከርና ብዥታ የፈጠሩበትን ነገሮች በግልጽ ለመረዳት ሲሻ ነው፡፡

እንደ አይሁድ ክርስትና የመሳሰሉ ቀደምት ኃይማኖቶችን በተመለከተ ግን እውነተኛነታቸውን ለማረጋገጥና ራሳችንንም ሆነ ሌላውን የሚጠራጠራቸውን ለማርካት በኢስላም ላይ እምነት ከሌለን ማስረጃ ማቅረብ አንችልም፡፡ ምክንያቱም እንደ ቁርአን ያለ ዘለዓለማዊ ማስረጃ የላቸውምና፡፡ ተከታዮቻቸው እንደ ማስረጃ የሚያቀርቧቸው የቀደምት ነቢያት ተዓምራትም ተቀባይነት የላቸውም፡፡ ምክንያቱም የዘገባቸው ወይም ትረካቸው ትክክለኛነት አጠራጣሪ ስለሆነ ነው፡፡ ወደኛ

የተላኩ የቀደምት ነቢያት መጽሐፍት፣ ማለትም እንደ ተውራህና ወንጌል ያሉ ለነዚህ ነቢያት የተገለጡ መጽሐፍት የኃይማኖታቸውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የሚቀርቡ ዘለዓለማዊ ተዓምራት በምንም መልኩ ሊሆኑ አይችሉም፡፡ ነገር ግን ይህ በኢስላም ተረጋግጧል፡፡

ኢስላምን ከተቀበልንና ካመንበት፣ ኢስላም ባመጣውንና ባረጋገጠው ማንኛውም ነገር ማመን እንዳለብን ግልጽ ነው፡፡ ከአስተምህሮዎቹ አንዱ ደግሞ ቀደም ሲል እንደተገለጸው በቀደምት ነቢያት ነቢይነት ማመን ነው፡፡ ስለዚህ አንድ ሙስሊም የኢስላምን አስተምህሮ ከተቀበለ በኋላ የክርስትናን ወይም የአይሁድን ወይም የሌሎች መሰል ኃይማኖቶችን ትክክለኛነት መገምገም አያስፈልግም፡፡ ምክንያቱም በኢስላም ማመን በቀደምት ኃይማኖቶችና ነቢያት ማመንም የግድ ያካትታል፡፡ በተጨማሪም ሙስሊሙ የቀደምት ነቢያትን ተዓምራት ትክክለኛነት ማረጋገጥ አይጠበቅበትም፡፡

ነገር ግን አንድ ሰው የኢስላም ኃይማኖትን መርምሮና አጥንቶ ነገር ግን ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ካልቻለ ወይም

ካላመነበት የክርስትና ኃይማኖትን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ መገምገም ግዴታ ይሆንበታል፡፡ ምክንያቱም ከኢስላም ቀጥሎ የነበረ ኃይማኖት ክርስትና ስለሆነ ነው፡፡ ክርስትናም ካላሳመነው ከዛ ቀጥሎ የነበረውን የአይሁድ ኃይማኖትን ማጥናት አለበት፡፡ በዚህ መልኩ ትክክለኛነቱን የሚያምንበትን ኃይማኖት እስኪያገኝ ድረስ መቀጠል አለበት፡፡

በተመሳሳይ ምክንያት የአይሁድ ኃይማኖት (ጁዳይዝም) ወይም የክርስትና ኃይማኖት ተከታይ ሆኖ ያደገ ሰው ከራሳቸው ነቢይ በኋላ በተነሳ ሌላ ነቢይ የሚሰበክን ኃይማኖት ከግምት ማስገባትና መከታተል እንዳለባቸው ግልጽ ነው፡፡ ለምሳሌ ቀደም ሲል ኃይማኖትን መርምሮ እውነት ላይ የመድረስ አስፈላጊነትን አስመልክቶ እንደተጠቀሰው አይሁዳውያን ኢስላምንና ክርስትናን መገምገምና እውነታውን ማወቅ አለባቸው፡፡ እንደዚሁም ክርስቲያኖች የኢስላምን እውነታ መመርመርና መጠየቅ አለባቸው፡፡ ይህ ደግሞ የሚያመለክተው አንዳቸውም (አይሁድም ሆነ ክርስቲያን) በራሳቸው ኃይማኖት ያመኑ ናቸው ተብለው ከዚያ በኋላ የመጡትን ኃይማኖቶች

በመተዋቸው በይቅርታ የሚታለፉ አይደሉም፡፡ ምክንያቱም በአይሁድ ኃይማኖትም ሆነ በክርስትና ውስጥ ቀጥሎ የመጡትን ኃይማኖቶች የሚቃረን ነገር የለምና፡፡ ይኸውም ሙሳም (ዐ.ሰ) ሆነ ኢሳ (ዐ.ሰ) ከነሱ በኃላ ነቢይ እንደማይነሳ የተናገሩት ነገር የለም፡፡ አይሁዶችም ሆነ ክርስቲያኖች ቀጥሎ የመጣውን ኃይማኖት እውነተኛነት ሳይመረምሩና ከግምት ሳያስገቡ በኃይማኖታቸውና በእምነታቸው እንዴት እርግጠኛ መሆን እንደቻሉ የሚያስገርም ነው፡፡

ከኃይማኖታቸው በኋላ የመጣውን ሌላ ኃይማኖት ወይም ኃይማኖቶች እውነተኛነትን አስመልክቶ ምርምር ማድረግና መገምገም አዕምሮአዊ ግዴታ ነው፡፡ መርምረውና ገምግመው እውነታው ላይ መድረስ ካልቻሉ ቀደም ሲል በነበረባቸው እምነት ላይ ፀንተው መቀጠል አለባቸው፡፡ በሌላው አንፃር ግን ቀደም ሲል እንደተገለፀው ሙስሊሙ በኢስላም ማመኑ ቀደም ሲል የነበሩና ኃይማኖቶችንም ሆነ ወደፊት መምጣት የሚችሉትን ኃይማኖቶችን እውነታ መገምገምና ማወቅ አያስፈልገውም፡፡ ቀድሞ የነበሩ ኃይማኖቶችን

በተመለከተ ኢ.ስላም ያረጋገጣቸውና እውቅና የሰጣቸው ናቸው፡፡ ነገር ግን ኢ.ስላም በነሱ ላይ የበላይ ሆኖ ስለተካቸውና ስለጠቀለላቸውና ስለሻራቸው ሙስሊሙ በህግጋታቸውም ሆነ በመጽሐፍታቸው መተዳደር የለበትም፡፡ ከኢ.ስላም ቀጥሎ ሊከሰት የሚችልን ኃይማኖት በተመለከተ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የሚከተለውን ተናግረዋል፡፡

«*ከኔ በኋላ የሚመጣ ነቢይ የለም፡፡*»

በሙስሊሙ ዓይን ነቢዩ እውነት የሚናገሩ ታማኝ ስለሆኑ አላህም በቁርአኑ፡-

وَمَا يَنْطِقُ عَنِ الْهَوَىٰ. إِنْ هُوَ إِلَّا وَحْيٌ يُوحَىٰ

«***ከራሱ ፍላጎት የሚናገረው አንዳችም ነገር የለም፣ የተገለጠለትን (በወህይ የተነገረውን) ካልሆነ በቀር***» (53፡ 3-4)

በማለት ስለመሰከረላቸው ከኢ.ስላም በኋላ ስለሚመጣ አዲስ ኃይማኖት ውሸት ማረጋገጡም አስፈላጊ አይደለም፡፡

እንግዲህ ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) በኋላ ባሉት ረዥም ዘመናት ውስጥ ብዙ ሐሳቦች፣ እምነቶችና ቡድኖች ስለተከሰቱ ለነቢዩ የተሰጡትን የአላህ ትዕዛዛት በትክክል ለመታዘዝና ግዴታውን ለመወጣት ሙስሊሙ ወደ ትክክለኛውና ወዳልተበረዘው ሱና የሚመራውን መንገድ የመምረጥ ግዴታ አለበት፡፡ ምክንያቱም አንድ ሙስሊም የአላህን ትዕዛዛትና መመሪያዎች መከተልና መታዘዝ ያለበት ለነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) በተሰጡትና ነቢዩ በተገበሩትና ባስተማሩት መልኩ መሆን አለበት፡፡ ታዲያ እነዚህ ትዕዛዛት በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ላይ ከወረዱት ትዕዛዛት ጋር አንድ መሆናቸውን እንዴት እርግጠኛ መሆን ይችላል? ሙስሊሞች አስተሳሰባቸውን መሠረት በማድረግ በብዙ ቡድኖች እንደተከፋፈሉ ሁሉ ሰላታቸው፣ ሌሎች ዒባዳዎች (የአምልኮ ተግባራት) እና ፀባያቸውም ይለያያል፡፡ ስለዚህ ምን ማድረግ አለባቸው? ጋብቻ፣ ፍቺ፣ ውርስ፣ ግብይት፣ ቅጣት፣ የደም ካሳና የመሳሰሉትን ጉዳዮች አስመልክተው የትኛውን መዝሀብ (ቡድን) መከተል አለባቸው? ሙስሊሙ ምን ማድረግ አለበት?

አባቱን፣ ቤተሰቡን ወይም ጓደኛውን በደፈናው መከተሉ ትክክል አይሆንም፡፡ በሚያምንበት ነገር እርግጠኛና ጽኑ መሆን ይጠበቅበታል፡፡ በኃይማኖት ውስጥ ጥርጣሬ፣ ጎደሎነት ወይም አጥባቂነት የለም፡፡ ትክክለኛና በላጭ ብሎ የሚያምነውን መንገድ መምረጥ አለበት፡፡ ኃይማኖታዊ ግዴታዎቹን ለመወጣት፣ ጌታውን አስመልክቶ ያለበትን ኃላፊነት ለመወጣትና ከአላህ ቅጣት ለመዳን (ትክክል እንደሆኑ አስቦ በሠራቸው ሥራዎች ለቅጣት እንዳይዳረግ አዕምሮውን ተጠቅሞ ትክክለኛውን ጎዳና የመምረጥ ግዴታ አለበት፡፡ እንዲሁም ቀጥተኛውንና ትክክለኛውን መንገድ በመከተሉ የሚወቅሱትንና የሚያላግጡበትን ሰዎች መስማት የለበትም፡፡ ለአሉባልታ ብሎ ሐቁንና እውነታውን መሸፋፈን አይገባም፡፡

አላህ እንዲህ ይላል፡-

أَيَحْسَبُ الْإِنْسَانُ أَنْ يُتْرَكَ سُدًى

«*የሰው ልጅ እንዲሁ ያለ ዓላማ የሚቀር ይመስለዋልን?*» (75፡36)

እንዲሁም፡-

بَلِ الْإِنْسَانُ عَلَىٰ نَفْسِهِ بَصِيرَةٌ

«***በእርግጥም ሰው በነፍሱ ላይ አስረጅ ነው፡፡***» (75፡14)

እንዲሁም፡-

إِنَّ هَٰذِهِ تَذْكِرَةٌ فَمَنْ شَاءَ اتَّخَذَ إِلَىٰ رَبِّهِ سَبِيلًا

«***ይህቺ መገሠጫ ናት፡፡ የሻም ሰው ወደ ጌታው መንገድን ይይዛል፡፡***» (76፡29)

እራሱን መጠየቅ ያለበት የመጀመሪያው ጥያቄ መከተል የሚገባው መንገድ የአህለል ቤይት (የነቢዩ ቤተ-ዘሮች) መንገድን ነው ወይስ ሌላ ነው የሚለው ነው፡፡ የነቢዩን ቤተ-ዘሮች መንገድ የሚመርጥ ከሆነ ከአስራ ሁለቱ ኢማሞች መንገድ (በኢስነ-ዐሸሪያህ) እና ከሌሎች ቡድኖች አንዱን መምረጥ አለበት፡፡ ወይም ደግሞ የሱኒ መንገድ የሚመርጥ ከሆነ ከአራቱ መዝሐቦች የትኛውን እንደሚከተል መምረጥ አለበት፡፡ እነዚህ ጥያቄዎች ሁሉ የሚነሱት በነፃነት የሚያስብ አዕምሮ ላለው ሰው ነው፡፡

ስለዚህ ውኹርንብር እንዳይፈጠርበት አዕምሮውን ግልጽና ነፃ አድርጎ መጠበቅ አለበት፡፡

ስለዚህ የኢስነ-ዐሽሪያህ እምነት መሠረት የሆነውን የኢማማህ (መሪነት) ጉዳይ እናንሳ፡፡ በሚቀጥለው ክፍል ውስጥ በዝርዝር ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

# ክፍል ሶስት

# አል-ኢማማህ (የነቢዩ ተተኪዎች መሪነት)

## 23. የነቢዩ ተተኪዎች መሪነት (አል-ኢማማህ) አስመልክቶ ያለን እምነት

ኢማማህ ከኢስላም መሠረቶች (አሱል አል-ዲን) አንዱ እንደሆነና በዚህ ካላመነ የሰው ልጅ እምነት የተሟላ እንዳልሆነ እናምናለን፡፡ የፈለገውን ያህል ብናከብራቸው እንኳ በዚህ ጉዳይ ላይ አባቶቻችንን፣ ቤተሰቦቻችንን ወይም መምህራንን መከተል ትክክል አይደለም፡፡ ምክንያቱም ተውሂድንና ኑቡወህን መቀበል ግዴታ እንደሆነ ሁሉ ኢማማንም መቀበል የግድ ስለሆነ ነው፡፡ ኢማማህ መታየት ያለበት ተውሂድና ኑቡወህ መታየት ባለባቸው ሁኔታ ነው ማለት ነው፡፡ አንድ ሰው በኢማማህ የማያምን ከሆነና የኢስላም መሠረት አይደለም ብሎ የሚያስብ ከሆነ ይህን ጉዳይ በተመለከተ ምናልባት እራሱን ከኃላፊነቱ ነፃ ለማድረግ ቢያንስ የኢማማህን

ጽንሰ-ሐሳብ መመርመርና ጥናት ማድረግ አለበት፡፡ ይህ ማለት በጭፍን ውሳኔ ከመውሰዱ በፊት ጉዳዩን በሚገባ ማጤንና ከመሰረቱ ማወቅ አለበት፡፡ ይህንን ጉዳይ ማንሳት ያስፈለገበት ምክንያት ኃይማኖታዊ ግዴታዎቻችንን በሚመለከት መመሪያዎችን ከአላህ በቀጥታ መቀበል ስለማንችል በዚህ ጉዳይ ላይ አንድ የምንተማመንበትና የምንከተለው ሰው መኖር አለበት፡፡ ላጠፉነው ስህተት አላህ በኃላፊነት እንደማይጠይቀን እርግጠኛ የምንሆንበት የምንከተለው ሰው ሊኖር ግድ ይላል፡፡ እንደኛ እምነት የነቢዩ ቤተዘሮች አባላት ይህንን መስፈርት ያሟላሉ፡፡

አላህ በፀጋውና በምህረቱ አንድን ሰው ነቢይ አድርጎ መላክ እንዳለበት ሁሉ ነቢዩን ተክቶ ህዝቡን ወደ ቀናው መንገድ የሚመራና የነቢዩን ሥራ በወኪልነት የሚሰራ ኢማምም መምረጥ አለበት፡፡ ህዝቡን ወደ ቀጥተኛው መንገድ የሚመራ፣ መልካምን የሚያስተምርና በዚህ ዓለምም ሆነ በወዲያኛው የሰው ልጅ ደስታና ብልጽግና ይጎናጸፍ ዘንድ መንገዱን የሚያሳይ መሪ ያስፈልጋል፡፡ ኢማም እንደ ህዝብ መሪነቱ በሁሉም የህይወት መስክ በህዝቡ ውስጥ ከፍተኛውን ቦታ የያዘና ከሁሉም የላቀ

መሆን አለበት፡፡ በዚህም በህዝቡ ውስጥ ፍትህ እንዲጎለብትና ከመካከላቸው ጠላትነትና ጭቆና እንዲወገድ፣ ሰላምና መረጋጋት እንዲሰፍን መትጋት አለበት፡፡ ስለዚህ ኢማምነት ከነቢይነት የመነጨና የቀጠለ ሲሆን ለነቢይነት አስፈላጊነት የምናስቀምጣቸው ምክንያቶች ለኢማምነት አስፈላጊነትም የምናስቀምጣቸው ናቸው፡፡

በዚህ ምክንያት ነው እንግዲህ የአንድ ሰው ኢማም ሆኖ መመረጥ የሚመጣው በአላህ ፈቃድ በነቢዩ ወይም ቀደም ሲል ባለው ኢማም በኩል ብቻ እንደሆነ የምንናገረው፡፡ ህዝቡ ኢማም የመምረጥ መብት የለውም፡፡ ከስልጣን ማውረድ ካለባቸው ደግሞ፡- *«የዘመኑን ኢማም ሳያውቅ የሞተ ሰው በጃሂሊያ (በድንቁርናው ዘመን) እንደሞተ ይቆጠራል፡፡»* ይህ ከታላቁ ነቢይ የተነገረ ሰሂህ ሐዲስ ነው፡፡ ከዚህ መረዳት የምንችለው በአላህ የተመረጠ ኢማም የማይኖርበት ዘመን መኖር እንደማይችልና ሰዎች አመኑበትም አላመኑበትም፣ ረዱትም አልረዱትም፣ ታዘዙትም አልታዘዙትም፣ ከሰዎች እይታ ውጭ ቢሆንም ልዩነት እንደማይፈጥር ነው፡፡ ነቢዩ በአንድ ወቅት ዋሻ ውስጥ በነበሩ ጊዜና ወደ ተራራ በሸሹበት ወቅት ከሰው

እይታ ተሰውረው እንደነበረ ሁሉ ኢማምም ከሰው እይታ ተሰውሮ በኢማምነቱ ሊኖር ይችላል፡፡

(ነቢዩ ከመዲና ወደ መካ በተሰደዱ ጊዜ ሦስት ቀናትን በስውር ዋሻ ውስጥ ከአቡ በክር ጋር አሳለፉ፡፡ የመካ ቁሬይሾች ተከትለው ዋሻው ድረስ ቢደርሱም ሸረሪት በዋሻው መግቢያ ላይ ድሯን አድርታ ስላዩ ሰው እዚህ ውስጥ ሊገባ አይችልም ብለው ስላሰቡ ነቢዩን ሳያገኙ ተመለሱ፡፡ ለሂጅራ ጥቂት ዓመታት ሲቀሩ ቁሬይሾች ከሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) እና ከተከታዮቹ ያላቸውን ማንኛውንም ግንኙነት ለማቋረጥና ምንም ዓይነት ነገር ላለመለዋወጥ ወሰኑ፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ተከታዮቻቸውን መካ አቅራቢያ ወደሚገኝ አንድ ተራራ አንቀሳቀሱ፡፡ እዚህም ቦታ ለሦስት ዓመታት ገደማ ቆዩ፡፡ ብዙ ችግር ገጠማቸው፡፡ ከውጭው ዓለም ጋር መገናኘት የሚችሉት ስምምነት ላይ በደረሱባቸው ወራት ውስጥ ብቻ ነበር፡፡)

ምክንያታዊ ሆነን ስናየው ደግሞ ከእይታ የመሰወሪያ ጊዜው አጭር ወይም ረዥም መሆኑ ልዩነት አያመጣም፡፡

**አላህ እንዲህ ብሏል፡-**

وَلِكُلِّ قَوْمٍ هَادٍ

«...***ለእያንዳንዱ ህዝብ መሪ አለ፡፡***» (13፡7)

**እንዲሁም፡-**

وَإِنْ مِنْ أُمَّةٍ إِلَّا خَلَا فِيهَا نَذِير

«...***ማንኛይቱም ሕዝብ በውስጧ አስፈራሪ ያላለፈባት የለችም፡፡***» (35፡24)

## 24. የኢማም እንከን-የለሽነት (ዕሰማህ) በተመለከተ ያለን እምነት

**ነቢይ እንከን-የለሽ (*መዕሱም*) እንደሆነ ሁሉ ኢማምም እንከን-የለሽ (*መዕሱም*) *መሆኑን* እናምናለን፡፡ ይህም ማለት አንድ ኢማም በህይወት ዘመኑ በሙሉ (ከልደት እስከ ሞት) አውቆም ሆነ ሳያውቅ፣ በገሀድም ሆነ በድብቅ ጥፋት ከመፈጸምና ከመሳሳት የተጠበቀና የጠራ ነው ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም ኢማሞች ኢስላምን ጠብቀው የሚያቆዩና የሚከለከሉ የነቢያት ተወካዮች ናቸውና፡፡**

በኢስላም ውስጥ ያላቸው ቦታና ደረጃ ነቢዩ ካለው ቦታ ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ እንከን-የለሽ የመሆናቸው አስፈላጊነት ምክንያትም የነቢይ እንከን-የለሽነት አስፈላጊነት ምክንያት ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ በዚህ ረገድ በሁለቱ መካከል ልዩነት የለም፡፡

አንድ የአረብኛ አባባል እንዲህ ይላል፡-

ليس على الله بمستنكر ان يجمع العالم فى واحد

*«በአንድ ሰው ሥር መሰብሰብ ጠቅላላውን ዓለም*
*ለሁሉን ቻይ አላህ የሚሳን አይደለም»*

## 25. የኢማም ባህሪያትና ዕውቀትን በተመለከተ ያለን እምነት

ልክ እንደ ነቢይ ኢማምም ከሰው ልጅ ውስጥ ምርጥና በላጭ እንደሆነና እንደ ጀግንነት፣ ልግስና፣ ጨዋነት፣ እውነተኛነት፣ ታማኝነት፣ ፍትሓዊነት፣ ቻይነት፣ ምክንያታዊነት፣ ጥበብ፣ ግብረ-ገብነትና በመሳሰሉት የሰው ባህሪያት ከሁሉም የላቁና ከፍተኛውን ቦታ የያዙ መሆኑን እናምናለን፡፡ ለዚህ ምክንያቱ የነቢይን በላጭነት

አስመልክቶ የተሰጠ ምክንያት ጋር አንድ ነው፡፡ ኢማም ዕውቀቱን የሚያገኘውና ጥበብን የሚወርሰው ከነቢይ ወይም ቀድሞ ከነበረው ኢማም ነው፡፡ አዲስ ጥያቄ በሚነሳበት ወቅት ከመለኮታዊ መገለጥ በሚያገኘው ዕውቀትና ከአላህ በተሰጠው ብሩህ አዕምሮ በመጠቀም የቀረቡትን ጥያቄዎች የመመለስ ጥበብና ችሎታ የተጎናጸፈ ነው፡፡ አንድን ነገር ለማወቅ ትኩረት ከሰጠው ያለምንም ስህተት በሚገባ የመረዳት ተሰጥኦ አላቸው፡፡ ምክንያቱም ኢማሞች ዕውቀታቸውን የሚቀስሙት ከአዕምሮአዊ ምርምርና ከሰው ልጅ በመማር ሳይሆን ከመለኮታዊ መገለጥ፣ ስለሆነ ነው፡፤ ነገር ግን ዕውቀታቸው ሊጨምርና ሊጎለብት ይችላል፡፡ ይኸውም ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) በዱአቸው ውስጥ፡-

«*ጌታዬ ሆይ! ዕውቀት ጨምርልኝ*» ይሉ ነበር፡፡

በሥነ-ልቦናዊ ምርምር ሊደረስበት እንደተቻለው እያንዳንዱ ሰው በህይወት ዘመኑ አንድን ነገር በተፈጥሮአዊ ግንዛቤው መረዳት የሚችልባቸው አንድ ወይም ሁለት ጊዜያት አሉ፡፡ በእርግጥ ይህ ከአላህ የሆነ የመገለጥ ዓይነት ነው፡፡ ይህ ኃይል እንደየሰው አቅምና

ችሎታ እንጂ ለሁሉም ሰው እኩል አልተሰጠም፡፡ በዚህ ወቅት የሰው ልጅ አዕምሮ ያለ ምንም ማሰብና ምክንያት አንድን እውነታ ለደርስበትና ሊረዳ ይችላል፡፡ እያንዳንዱ ሰው ከራሱ ልምድ በህይወት ዘመኑ ይህ ሁኔታ እንዳጋጠመው ከህይወት ተሞክሮው ለማረጋገጥ ችሏል፡፡

ስለዚህ ቀደምት ፈላስፋዎችም ሆኑ የዘመኑ ፈላስፋዎች እንደገለፁት የሰው ልጅ በዚህ ረገድ የመጨረሻውን ከፍተኛ ደረጃ ሊቆናጠጥ የሚችልበት ሁኔታ ይኖራል ማለት ነው፡፡ ይህንን መገለጥ በመቀበል ረገድ ኢማሞች ከፍተኛውን ደረጃ እንደደረሱ እናምናለን፡፡ ይህ ችሎታ ከመለኮታዊ ኃይል የሚሰጥ ነው እንላለን፡፡ በዚህ መልኩ ኢማሙ ስለማንኛውም መረጃ፣ በየትኛውም ቦታና ወቅት ከመለኮታዊ ኃይል በተሰጠው ጥበብ መሠረት፣ እንዴትና በምን መልኩ እንደሆነ ምክንያት ማቅረብ ሳያስፈልገውና ሌላ ሰው ወይም መምህር ሳያግዘው፣ ባንዴ በሚገባ የመረዳት ኃይልና ችሎታ አለው ማለት ነው፡፡ ስለ አንድ ጉዳይ ለማወቅ ሲያስፈልገው ልክ እንደተወለወለ መስታወት በብሩህ አእምሮው ውስጥ ፍንትው ብሎ ይታየዋል፡፡ ከህይወት ታሪካቸው በግልጽ መረዳት

እንደሚቻለው ልክ እንደማንኛውም ነቢይ ኢማሞችም ከሌላ ሰው ምንም ዓይነት ስልጠና እንዳልወሰዱ እናያለን፡፡ ይኸውም ከልጅነታቸው ጀምሮ እስከ ዕድገታቸው የማንበብና የመጻፍ ክህሎትን ጨምሮ ምንም ዓይነት ስልጠና እንዳልወሰዱ ይታወቃል፡፡ ማንም ፀሐፊ ወይም መምህር ሲያስተምራቸውና መመሪያ ሲሰጣቸው ታይተው አያውቁም፡፡ ነገር ግን በዕውቀታቸው ተወዳዳሪ ያልተገኘላቸውና አንድን ነገር ተጠይቀው አጥጋቢ መልስ ያልሰጡበት አጋጣሚ እንዳልተገኘና ለማንኛውም ጉዳይና ጥያቄ አናውቅም የሚል ምላሽ ሰጥተው እንደማያውቁ ታሪክ ይመሰክራል፡፡ ለተጠየቁት ጥያቄ መልስ ለመስጠት ጊዜ ወስደው አያውቁም፡፡ ለማንኛውም ጉዳይ ምላሽ ለመስጠት በይደር ያቆዩት ነገር አልነበረም፡፡

በአንፃሩ ግን ማንኛውንም ኢስላማዊ ምሁር፣ ፀሐፊ ወይም ሳይንቲስት ብንወስድ በህይወት ታሪካቸው ውስጥ ሳይጥሩና ሳይግሩ እንዲሁም ሌላ ምሁር ሳያስተምራቸው እንዲሁ ዕውቀት የቀሰሙበት አጋጣሚና ስለማንኛውም ነገር ጥርጣሬና ጉድለት እንደሌለባቸው የሚያወሳ ታሪክም የለም፣ በህይወት ታሪኩ ውስጥ ይህን የዘገበ

አንድም ምሁር የለም፡፡ ሰው በተፈጥሮው ይህንን ባህሪ የተላበሰ ነውና፡፡

## 26. ለኢማሞች መታዘዝን አስመልክቶ ያለን እምነት

ኢማሞች ሁለንተናዊ ስልጣን እንዳላቸውና አላህ ሰዎች እንዲታዘዟቸው ያዘዘ መሆኑን እናምናለን፡፡ ኢማሞች ለሰው ልጆች ምስክሮች ናቸው፡፡ ወደ አላህ መንገድ የሚመሩ የተከፈቱ በሮች ናቸው፡፡ የአላህን ወህይ የሚያብራሩ፣ የዕውቀቱ ጠባቂዎች፣ የአንድነቱ ምሰሶዎችና የጥበቡ መገለጫዎች ናቸው፡፡ ክዋክብቶች ለሰማያት እንደሆኑ ሁሉ ለምድር ነዋሪዎች የሰላም ምንጮች ናቸው፡፡ ይህንንም በሚመለከት ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡፡

«*የቤተ-ዘሮቼ (አህለል ቤይቴ) ምሳሌ እንደ ኑህ መርከብ ነው፤ በመርከቡ የተሳፈረ ሁሉ ይድናል፤ በመርከቡ ያልተሳፈረ ወይም ያፈነገጠ ሁሉ ይሰጥማል (ይጠፋል፤)*»

በቁርአን መሠረት ደግሞ ኢማሞች፡-

عِبَادٌ مُكْرَمُونَ. لَا يَسْبِقُونَهُ بِالْقَوْلِ وَهُمْ بِأَمْرِهِ يَعْمَلُونَ

«*...እሱ ሳይናገር የማይናገሩና በትዕዛዙ የሚሠሩ የተከበሩ ባሮች ናቸው፡፡*» (21፡26-7)

እንዲሁም እነዛ ከርክሰት ሁሉ ያራቃቸውና ፍጹም የሆነ ማጥራትን ያጠራቸው ናቸው፡፡

እነሱ የሚያዙትና የሚከለክሉት ነገር አላህ የሚያዘውና የሚከለክለው ነገር መሆኑን እናምናለን፡፡ እነሱን መታዘዝና አለመታዘዝ፣ ከነሱ ጋር መዋዳጀት ሆነ መጣላት፣ ለአላህ መታዘዝና አለመታዘዝ፣ ከአላህ ጋር መወዳጀት ወይም መጣላት ጋር ተመሳሳይ እንደሆነ እናምናለን፡፡ እነሱን መካድ ኃጢአት ነው፡፡ እነሱን ማስተባበል/መካድ ማለት በመልዕክተኛው መካድ ነው፣ መልዕክተኛውን መካድ ደግሞ በአላህ መካድ ነው፡፡

ለኢማሞች እጅ መስጠት፣ ትዕዛዛቸውን መቀበልና መከተል እንዲሁም የሚሉትን ሁሉ መታዘዝ በሁሉም

ህዝብ ላይ ግዴታ ነው፡፡ ስለዚህ ሁሉንም ትዕዛዛት መረዳት ያለብን ከነሱ ንጹህ አስተምህሮዎች መሆን አለበት፡፡ የዲኑን (ኃይማኖቱን) መመሪያዎችና ትዕዛዛት አስመልክቶ ሌላን ሰው ዋቢ የሚያደርግና የሚከተል ሰው ዲኑን አስመልክቶ ካለበት ኃላፊነት ነፃ መሆን አይችልም፤ የሚያደርገውን ነገርም አስመልክቶ ኃላፊነቱን በትክክል ስለመወጣቱ እርግጠኛ መሆን አይችልም፡፡ እንደ መርከብ ኑህ በመርከቡ የተሳፈረ ሁሉ ለጥፋት አይዳረግም፡፡ ሳይሳፈር የቀረ ደግሞ በጥልቅ የጥርጣሬ ባህር ውስጥ እየዋዠቀ፣ እየተንቀዋለለ፣ ፈራ ተባ እያለ በችግር ውስጥ ህይወቱን ያሳልፍና መጨረሻው ጥፋትና ኪሳራ ይሆናል፡፡

እዚህ ቦታ ላይ ህጋዊ የነቢዩ ተተኪዎች (ኹለፋዎች) እንደነበሩና ከአላህ የተሰጠ ስልጣን እንደነበራቸው ማስረጃ ለማቅረብና ዝርዝር ጉዳዮች ውስጥ ለመግባት አንፈልግም፡፡ ምክንያቱም ይህ ቦታውና ወቅቱ አይደለም፤ ስለዚህ ጉዳይ ማንሳቱም ያለፈውን ዘመን ወደ ኋላ መመለስ አይችልም፣ ጉዳዩንም ለተገቢው ባለ መብቶቹ ሊመልስ አይችልም፡፡ እዚህ ላይ ለመጥቀስ

የተፈለገው መለኮታዊ ትዕዛዛቱን ለማግኘት እነሱን ለማንሳት ስለሚገደድና ነቢዩ በእርግጥ ያሉትን ነገር ለማወቅ ብቻ ነው፡፡

ከኢማሞቹ ዕውቀት ያልቀሰሙ ሰዎች ወይም ደግሞ አዕምሮአቸው በኢማሞቹ ያልተከፈተ/ያልበራ ሰዎች የሚከተሉት መንገድ ከትክክለኛው የኢስላም መንገድ ያፈነገጠ ነው፡፡ እንዲህ ዓይነቶቹ ሰዎች ደግሞ አላህ ያወረደውን ግዴታዎችና ኃላፊነቶችን መወጣትን በተመለከተ በራሳቸው ሊተማመኑ አይችሉም፡፡ የዲኑን (ኃይማኖቱን) ትዕዛዛትና መመሪያዎችን አስመልቶ በሙስሊም ቡድኖች መካከል የሐሳብ ልዩነት እስካለ ድረስና ለወደፊቱም ይስማማሉ የሚያስብል ተስፋ በሌለበት ሁኔታ እነዚህን ሰዎች ወይም ቡድኖች በጭፍኑ ልንከተላቸው አንችልም፡፡ እያንዳንዱን ቡድን (መዝሐብ) በመመርመር ከቡድኖቹ ውስጥ የትኛው አላህ ባዘዘው መልኩ የሚጓዝን የአንዱን ቡድን እውነታ በማስረጃ ማረጋገጥና ትክክለኛ የሆነውን በእርግጠኝነት እስክንደርስበት ድረስ ጥናት ማድረግ የግድ ይላል፡፡ ይኸውም አንድ ሰው የሆነ ኃላፊነትና ግዴታ ከተሰጠው

ስለግዴታውና ኃላፊነቱ በግልጽ ማስረጃ አብጠርጥሮ ማወቅ አለበት፡፡

በዚህ ረገድ ቁርጥ ያለ ማስረጃ የሚያመለክተው ወደ ነቢዩ ቤተ-ዘሮች (አህለል ቤይት) መመለስ እንደሚገባን ነው፡፡ ኢስላማዊ ህግጋትንና መመሪያዎችን አስመልክቶ ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ቀጥሎ ብቸኛ መርጅዕ ወደሆኑት ቤተ-ዘሮቹ መመለስ ግዴታ ነው፡፡ ነቢዩ በትክክለኛነቱ (ሰሂህነቱ) ግንባር ቀደም ቦታ በያዘው ታዋቂ ሐዲሳቸው የሚከተለውን በግልጽ አስቀምጠዋል፡-

«*በመካከላችሁ እጅግ ከባድና ውድ የሆኑ ሁለት ነገሮችን ትቼላችኋለሁ፡፡ እነሱም የአላህ ኪታብ (ቁርአን) እና ቤተ-ዘሮቼ ናቸው፡፡ እነዚህ ሁለቱን የሙጥኝ ካላችሁ ከኔ በኋላ በፍጹም ለጥመት አትዳረጉም፡፡ አንደኛው ከሌላኛው ይበልጣል፡፡ የአላህ ኪታብ ከሰማይ ወደ ምድር እንደተንጠለጠለ ገመድ ነው፡፡ ሌላኛው ቤተ-ዘሮቼ ናቸው፡፡ እነሆ እነዚህ ሁለቱ ጀነት ውስጥ በከውሰር ላይ እስከንገናኝ ድረስ ፍጹም አይለያዩም፡፡*»

ይህ ሐዲስ በሱኒም በሺዓ የሐዲስ ሊቃውንት በሰፊው የተዘገበ ድንቅ የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ኑዛዜና አደራ ነው፡፡ ይህንን ሐዲስ በአንክሮና በአስተውሎት ብታየው በመልዕክቱና በመጠቀ አባባሉ ትደማማለህ፡፡ ምክንያቱም በመጀመሪያ «*እነዚህ ሁለቱን የሙጥኝ ብላችሁ ከኔ በኋላ ፍጹም ለጥመት አትዳረጉም*» ይላል፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የተዉልን ሁለት ውድ ነገሮችን ነው፡፡ ሁለቱን አንድ ላይ እንደ አንድ ያያሉ፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ያሳሰቡት ግልጽ ጉዳይ ከሁለቱ ውድ ነገሮች አንዱን ብቻ ነጥለን እንድንይዝ ወይም እንድንከተል ሳይሆን፣ ከጥፋትና ከጥመት ለመዳን ሁለቱን የሙጥኝ እንድንልና እንድንከተል ነው፡፡ ምክንያቱን በቀጣዩ ሐረግ

«*እነዚህ ሁለቱ ጀነት ውስጥ በከውሰር ላይ እስክንገናኝ ድረስ በፍጹም አይለያዩም*» በማለት በግልጽ ያስቀምጣሉ፡፡ ስለዚህ አንድ ሰው አንዱን ብቻ ነጥሎ እከተላለሁ የሚል ከሆነ ወደ እውነተኛው መንገድ በፍጹም ሊመራ አይችልም ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ለሰው ልጆች የኑህ መርከብና ሰላም ናቸው፡፡ ወደነሱ የማይጠጋና በጥበቃቸው ስር የማይሆን ሰው በኃይለኛ ማዕበል ተናውጦ በጥልቅ ችግር ውስጥ ይሰጥማል፡፡

የዚህ ሐዲስ ትርጉም ወይም መልዕክት የነቢዩ ቤተ-ዘሮችን መከተልና መታዘዝ ሳያስፈልግ እንዲሁ ለነርሱ መስጠት የሚገባን ውዴታ አስፈላጊ መሆኑን ለመግለጽ ያህል ነው ብሎ ማሰብ እጅግ የተሳሳተ አተረጓጎም ነው፡፡ አላዋቂና እንዲሁ በደመ-ነፍስ የሚመራ ዋሾ ካልሆነ በስተቀር በዚህ መልኩ የሚተረጉም ጤነኛ ሰው ሊኖር አይችልም፡፡ ምክንያቱም ይህ ለአረብኛው ዐረፍተ ነገር ትክክለኛ ትርጓሜ በምንም መልኩ ሊሆን አይችልምና፡፡

## 27. ለነቢዩ ቤተ-ዘሮች(አህለል ቤይት) ውዴታን አስመልክቶ ያለን እምነት

አላህ እንዲህ ይላል፡-

قُلْ لَا أَسْأَلُكُمْ عَلَيْهِ أَجْرًا إِلَّا الْمَوَدَّةَ فِي الْقُرْبَىٰ وَمَنْ يَقْتَرِفْ حَسَنَةً نَزِدْ لَهُ فِيهَا حُسْنًا إِنَّ اللَّهَ غَفُورٌ شَكُورٌ

«***(ሙሐመድ ሆይ! ለሰው ልጆች) እንዲህ በላቸው፡- ለቅርቦቼ ውዴታ እንዲኖራችሁ እንጂ ለዚህ ምንም ዓይነት ምንዳ (አጅር) አልጠይቃችሁም፡፡***» (42፡23)

የነቢዩን ቤተ-ዘሮች ሙጥኝ ከማለትና ከመከተል ባሻገር እያንዳንዱ ሙስሊም ከዲኑ አንፃር ሊወዳቸውና ሊያከብራቸውና ይገባል፡፡ ምክንያቱም እላይ በተጠቀሰው የቁርአን አንቀጽ የሰው ልጆች ሊወዷቸው እንደሚገባቸው አላህ ተናግሯልና፡፡

ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሐዲሶችም የሚከተለው ይገኛል፡-
«*እነሱን (ቤተ-ዘሮቼን) መውደድ የኢማን ምልክት ነው፤ ለነሱ ጥላቻ ማሳየት ደግሞ የንፍቅና (ሙናፊቅነት) መገለጫ ነው፡፡ እነሱን የሚወድ አላህና መልዕክተኛውን የሚወድ ነው፡፡ ለነሱ ጥላቻ የሚያሳይ አላህና መልዕክተኛውን የሚጠላ ነው፡፡*»

የነቢዩን ቤተ-ዘሮች መውደድ እንዳለብን ግልጽ ነው፡፡ ይህ ምንም ከማያከራክሩና ከማያጠራጥሩ አስፈላጊ ኢስላማዊ ግዴታዎች አንዱ ነው፡፡ የነቢዩ ቤተ-ዘሮች

ጠላቶች በመሆን የሚታወቁና ነዋሲብ (በልባቸው ውስጥ በነቢዩ ቤተ-ዘሮች ጥላቻ ያደረባቸው) የሚል አስጠሊታ ስም ከተሰጣቸው ጥቂት ግለሰቦች በስተቀር ሁሉም የኢስላም ቡድኖች በዚህ ይስማማሉ፡፡

(ነዋሲብ የሚለው ቃል ለአንድ የተለየ ቡድን የተሰጠ ስያሜ ሳይሆን ለነቢዩ ቤተ-ዘሮች ክብር ለሌላቸውና ለሚሰድቧቸው ሰዎች በአጠቃላይ የተሰጠ ስም ነው፡፡)

ሰላት የመስገድ ግዴታንና ዘካ የመክፈል ግዴታ የመሳሰሉ ጥርጣሬ የሌለባቸውን ኢስላማዊ ትዕዛዛት የሚክድ ሰው፣ የኢስላማዊ እምነት ሁለቱን ሸሃዳዎች ማለትም (*አሽሐዱ አንላ ኢላሀ ኢለላህ ወአሽሐዱ አንነ ሙሐመደን ረሱሉላህ (ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፣ ሙሐመድ የአላህ መልዕክተኛ መሆኑንም እመሰራክለሁ*)) በአፉ ቢናገርም ነቢይነትን ከብዙ ሰዎች ጎራ እንደሚመደብ ያለ ጥርጥር መገንዘብ አለብን፡፡ ለነቢዩ ቤተ-ዘሮች ጥላቻ ማሳየት የከሃዲነት (ሙናፊቅነት) መገለጫ ነው፡፡ ስለዚህ የነሱ ጠላት የአላህና መልዕክተኛው ጠላት ነው፡፡

አላህ ኢማሞችን እንድንወድ ግዴታ ያደረገብን ምክንያት ለአላህ ያላቸው ቅርበትና ለትዕዛዛቱ በመታዘዝ ባላቸው ከፍተኛ ደረጃ፣ አላህ ጋር ባላቸው ከፍተኛ ደረጃ፣ ከሽርክና ከእኩይ ተግባራት ባላቸው የላቀ ንጽህና እንዲሁም ከአላህ ምህረትና ፀጋ ከሚያርቅ ከማንኛውም ነገር የራቁና የፀዱ በመሆናቸው፣ ፍቅርና ውዴታ የሚገባቸው ስለሆነ ነው፡፡

አላህ ወንጀል የሚሰሩትንና መታዘዝ ባለበት መልኩ የማይታዘዙትን ሰዎች እንድንወድ ግዴታ አድርጎ ያዘናል ብሎ ማሰብ የማይመስል ነገር ነው፡፡ አላህ ለማንም ሰው የተለየ ቅርበትና ወዳጅነት የለውም፡፡ ሁሉም የሰው ልጆች በእኩልነት የተፈጠሩ አገልጋዮች ናቸው፡፡ አላህ ዘንድ የበለጠ ክብር እንዲያገኙ የሚያደርጋቸው ተቅዋቸው (መልካም ስብዕናቸውና ለአላህ ያላቸው ፍራቻ) ነው፡፡ ስለዚህ አላህ እንድንወዳቸው የሚያዘን ሰዎች በተቅዋቸው ከሁሉም የላቁና በስብዕናቸው በላጮች መሆን አለባቸው፡፡ አለበለዚያ ውዴታው የሚገባው ሌላ ሰው መሆን አለበት፡፡ ወይም ደግሞ አላህ ያለ ምንም

ምክንያት እንዲሁ ለፈዝ አንዱን ሰውን ከሌላው አስበልጦ እንድንወድ እንድንታዘዝ ያዝናል ማለት ነው፡፡ አላህ እንዲህ ዓይነቱ የማይገባው ነገር የላቀና የጠራ ጌታ ነው!

## 28. ስለ ኢማሞች ያለን እምነት

አንዳንድ ቡድኖች እንደሚያደርጉት ስለ ኢማሞች አናጋንንም፡፡

كَبُرَتْ كَلِمَةً تَخْرُجُ مِنْ أَفْوَاهِهِمْ...

«ከአፉቸው የሚወጣው ቃል ምንኛ የገዘፈ ነው!...» (18፡5)

እንደኛው ዓይነት ሰዎች መሆናቸውን እናምናለን፣ መልካም ከሰሩ የሚሸለሙ፣ ከጠፉም የሚቀጡ ሰዎች እንደሆኑ እናምናለን፡፡ በእርግጥ የተከበሩ የአላህ ባሮች እንደሆኑና ታላቅ ክብርና ስልጣን እንዳጎናጸፉቸው እናምናለን፡፡ የመጠቀ ዕውቀት፣ መልካምነት፣ ጀግንነት፣ ለጋስነት፣ ጨዋነትና ማንኛውንም መልካም ስብዕናና ድንቅ ባህሪ የተለበሱ፣ ከፍተኛውን የፍጹምነት ደረጃ የተቸሩ ናቸውና፡፡ በስብዕና ረገድ የሚወዳደራቸው

የለም፡፡ ስለዚህ በኢስላማዊ መመሪያዎች (አህካም)፣ በፍርድ (ሁክም)፣ በህግጋት (ተሽሪዕ)፣ በቁርአን ትርጓሜ (ተፍሲር) እና ገለጻ (ተእዊል) እንዲሁም በማንኛውም ህዝቡ እርዳታ በሚፈልግባቸው ጉዳዮች በሙሉ ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) በኋላ ኢማሞች፣ መሪዎችና የስልጣን ባለቤቶች መሆን የሚገባቸው ናቸው፡፡ ኢማም ጃዕፈር አል-ሳዲቅ ሲናገሩ፡-

*«ስለኛ የተነገረ ማንኛውም ነገር ከሰው ልጆች አንዱ ማድረግ የሚችለው ነገር ከሆነ ባታውቁትም ባትረዱትም አታስተባብሉ፣ እውነት አድርጋችሁ ተቀበሉ፡፡ ስለኛ የተነገረው ማንኛውም ነገር ከሰው ልጆች አንዱ ሊያደርገው የማይቻል ነገር ከሆነ ደግሞ አስተባብሉ፣ እውነት አድርጋችሁ አትቀበለ»* ብለዋል፡፡

## 29. የመሪነት ስልጣን (ኢማማህ) ከአላህ መሆን አለበት

ልክ እንደነብይነት ስልጣን ኢማምነትም (ነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) የሚተኩ መሪዎች) በመልዕክተኛው በኩል ወይም ደግሞ በዚህ መልኩ በተመረጠ ቀደም ሲል በነበረ ኢማም

አማካይነት ከአላህ የሚመጣ ሹመት መሆኑን እናምናለን፡፡ ከዚህ አንፃር ነቢይነትና ኢማምነት ተመሳሳይ ናቸው፡፡

አላህ መሪና ገዢ አድርጎ የመረጣቸው ሰዎችን መቃወምና መጋፈጥ ትክክል አይደለም፡፡ ምክንያቱም የኢማምነት ሹመት ከሰዎች የሚሰጥ አይደለምና፡፡ ሰዎች በነቢይ ሹመትም ሆነ በኢማም ሹመት ላይ ቅንጣት ያህል መብት የላቸውም፡፡ የኢማምነትን ኃላፊነት መወጣት የሚችልን ሰውና ህዝቡን ወደ ቀናው መንገድ መምራት የሚችልን ሰው መምረጥና ዕውቅና መስጠት የሚችለው አላህ ብቻ ነው፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከሳቸው ቀጥሎ ህዝቡን የሚመራ ተተኪ (ኸሊፋህ) መርጠው በአዋጅ አስነግረው፣ በግልጽ አስቀምጠው ማለፋቸውንና ይኸውም የአጎቱ ልጅ የሆነው አሚረል ሙዕሚኒን ዓሊይ ኢብን አቢ ጧሊብ (ዐ.ሰ) መሆኑን እናምናለን፡፡ ይህንንም ሹመት በተለያየ ጊዜያትና አጋጣሚዎች ማሳወቃቸውንና ዓሊን ለዚሁ ጉዳይ ማዘጋጀታቸውን እናምናለን፡፡ ዓሊን የህዝቡ መሪና የወህይ ጠባቂ አድርገው መሾማቸውን እናምናለን፡፡ ኢማምነት በነቢዩ

(ሰ.ዐ.ወ) አማካይነት ከአላህ የሚሰጥ ሹመት ነውና፡፡ በዕለተ-ገዲር (ዙል-ሂጃ 18፣10ኛ ህጅራ) ለዓሊይ የመሪነት ስልጣን ቃል እንዲሰጡ (በይዓ እንዲያደርጉ) ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ህዝቡን አስገድደዋል፡፡ ህዝቡም በይዓ አድርጓል፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ለህዝቡ እንዲህ ነበር ያሉት፡-

«*አማኞች ሆይ! እኔ መሪው (መውላ) የሆንኩትና ስልጣኔን ለሚቀበል ሰው ሁሉ ይህ ዓሊም መሪው (መውላ) ነው፡፡ አላህ ሆይ! ለዓሊ ወዳጆች አንተም ወዳጅ ሁናቸው፡፡ እሱን ለሚረዱት አንተም ረዳታቸው ሁን፡፡ ከሱ ገሸሽ የሚሉትን አንተም ራቃቸው፡፡ እውነትን ምንጊዜም ከሱ (ዓሊ) ጋር ይሁን፡፡*»

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ኢ.ማምነትን ለመጀመሪያ ጊዜ ያወጁበት ቦታ የቅርብ ዘመዶቻቸውን ሰብስበው የሚከተለውን በተናገሩ ጊዜ ነበር፡-

«*እሱ (ዓሊ) ወንድሜ፣ ወራሼ (ዋሲ) እና ተተኪዬ (ኸሊፋህ) ነው፡፡ እሱን ልትሰሙትና ልትታዘዙት ይገባል፡፡*»

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ይህንን በተናገሩ ጊዜ ዓሊ ገና ልጅ ነበር፡፡ ይህንን ጉዳይ አስመልክቶ ነቢዩ በተደጋጋሚ ተናግረዋል፡-

«*ዓሊ ሆይ! አንተ ከኔ አንፃር ያለህ ቦታ ከኔ በኋላ ነቢይ አለመኖሩ በስተቀር ሐሩን ለሙሳ ያለው ቦታ ዓይነት ነው፡፡*»

ሌሎች በርካታ ሐዲሶችም ዓሊ የህዝቡ መሪ እንደሆነና የነቢዩ ተተኪ (ኸሊፋ) መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ በቁርአን አያትም ይህንኑን ማረጋገጥ ይቻላል፡-

إِنَّمَا وَلِيُّكُمُ اللَّهُ وَرَسُولُهُ وَالَّذِينَ آمَنُوا الَّذِينَ يُقِيمُونَ الصَّلَاةَ وَيُؤْتُونَ الزَّكَاةَ وَهُمْ رَاكِعُونَ

«***ወሊያችሁ አላህ፣ መልዕክተኛውና እነዛ ሰላትን ቀጥ አድርገው ያቆሙና ሩክዕ ውስጥ ሆነው ዘካን የሚሰጡ አማኞች ናቸው፡፡***» (5፡55)

የዚህ ቁርአን አያህ የመጨረሻው ክፍል ዓሊ ሰላት በሚሰግድበት ጊዜ በሩኩዕ ውስጥ እያለ ለአንድ ለማኝ የጣት ቀለበቱን መስጠቱን አስመልክቶ አላህ ያወረደው አንቀጽ ነው፡፡ በዚህ ዓይነቱ ትንሽና አጭር መጽሐፍ ውስጥ ይህንን የመሳሰሉ ሁሉንም ሐዲሶችና የቁርአን አንቀጾች መጥቀስ በእውነቱ የሚቻል ነገር አይደለም፡፡

ኢማም ዓሊ የሐሰንና ሁሴንና ኢማምነት በግልጽ አወጀ፡፡ ኢማም ሁሴን ደግሞ ልጁን ዓሊ ዘይነል ዓቢዲንን ኢማምነት አወጀ፡፡ በዚህ መልኩ እያንዳንዱ ኢማም ቀድሞ በነበረው ኢማም አማካይነት በኢማምነት ተመርጠዋል፡፡

## 30. የኢማሞችን ቁጥር (ብዛት) አስመልክቶ ያለን እምነት

ኢማሞች በቁጥር አስራ ሁለት እንደሆኑ እናምናለን፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እያንዳንዳቸውን በስም ጠርተው በግልጽ አሳውቀዋል፡፡ እያንዳንዱ ኢማም ደግሞ ተተኪውን ኢማም አሳውቋል፡፡ እነዚህም፡-

1. አቡል ሐሰን ዓሊ ኢብን አቢ ጣሊብ- አል-ሙርተዳ ከሂጅራ በፊት በ23 ዓመት (601 ዓ.ክ) ተወለደ፣ ከሂጅራ በኋላ በ40 (661 ዓ.ክ) ሞተ፡፡

2. አቡ ሙሐመድ ሐሰን ኢብን ዓሊ - ዘኪይ (2-50/623-670)

3. አቡ አብድላህ ሁሴይን ኢብን ዓሊ- ሰይድ አሽ-ሹሐዳእ (3-61/624-713)

4. አቡ ሙሐመድ ዓሊ ኢብን ሁሴይን- ዘይነል ዓቢዲን (38-95/658-713)

5. አቡ ጃዕፈር ሙሐመድ ኢብን ዓሊ- አል-ባቂር (57-114/678-732)

6. አቡ አብድላህ ጃዕፈር ኢብን ሙሐመድ- አስ-ሷዲቅ (83-148/702-765)

7. አቡ ኢብራሂም ሙሳ ኢብን ጃዕፈር- አል-ካዚም (128-183/745-799)

8. አቡል ሐሰን ዓሊ ኢብን ሙሳ- ሪዳ (148-203/765-818)

9. አቡ ጃዕፈር ሙሐመድ ኢብን ዓሊ- አል-ጀዋድ (195-220/810-835)

10. አቡል ሐሰን ዓሊ ኢብን ሙሐመድ- አል-ሓዲ (212-254/827-868)

11. አቡ ሙሐመድ ሐሰን ኢብን ዓሊ- አል-አስከሪ (232-260/846-870)

12. አቡል ቃሲም ሙሐመድ ኢብን ሐሰን- አል-መህዲ (256- /870- )

## 31. መህዲን አስመልክቶ ያለን እምነት

የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ልጅ የሆነችው ከፋጢማ የዘር ሐረግ የሆነው መህዲ በመጨረሻው ዘመን ደግሞ መገለጥን አስመልክቶ ብዙ ሰዎች ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) መስማታቸውን አውርተዋል፡፡ ዓለም በጭቆናና በበደል ከተሞላች በኋላ እኩልነትና ፍትህን በመላው ዓለም ላይ እንደሚያሰራጭ

ተነግሯል፡፡ ሁሉም የሙስሊም ቡድኖች ይህንን መልካም ዜና/ብስራት ተቀብለዋል፡፡ ነገር ግን የተለያየ ትርጓሜና ገለጻ ሰጥተውታል፡፡

አንዳንድ አጉል ፈላስፋዎች እንደሚሉት ከዓለማችን ኢ-ፍትሓዊነትን የሚያጠፋ አንድ ሰው እንዳለ በማለም በጭቆናና በበደል እንዲያምኑ የተደረጉ በሺዓዎች ውስጥ ብቻ የሚገኝ መጤ ሐሳብ እንደሆነ በጭፍንና በድንቁርና እንደሚናገሩት አይደለም፡፡ ከዚህ በተቃራኒ የመህዲ ዳግም መገለጥ ጉዳይ በሁሉም ሙስሊሞች ውስጥ በሚገባ የታወቀና ሁሉም የሚያምኑበት ጉዳይ ነው፡፡ ለዚህ ማረጋገጫ ቢያስፈልግ ከኢስላም ማንሰራራት በኋላ በመጀመሪያው ምዕተ-ዓመት አንዳንድ ሐሰተኞች እራሳቸውን መህዲ ነን እያሉ ለመቀጣጠፍ መሞከራቸውን መጥቀስ ይቻላል፡፡ እነዚህም የከይሳኒያህ፣ የአባሲያህና የዓላዊያህ መሪዎች ነበሩ፡፡

(ከይሳኒያዎች የከይሳን ተከታዮች ነበሩ፡፡ ከይሳን ደግሞ ነፃ የወጣ የዓሊ ኢብን አቢ ጧሊብ ባሪያ የነበረና የዓሊ ልጅ የነበረው የሙሐመድ ኢብን ሐነፊያ ተማሪ

እንደነበረ ይነገራል፡፡ ለሙሐመድ ኢብን ሐነፊያ የነበራቸውን ዕምነት እጅግ በማጋነን አጠቃላይ የሆነ ዕውቀት እንዳለው አድርገው ይቆጥሩት ነበር፡፡ ኃይማኖት ግልጽ የሚሆነውና መረዳት የሚቻለው የተለየ ዕውቀት ያለውን ሰው መከተል እንደሆነ የሚያትት እምነት በመያዝ ሙሐመድ ኢብን ሐነፊያ ሟች እንዳልሆነና መህዲ እንደነበረ ያምኑ ነበር፡፡ እነዚህም በሙክታሪያህ፣ ሐሺሚያህ፣ በያኒያህና ራዘሚያህ ቡድኖች ተከፋፍለው ነበር፡፡) ሰዎች በመህዲ በማመናቸው ብቻ እነዚህ ሰዎች ህዝቡን ሊያታልሉና እምነታቸውን ያለአግባብ በመጠቀም ስልጣን ላይ መውጣት ችለው ነበር፡፡ ስለዚህ በመህዲ ስም የተነሱበት ምክንያት የህዝቡን የልብ ትርታ ስለተረዱ በዚህ መልኩ ህዝቡን በማነቃቃትና በማሳመን ፍላጎታቸውን ለማራመድ ተጽእኖአቸውን ለማስፋፋት ነበር ማለት ነው፡፡

እኛ ሺዓዎች ግን በኢስላም ኃይማኖት እውነተኛና የመጨረሻው መለኮታዊ ኃይማኖት መሆኑን እንዲሁም ለሰው ልጆች ተሻድሶ ሌላ ኃይማኖት ይመጣል ተብሎ እንደማይጠበቅ እናምናለን፡፡ ግን በሌላው አንፃር ደግሞ

የሰው ልጅ በሚኖርባቸው የዓለማችን ክፍሎች በሙሉ ጭቆናና ሙስና በየቀኑ እየተንሰራፋ መምጣቱንና ፍትህና ዕድገት እየተሟጠጠ መሄዱን እናያለን፡፡ ሙስሊሞች በእያንዳንዱ ኢስላማዊ ሀገር ውስጥ እያንዳንዱን ኢስላማዊ ህግ ሲጥሱና ህግጋቱን ሲተላለፉ በገሃድ እያየንም ነው፡፡ ይህን በጭቆናና በሙስና ውስጥ የተዘፈቀውን ዓለም ለማደስ የኢስላም ከሙሉ ኃይሉ ጋር ዳግም መቋቋምን መጠበቅ እንዳለብን እናውቃለን፡፡

በእውነቱ ዛሬ እራሱን ሙስሊም ብሎ በሚጠራው ህዝብ መካከል ያለውን ሥፍር ቁጥር የሌለው የሐሳብ ልዩነት በምናይበት ወቅት፣ ከኢስላም ጋር የተቀላቀለውን (የተደባለቀውን) ስህተትና ብክለትን በማጣራት በመለኮታዊ መመራት የህዝቡን አንድነት የሚያንሰራራ ታላቅ መሪ ካልተገኘ በቀር የኢስላም የበላይነት ይመለሳል ማለት ዘበት ነው፡፡ ምድራችን በጭቆና፣ በበደልና በሙስና አረንቋ ውስጥ ከተዘፈቀች በኋላ ዳግም ፍትህን ለማምጣትና እኩልነትን ለማስፈን በእርግጥ እንዲህ ዓይነቱ መሪ ከፍተኛ ቦታና ደረጃ የተጎናጸፈ፣

አጠቃላይ ስልጣን ያለውና የመጠቀ ኃይል ያለው መሆን አለበት፡፡

በአጭሩ ሰብዓዊነት በሚያሳዝን ሁኔታ ውስጥ የመውደቁ ጉዳይ፣ በኢስላም እውነተኛነት የማመን እምነትና የመጨረሻው ኃይማኖት የመሆኑ አቋም፣ ለዓለም መዳን የእንዲህ ዓይነቱ መሪ(መህዲ) አስፈላጊነትን ይጠቁማል፡፡ ሁሉም የሙስሊም ቡድኖችና የሌሎች ኃይማኖቶች ህዝቦችም ይነሳል ተብሎ በሚጠበቅ መሪ ያምናሉ፡፡ ልዩነቱ በኢማሚያህ መዝሐብ እምነት መሠረት የሚገለጠው መሪ አንድ የተወሰነ ሰው ሲሆን እሱም መህዲ እንደሆነ፣ በ256 ሂጅራ (870 ዓ.ክ) የተወለደ፣ በአሁኑ ወቅት ህያው እንደሆነ፣ የኢማም ሐሰን አል-አስከሪ ልጅ እንደሆነና ስሙ ሙሐመድ እንደሆነ ነው፡፡ መወለዱንና ከዚያም መሰወሩን አስመልክቶ ከነቢዩና ከቤተ-ዘሮቹ በርካታ ሐዲሶች ደርሰውናል፡፡

ኢማም አላህ በፈለገ ጊዜ እስኪገለጥ ድረስ ከእይታ ተሰውሮ መቆየት ቢችልም ኢማምነት ሳይቋረጥ መቀጠል ያለበት ሥርዓት ነው፡፡ የመገለጡ ጊዜ ጉዳይ አላህ ለራሱ

ያደረገው መለኮታዊ ምስጢር ነው፡፡ ለዚህ ያህል ረዥም ዘመን የመኖሩ ጉዳይ አላህ የቸረው ተዓምር ሲሆን አባቱ ከዚህ ዓለም በተለዩበት ወቅት ገና የአምስት ዓመት ዕድሜ ያለው ልጅ ለሰው ልጆች መሪ ሆኖ ከመልላኩ ተዓምር የበለጠ ሆኖ የሚጋነን አይደለም፡፡

ነቢዩ ዒሳ (ዐ.ሰ) ገና በአንቀልባ ሆኖ ሰዎችን ማናገር ከመቻሉና ገና ጨቅላ ህጻን እያለ በነቢይነት ከመሾሙ የበለጠ ተዓምር ሆኖ ሊጠቀስ አይገባም፡፡ ምንም እንኳ እስከ አሁን ሳይንስ ህይወት እስከሚፈለገው ድረስ የማርዘም ወይም የመቆየት ደረጃ መድረስ ባይችልም ከፊዚዮሎጂካዊ አስተሳሰብ አንፃር ከተፈጥሮአዊ የህይወት ዘመን ወይም ከተለመደው የህይወት ገደብ በላይ መኖር የማይቻልበት ምክንያት የለም፡፡ የህክምና ሳይንስ (ሜዲስን) ይህን ማድረግ ቢሳነውም፣ ሁሉን አዋቂውና ሁሉን ቻዩ አላህ ማድረግ ይችላል፡፡ ቁርአን ነቢዩ ኑህ ረዥም ዘመን እንደኖሩና ነቢዩ ዒሳ ደግሞ እስከአሁን ህያው እንደሆኑ ይነግረናል፡፡ አንድ ሰው ኢስላምን ከተቀበለ ደግሞ ቁርአን ያስቀመጠውን ነገር ማስተባበል የለም፡፡ አንድ ሙስሊም በቁርአን አምናለሁ ብሎ ራሱን

እስከሰየመ ድረስ በነዚህ ነገሮች እውነታ ላይ ሙግት መፍጠር የማይታሰብ ነገር ነው፡፡

እዚህ ላይ ማስታወስ ያለብን ነገር ይህንን አዳኝና የለውጥ ምንጭ የሆነውን ኢማም መህዲን መጠበቅ ማለት ሙስሊሞች እጆቻቸውን አጣጥፈው ኃይማኖታቸውን ትተው መቀመጥ አለባቸው ማለት አይደለም፤ እንዲሁም ኃይማኖታዊ ግዴታቸውን መወጣት የለባቸውም ማለትም አይደለም፡፡ ነገር ግን መለኮታዊ ትዕዛዛቱን ለመተግበርና ወደ እውነት የሚያመራውን መንገድ ለማግኘት የተቻላቸውን ጥረት ሁሉ ማድረግ አለባቸው፡፡ ለኢስላም መታገል፣ ኢስላማዊ መመሪያዎችን መተግበር፣ ሌሎችን ሰዎች በመልካም ማዘዝና ከመጥፎ ተግባራት መከልከል የሁሉም ግዴታ ነው፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋልና፡- *«ሁላችሁም እረኞች ናችሁ፤ እያንዳንዳችሁም ለምትጠብቁት ነገር ተጠያቂዎች ናችሁ፡፡»*

ስለዚህ ማንኛውንም ሙስሊም መልካሙን ብስራት የሚያመጣውን መህዲን እየጠበቀ በመሆኑ ኃይማኖታዊ ግዴታውን መዘንጋትና መተው የለበትም፡፡ ይህንን ተስፋ

በመጠበቅ ምንም ኃላፊነትና ግዴታ እንደሌለንና መስራት የሚገባንን ነገር በመተውና በማቆየት/ በማስተላለፍ ዓላማ እንደሌለው እንስሳ መኖር እንደሌለብን መረዳት አለብን፡፡

## 32. ረጅዓህ (ሙታን ህይወት ዘርተው ወደ ሕያውነት መመለስን) አስመልክቶ ያለን እምነት

ይህንን ጥያቄ አስመልክቶ ሺዓዎች የነቢዩ ቤተ-ዘሮች (አህለል ቤይት) የሚሉትን ይከተላሉ፡፡ ይኸውም አላህ ሰዎች በምድር ላይ በነበሩ ጊዜ በነበራቸው መልክ እንደነበሩ አድርጎ ዳግም ወደዚህ ምድር እንደ-ሚመልሳቸውና ጻድቃንና ጥፋተኞችን እንዲሁም ጨቋኞችንና ተጨቋኞችን እንደሚለይና ይህም የሚከሰተው በመህዲ ዘመን መሆኑን ያምናሉ፡፡ አላህ ወደ ህይወት የሚመልሳቸው ሰዎች በጽድቅናቸው ከፍተኛውን ቦታ የተቆናጠጡ ወይም በጥልቅ ጥፋት ውስጥ የተዘፈቁ ሰዎችን ብቻ ነው፡፡ ከዚህ በኋላ ዳግም ይሞታሉ፣ በትንሳዔ ቀን ደግሞ ለፍርድ (ለሽልማት ወይም ለቅጣት) ዳግም ይቀሰቀሳሉ፡፡ ሁለት ጊዜ ወደዚህ ዓለም

የመጡትንና ንስሃ ለመግባት ለሦስተኛ ጊዜ ወደ ምድር ለመምጣት ስለሚመኙ ሰዎች አላህ በቁርአኑ ውስጥ ያወሳል፡-

قَالُوا رَبَّنَا أَمَتَّنَا اثْنَتَيْنِ وَأَحْيَيْتَنَا اثْنَتَيْنِ فَاعْتَرَفْنَا بِذُنُوبِنَا فَهَلْ إِلَىٰ خُرُوجٍ مِنْ سَبِيلٍ

«***ጌታችን ሆይ! ሁለት ጊዜ እንድንሞት አደረግከን፣ ሁለት ጊዜ ህይወት እደድንራዘም አደረግከን፤ እነሆ አሁን ከሐጢአታችን እንፀፀታለን፡፡ ታዲያ (ከእሳት) ወደ መውጣት መንገድ አለን?» ይላሉ፡፡***» (40፡11)

በእርግጥ ቁርአን ወደዚህ ዓለም በህይወት መመለስ (ረጅዓህ) እንዳለ ይናገራል፡፡ የእንከን-የለሾቹ ኢማሞች በርካታ ሐዲሶችም ይህንኑን ያረጋግጣሉ፡፡ የረጅዓን ጉዳይ በተለየ ሁኔታ የተረጎሙ ማለትም 'ረጅዓ'ን በመህዲ ዘመን የመንግስት ወይም የመሪነት ስልጣን ከማዘዝና መከልከል ሙሉ ኃይሉ ጋር ወደ ነቢዩ ቤተ-ዘሮች (አህለል ቤይት) ይመለሳል በሚል አስተሳሰብ እንጂ ሰዎች ዳግም ህይወት ዘርተው ወደ ምድር መመለስን

አያመለክትም በማለት ከተረጎሙት ጥቂቶች በስተቀር ሁሉም ኢማሞች በረጅዓ ያምናሉ፡፡

በረጅዓ ማመን በሱኒዎች እንደተረትና ከጥላቻ የመነጨ አጉል እምነት እንደሆነ ይቆጠራል፡፡ የሱኒ ሐዲስ ሰብሳቢዎችና አጠናቃሪዎች ረጅዓን በተመለከተ ሐዲስ የሚያስተላልፍ ሰው ተዓማኒነት እንዲያጠና መረጃውን ለማድከምና ዋጋ ለማሳጣት በእንዲህ ዓይነቶቹ ሰዎች ላይ ስማቸውን የሚያጠፉ አስነዋሪ ስያሜ የመለጠፍ ዘዴ እንደተጠቀሙ ይነገራል፡፡ በተጨማሪም በረጅዓ የሚያምን ሰው ወደ ኢ-አማንነት (ኩፍር) ደረጃ እንደወረደ ወይም አጋሪ (ሙሽሪክ) እንደሆነና ከዚህም የከፋ እንደሆነ የተፈረደበት ሰው ነው፡፡ ስለዚህ ይህ እምነት ሱኒዎች ሺዓዎችን ከሚንቁበትና ከሚዘልፉበት መንስኤዎች ዋነኛው ነበር፡፡

ያለጥርጥር ይህ አካሄድ አንዳንድ ኢስላማዊ ቡድኖች እርስ በርስ ለመወዳደምና ክፍፍልን ለማስፋፋት የሚጠቀሙት የመወነጃጀልና የማስፈራራት ዘዴ ነበር፡፡ በእርግጥ ወቀሳቸውን ለማረጋገጥና ለመደገፍ ምንም ማስረጃ የለም፡፡ ምክንያቱም በረጅዓ ማመን በተውሂድ

ወይም በኑቡወህ እምነት ላይ የሚያመጣው ወቀሳ የለም፡፡ ይልቁንስ የሁለቱንም ትክክለኛነት የሚያረጋግጥ ነው እንጂ፡፡ ምክንያቱም ረጅዓ ሰዎቹ ከሞቱ በኋላ ዳግም ህይወት እንዲዘሩ የማድረግ የአላህን ወደር-የለሽ ችሎታ የሚያረጋግጥና ለነቢዩና ቤተ-ዘሮቹ የተመሰከረ ከመለኮታዊ ኃይል የሆነ ተአምር እንደሆነ መጠቀስ የሚችል ጉዳይ ነው፡፡ በነቢዩ ዒሳ ከተደረገው ከሞት የማስነሳት ተዓምር ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ ልዩ የሚያደርገው ነገር ቢኖር የበሰበሱ የሙታን አካላትን ዳግም ህይወት እንዲዘሩ ማድረጉ ብቻ ነው፡፡

وَضَرَبَ لَنَا مَثَلًا وَنَسِيَ خَلْقَهُ قَالَ مَنْ يُحْيِي الْعِظَامَ وَهِيَ رَمِيمٌ. قُلْ يُحْيِيهَا الَّذِي أَنْشَأَهَا أَوَّلَ مَرَّةٍ وَهُوَ بِكُلِّ خَلْقٍ عَلِيم

«*ለእኛም ምሳሌን አደረገልን፡፡ መፈጠሩንም ረሳ፡፡ «አጥንቶችን እነርሱ የበሰበሱ ሲሆኑ ሕያው የሚያደርጋቸው ማነው?» አለ፡፡ «ያ በመጀመሪያ ጊዜ (ከኢምንት) ያስገኛት ሕያው ያደርጋታል፡፡ እርሱም በፍጡሩ ሁሉ (ሁኔታ) ዐዋቂ ነው» በለው፡፡*» (36፡78-79)

ረጅዓን እንደ ተናሱኽ (ነፍስ ከአንድ አካል ወጥታ ወደ ሌላ አካል የመተላለፍ ሥርዓት) አድርጎ የሚያስብ ሰው በተናሱኽና በ አል-መዓድ አል-ጂስማኒ (በአካላዊ ትንሳዔ) መካከል ያለውን ልዩነት በውል ያልተረዳ ሰው ነው፡፡ ምክንያቱም ተናሱኽ ማለት ነፍስ ከአንድ አካል ወጥታ ወደ ሌላ አካል መግባት ሲሆን አካላዊ ትንሳኤ ግን ከዚህ ይለያል፡፡ አካላዊ ትንሳዔ (አል-መዓድ አል-ጂስማኒ) ማለት ነፍስ ባህሪዋና ሁኔታዋ ሳይቀየር ወደ ነበረችበት አካል መመለስ ማለት ነው፡፡ ረጅዓ እንደተናሱኽ ቢሆን ኖሮ የነቢዩ ዒሳ ሙታንን ወደ ህይወት መመለስም ሆነ ትንሳኤ (መዓድ) ተናሱኽ ይሆን ነበር ማለት ነው፡፡

አሁን እንግዲህ ረጅዓን በተመለከተ ሁለት የመነጋገሪያ ነጥቦች ይቀሩናል፡-
አንደኛ ይህ ክስተት በፍጹም ሊሆን የማይችል ነገር ነው፣ ሁለተኛ ደግሞ ስለ ረጅዓ የሚያወሱ ሐዲሶች እውነት አይደሉም፡፡ እነዚህ ሁለት ነጥቦች መነጋገር ፋይዳ ያለው ነገር ከሆነ ልክ የሺዓ ጠላቶች እንደሚሉት ረጅዓ እንደ ቁምነገር መነሳት የማይገባው አጉል ነገር ነው፡፡ በሌሎች የኢስላም ቡድኖች ውስጥ ለመሆኑ ስንትና ስንት

በኃይማኖቱ ማጣቀሻዎች ውስጥ ጭራሽ የማይገኙ ጉዳዮች ወይም ደግሞ ምንም ማረጋገጫ የሌላቸው ጉዳዮች፣ ቡድኖች በመከፋፈልና ጭራሽ አንዱ አንዱን እስከማክፈርና (በኢ-አማኝነት እስከመወነጃጀል) ከኃይማኖቱ አድማስ ውጭ የተደራረጉበት ጉዳዮች የሉምን? በዚህ ብዙ ምሳሌዎችን ማንሳት ይቻላል፡-
ነቢዩ ለመርሳት ወይም ለአላህ ፈቃድ ላለመታዘዝ የተጋለጡ ናቸው የሚለው እምነት፣ ቁርአን ዘለዓለማዊ ነው ወይስ አይደለም የሚለው እምነት፣ ለአላህ በቅጣት ካስጠነቀቀ ለመቅጣት ይገደዳል የሚለው እምነት (አል-ወዒድ)፣ ነቢዩ የሚተካቸውን ኸሊፋ አልመረጡም የሚለው እምነትና የመሳሰሉት ተጠቃሾች ናቸው፡፡

የመነጋገሪያ ነጥቦቻችንን በተመለከተ፣ ረጅዓ ሊከሰት የማይቻል ነገር ስለሆነ መሰረት የለውም ለሚለው አስተሳሰብ፣ ረጅዓን ልዩ የሚያደርገው ወደዚች ምድር የመመለሱ ጉዳይ እንጂ ልክ እንደ መዓድ (አካላዊ ትንሳኤ) ነው እንላለን፡፡ ስለዚህ ለትንሳኤ ማረጋገጫነት የምንጠቀማቸውን ማስረጃዎች ለሪጅዓም እንጠቀማለን ነው፡፡ የተለየ ነገር መሆኑና በህይወታችን ያልገጠመን

ክስተት ከመሆኑ ባሻገር የተለየ አግራሞትን የሚፈጥር ነገር አይደለም፡፡ ነገር ግን ወደ መረዳት ወይም ወደ መቃወም የሚያቃርበን መንስኤም ሆነ የማይቻል ነገር ስለመሆኑ ማረጋገጫ አናውቅም፡፡ የሰው ልጅ አዕምሮ ያልተለመደን ነገር በቀላሉ መቀበል አለመቻሉ ብቻ ነው ጉዳዩ፡፡ ስለዚህ ትንሳዔን ለማስተባበል ከምናቀርበው ምክንያት ውጭ ሌላ ተጨማሪ ምክንያት የለም፡፡

قَالَ مَنْ يُحْيِي الْعِظَامَ وَهِيَ رَمِيمٌ

««...*አጥንቶችን እነርሱ የበሰበሱ ሲሆኑ ሕያው የሚያደርጋቸው ማነው?» አለ፡፡*» (36፡78)

قُلْ يُحْيِيهَا الَّذِي أَنْشَأَهَا أَوَّلَ مَرَّةٍ وَهُوَ بِكُلِّ خَلْقٍ عَلِيم

««*ያ በመጀመሪያ ጊዜ (ከኢምንት) ያስገኛት ሕያው ያደርጋታል፡፡ እርሱም በፍጡሩ ሁሉ (ሁኔታ) ዐዋቂ ነው» በለው፡፡*» (36፡79)

ረጅዓን ለማስተባበልም ሆነ ለማረጋገጥ አዕምሮአዊ ማስረጃ በሌለበት በዚህ ሁኔታ፣ ወይም ማስረጃ

እንደሌለው የሚያስበው አስተሳሰባችን ቢሆን እንኳ ከመለኮታዊ መገለጥ ምንጭ ወደሆኑት ወደ ኢስላማዊ ማስረጃዎች የመመለስ ግዴታ አለብን፡፡ ዒሳ ሙታንን ወደ ህይወት የመመለስ ተዓምር ማስረጃ እንዳለው ሁሉ አንዳንድ ሙታን ወደዚች ምድር የመመለስ (ረጅዓ) ተዓምር ማረጋገጫ በቁርአን ውስጥ አለና፡፡

وَأُبْرِئُ الْأَكْمَهَ وَالْأَبْرَصَ وَأُحْيِي الْمَوْتَىٰ بِإِذْنِ اللَّهِ

«***...በአላህም ፈቃድ ዕውር ሆኖ የተወለደን፣ ለምጸኛንም አድናለሁ፡፡ ሙታንንም አስነሳለሁ፡፡...***» (3፡49)

قَالَ أَنَّىٰ يُحْيِي هَٰذِهِ اللَّهُ بَعْدَ مَوْتِهَا فَأَمَاتَهُ اللَّهُ مِائَةَ عَامٍ ثُمَّ بَعَثَهُ

«***...«ይህችን (ከተማ) ከሞተች በኋላ አላህ እንዴት ሕያው ያደርጋታል?» አለ፡፡ አላህም ገደለው መቶ ዓመትን (አቆየውም)፡፡ ከዚያም አስነሳው፡፡...***» (2፡259)

ቀደም ሲል በተጠቀሰው የቁርአን አንቀጽ ውስጥም እንዲህ ይላሉ፡-

قَالُوا رَبَّنَا أَمَتَّنَا اثْنَتَيْنِ

«***ጌታችን ሆይ! ሁለት ጊዜ እንድንሞት አደረግከን፣...***» (40፡11)

በመሆኑም ምንም እንኳ አንዳንድ የቁርአን ትርጉም ሊቆች (ሙፈሲሮች) አጥጋቢ ያልሆኑና ትክክለኛውን ትርጉም የማያንፀባርቁ  የመሰላቸውን ፍቺ (ተእዊል) ቢሰጡም ከሞት በኋላ ወደዚህ ዓለም የመመለስ ጉዳይ ካልተሰጠ በቀር ይህ የቁርአን አያህ (አንቀጽ) ትርጉም አያገኝም፡፡

ሁለተኛውን የመነጋገሪያ ነጥብ በሚመለከት ማለትም ስለ ረጅዓ የሚያወሱ ሐዲሶች ትክክለኛ አይደሉም የሚለውን ሐሳብ ስናይ ምንም መሠረት እንደሌለው እናያለን፡፡ ምክንያቱም ረጅዓ አስፈላጊ ከሆኑ ጉዳዮች ውስጥ እንደሚካተት የነቢዩ ቤተ-ዘሮች (አህለል ቤይት) ማሳወቃቸውና በበርካታ ዘጋቢዎች የተተረከ ጉዳይ ስለመሆኑ በቂ ማስረጃ ማቅረብ ይቻላል፡፡

እራሱን ከአዋቂዎች ጎራ የሚመድበው ዕውቁ ፀሐፊ አህመድ አሚን «ፈጅረል ኢስላም» በተሰኘው መጽሐፉ ውስጥ፡፡ «*በረጅዓ እምነት የአይሁድ ኃይማኖት (ጁዳይዝም) በሺዓ እምነት ውስጥ ብቅ አለ*» ብሎ መጻፉ የሚያስገርም ነው፡፡ ለዚህ ሰው እንዲህ በማለት መልስ እንሰጠዋለን፡- «*የአይሁድ እምነት (ቀደም ሲል በተጠቀሱት የቁርአን አያዎች ውስጥ እንዳየነው) በረጅዓ እምነት በቁርአን ውስጥም ታየ፡፡*»

በተጨማሪም እንዲህ ብለን እንነግረዋለን፡- «*የአይሁድ ኃይማኖትም ሆነ የክርስትና ኃይማኖት ኢስላም ውስጥ ሊታዩ አይችሉም የሚያስብል መንገድ የለም፡፡ ምክንያቱም የተወሰኑ ህጎቻቸውን ቢሽሩም ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የመጡት በሰማያዊ ሸሪዓዎች ውስጥ የሚገኙትን ህግጋት ሊያረጋግጡ ነውና፡፡*» ስለዚህ ምንም እንኳ ፀሐፊው ረጅዓ የአይሁዶች እምነት እንደሆነ ቢያስቀምጥም፣ የአይሁድ ኃይማኖትና የክርስትና በኢስላም ውስጥ መገኘት ለኢስላም እፍረት እንዳልሆነ መገንዘብ አለበት፡፡

ያም ሆነ ይህ፣ ረጅዓ ከኢስላም መሠረታዊ እምነቶች ማለትም ማመኑ ግዴታ ከሆኑ መሠረታውያን አይደለም፡፡ ነገር ግን እምነታችን የሚመነጨው እንከን-የለሽ እንደሆኑ ከምናውቃቸው ከነቢዩ ቤተ-ዘሮች ከተገኙ የተረጋገጡ ሐዲሶች ነው፡፡ ከነገሩን የሩቅ ነገሮች (ገይቦች) አንዱ በመሆኑ ሊከሰት እንደማይችል የሚገልጽ አንድም ነገር የለም፡፡

## 33. ተቂያ (ለአደጋ የሚያጋልጥ ነገር ሲኖር ራስን ደብቆ የመኖር ጥበብን) በተመለከተ ያለን እምነት

ሰሂህ በሆነ ሐዲስ (ትክክለኛነቱ በተረጋገጠ ሐዲስ) ከኢማም ሳዲቅ በተተረከው መሠረት፡-

*«ተቂያ ኃይማኖቴ ነው፣ የቅድመ አያቶቼ ኃይማኖትም ነው፡፡ ተቂያ የሌለው ኃይማኖት የለውም፡፡»*

እራሳቸውንና ተከታዮቻቸውን ከጉዳትና ደም መፋሰስ ለመከላከል፣ የሙስሊሞችን ሕይወት ለማሻሻልና

ከነበሩበት ሁኔታ የባሰ እንዳይከተል ለመከላከል፣ በመካከላቸው ስምምነት እንዲኖርና ሰላምና መረጋጋት እንዳይጠፋ ለማድረግ ተቂያ የነቢዩ ቤተ-ዘሮች መፈክር ነበር፡፡

በአሁኑ ዘመንም ተቂያ ሺዓዎች የሚታወቁበትና ከሌሎች ህዝቦችና ቡድኖች የሚለያቸው ምልክት ነው፡፡ ማንኛውም ሰው ያመነበትን ነገር በገሃድ መስበክ ወይም እምነቱን በአደባባይ መተግበር በህይወቱና በንብረቱ ላይ አደጋ የሚያስከትል ከሆነ ተቂያን መጠቀም አለበት፡፡ ይህ ደግሞ ለማንኛውም ተፈጥሮአዊ አዕምሮ ላለው ሰው ምክንያታዊ የሆነ ነገር ነው፡፡ እንደሚታወቀው ሺዓዎችና ኢማሞቻቸው በታሪክ ብዙ ስቃይ እንደደረሰባቸው፣ መብታቸውን ተገፈው እንደኖሩና ማንም ሌላ ህዝብ ቡድን የእነሱን ያህል ስቃይ እንዳላሳለፈ ታሪክ ይነግረናል፡፡ በመሆኑም ኃይማኖታቸውና ህልውናቸው አደጋ ውስጥ እስከ ወደቀ ድረስ ሌላ እምነት ከሚያራምዱ ሰዎች ለመደበቅና ተግባሮቻቸውን በሚስጢር ለመፈጸም ተገደው ነበር፡፡ ከሌሎች ቡድኖች በተቂያህ የሚለዩበት ምክንያት ይኸው ነው፡፡

ተቂያ ግዴታ የሚሆንባቸውና የማይሆንባቸው ህግና ደንቦች አሉት፡፡ ይህ ደግሞ የህግ (ፊቅህ) ምሁራን በጻፉት መጽሐፍት ውስጥ ጉዳዩ በሚመለከታቸው ምዕራፎች ውስጥ በሰፊው ተጠቅሰዋል፡፡ በሁሉም ጊዜያትና ሁኔታዎች ግዴታ ሊሆን አይችልም፡፡ አንዳንድ ጊዜ እንደ አማራጭ ሆኖ ይቀርባል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ተቂያን ከመጠቀም መታቀብ ግዴታ የሚሆንበት ጊዜ አለ፡፡ ለምሳሌ እውነቱን በገሃድ ለህዝብ መናገር አስፈላጊ የሚሆንበት ጊዜ፣ ኢስላምን ለመከላከልና ከጥፋት ለማዳን ሲባል ወይም ለኢስላም ጉዳይ መዋጋት/መታገል ሲያስፈልግ ተቂያን መጠቀም የማይቻልባቸው ሁኔታዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በእንዲህ ዓይነት ሁኔታዎች ንብረት የግለሰብ ነፍሶች ዋጋ አይኖራቸውም፡፡

የአንድ ሰው ህይወት አደጋ ውስጥ በወደቀበት ጊዜ፣ ወይም ሐሰት በህዝብ ውስጥ እየተሰራጨ ባለበት ሁኔታ፣ ወይም ኢስላምን አደጋ ውስጥ የሚጥል ጉዳይ እየተከሰተ ባለበት ወቅት፣ ወይም ሙስሊሞች አስፈሪ ሁኔታ ውስጥ

በወደቁበት ሁኔታ ወይም በመካከላቸው ኢ-ፍትሓዊነት በተስፋፋበት ወቅትና እኩልነት በጠፋበት ወቅት ተቂያን መጠቀም የተከለከለ (ሐራም) ይሆናል፡፡ በሺዓዎች እይታ መሰረት አንዳንድ ጠላቶቻቸው እንደሚሉት የተቂያ ዓላማው ጥፋትና ውድመትን ለማራመድ የሚመሠረት ምስጢራዊ ድርጅት አይደለም፡፡ እንደዚህ የሚሉ ሰዎች ነገሮችን በእውነተኛው ብርሃን ውስጥ ማየት የማይችሉና የምንለውን ለመረዳት አንዳች ጥረት የማያደርጉ በራሳቸው ስሜት ውስጥ የሚዋኙ ናቸው፡፡ ጉዳዩ እነዛ ላለመኑት ሰዎች ኢስላምንና ህግጋቱን እንዳይረዱ ምስጢር አድርጎ የመደበቅ ሥራ አይደለም፡፡ በጭራሽ! በፊቅህ፣ በህግ (አህካም)፣ በስነ-መለኮታዊ ጥናቶች እንዲሁም በአቂዳቸው (እምነታቸው) ላይ የተጻፉ ከሌሎች ቡድኖች ሁሉ በላቀ ሁኔታ ተሰራጭተው የሚገኙ የሺዓ መጽሐፍት በመላው ዓለም ይገኛሉ፡፡ በተቂያ ማመናችን ሺዓን ለማንቋሸሽ በሚፈልጉ አካላት ለተደጋጋሚ በተደጋጋሚ ተኮንኗል፡፡ ከሺዓዎች ደካማ ጎን አንዱ ተደርጎም ተወስዷል፡፡ ሺዓዎችን ከምድር ገጽ ለማጥፋት «ሺዓ» መባል ብቻ ለሞት ያበቃበት በነበረ በዛ ክፉ ዘመን፣ የኡመያድና የአባሲድ እንዲሁም እስከ

ኦቶማኖች (ዑስማንዮች) ድረስ የዘለቁት በነቢዩ ቤተ-ዘሮች ጠላቶች ሰይፎች የተቀነጠሱት አንገቶች ፍላጎቶቻቸውን ለማሟላት የቻሉ አይመስልም፡፡ በዚህ አሰቃቂና ዘግናኝ ታሪክ እንኳን የረኩ አይመስሉም፡፡

ጠላቶቻችን በኢስላም ውስጥ ተቂያ ስለመኖሩ ማስረጃ የለም ለማለት የሚዳዱ ከሆነ ሐሳባቸውን ውድቅ ማድረግ እንችላለን፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ እኛ ኢማሞቻችንን እንከተላለን፣ በብርሃናቸውም እንመራለን፡፡ እነሱ ደግሞ አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ ሁሉ ተቂያን እንድንተገብር አዘውናል፡፡ ከኢማም ሳዲቅ አባባል ቀደም ሲል እንዳየነው ተቂያ በኢማሞቻችን እምነት መሠረት የኢስላም አካል ነው፡፡

«*ተቂያ የሌለው ሰው ኃይማኖት (ዲን) የለውም፡፡*»

በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ በቁርአን ውስጥ ትዕዛዝ ተስተላልፏል፡-

إِلَّا مَنْ أُكْرِهَ وَقَلْبُهُ مُطْمَئِنٌّ بِالْإِيمَانِ

« ***... ልቡ በእምነት የጸዳ ሆኖ የተገደደ ሰው ብቻ ሲቀር፡፡...***» (16፡106)

ይህ የቁርአን አያህ የተገለጠው አማር ኢብን ያሲር ከኢስላም ጠላቶች ለራሱን ለመከላከል ብሎ አማኝ እንዳልሆነ በመናገር ከለላ ያገኘበትን ሁኔታ በሚመለከት ነው፡፡

በተጨማሪም አላህ እንዲህ ይላል፡-

وَقَالَ رَجُلٌ مُؤْمِنٌ مِنْ آلِ فِرْعَوْنَ يَكْتُمُ إِيمَانَهُ

«***ከፈርዖንም ቤተሰቦች አንድ እምነቱን የሚደብቅ ምእመን ሰው አለ፡-…***» (40፡28)

# ክፍል አራት

# የነቢዩ ቤተ-ዘሮች አስተምህሮ ለተከታዮቻቸው (ለሺዓዎቻቸው)

## መግቢያ

የነቢዩ ቤተ-ዘር ኢማሞች በህይወት ዘመናቸው ስልጣናቸው እንደማይመለስላቸውና ሺዓዎች በሌሎች አገዛዝ ሥር እንደሚቆዩና ይህንን አገዛዝ ለመታገል ኃይልና አመጽን ለመጠቀም እንደሚገደዱ ያውቁ ነበር፡፡

በዚሁ ሁኔታ ደግሞ ተቂያ ደም መፋሰስን እስካላስከተለ ድረስና በኢስላምና በሌሎች ሰዎች ላይ ጉዳት እስካላመጣ ድረስ ኃይማኖታቸውንና የሚከተሉትን መንገድ መደበቅም አልተዋጠላቸውም ነበር፡፡ ስለዚህ በቤተ-ዘሩ ላይ የሚደርሰውን ሰቆቃና መከራ፣ የሚደርስባቸውን ችግርና እንግልት፣ የሚወሰድባቸውን የበቀል እርምጃና አሻጥር ሁሉ ተቋቁመው ለመቆየት ጥረት አደረጉ፡፡

በዚህ ምክንያት ኢማሞቹ አብዛኛውን ጊዜያቸውን የተጠቀሙት የኢስላማዊ ህግ መሰረታዊያን በተለየ ሁኔታ ተከታዮቻቸውን በማስተማርና ወደ ትክክለኛው ማህበራዊ ስብዕና በመምራት ተምሳሌት መሆን የሚችሉ ፍትሓዊ ሙስሊሞችን በማነጽ ተግባር ነበር፡፡

የነቢዩ ቤተ-ዘሮችን አስተምህሮ በተመለከተ በእንዲች ዓይነቷ ትንሽዬ መጽሐፍት ውስጥ ዘርዝሮ መጨረስ የማይሞከር ነገር ነው፡፡ የነሱን አስተምህሮና ኃይማኖታዊ ዕውቀት ምሳሌዎችን ለማወቅ የፈለገ ታዋቂ የሐዲስ መጽሐፍትን ማማከር ያስፈልጋል፡፡ ነገር ግን እዚህ ቦታ ላይ በእምነት ዙሪያ ያሉትን አንዳንድ አስተምህሮ-ቻቸውን መጥቀሱ ጥሩ ሐሳብ አይደለም ብዬ አላስብም፡፡ ይህ የሚያካትተው መልካም ማህበራዊ ስብዕና ለመላበስ የሚረዱና ተከታዮቻቸውን ወደ አላህ የበለጠ ለማቅረብ እንዲሁም ልቦቻቸውን ከቆሻሻ ነገሮች እንዴት ማጥራት እንዳለባቸውና በቅንነት የተሞሉ ይሁኑ ዘንድ የተሰጣቸውን የሞራል ወይም የሥነ- ምግባር አስተምህሮ-ዎቻቸውን ነው፡፡

ስለተቂያ ባነሳንበት ክፍል ስር በማህበራዊ ህይወት ውስጥ ስለሚያስፈልጉ መልካም ስብዕናዎች አንዳንዶቹን ጠቃቅሰናል፡፡ ቀጥሎ ባሉት ገጾች ውስጥ ተጨማሪ አስፈላጊ ጉዳዮችን እንጠቃቅሳለን፡፡

## 34. ዱዓን በተመለከተ ያለን እምነት

ነቢዩ እንዲህ ብለዋል፡-
*«ዱዓዕ (ፀሎት) የአማኞች ጦር፣ የዲን ምሰሶ የሰማይና የምድር ብርሃን ነው፡፡»*

ይሄ ነው እውነቱ፡፡ እናም ይህ ሺዓዎች ከሚታወቁበት ለየት ካሉ ነገሮች አንዱ ለመሆን በቃ፡፡ በዚህ ላይ ሺዓዎች በርካታ መጽሐፍትን ጽፈዋል፡፡ የዱዓን አስፈላጊነትና ጥቅም አስመልቶ ብዙ ድርሳናትን አበርክተዋል፡፡ ከነቢዩ ቤተ-ዘሮች የተላለፉልንን ዱዓዎች አስመልክቶ በመቶዎች የሚቆጠሩ ትላልቅና ትናንሽ መጽሐፍትን በማበርከት ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የዱዓን ትሩፋትና አስፈላጊነትን በመጥቀስ ህዝቡ እንዲገለገልበት ያሳሰቡትን አህለል ቤይት ያስተማሩንን ዱዓዎች ለአሁኑ

ትውልድ ለማድረስ የጀግና ሥራ ሠርተዋል፡፡ ከአህለል ቤይት በተላለፈልን መሰረት፡-

«*ከአምልኮ (ኢባዳ) ሁሉ በላጩ ዱዓዕ ነው፡፡*»
«*በዚች ምድር አላህ ዘንድ እጅግ ተወዳጅ የሆነ ተግባር ዱዓዕ ነው፡፡*»
«*ዱዓዕ በላእ (አደጋ/ችግር) እና ቀዷእ (ፍርደ-ውሳኔ) ይመልሳል፡፡*»
«*ዱዓዕ ለሁሉም በሽታዎች ፈውስ ነው፡፡*»

የመጀመሪያው ኢማም አሚረል ሙዕሚኒን ዓሊ (ዐ.ሰ) ለዱዓዕ ብዙ ትኩረት ይሰጡ ነበር፡፡ ይህም ግልጽ ነገር ነው፡፡ ምክንያቱም ዓሊ የተውሂደኞች መሪ (ሰይድ አል-ሙህዲን)፣ የአማኞች አለቃና (ኢማም አል-አሊሂዪን) ዱአዕና ቁጥባዎቹ የአረብኛ ቋንቋ ምጥቀት ተምሳሌት ባለቤትነትን የተቀዳጀ የሰው ቁንጮ በመሆኑ ነው፡፡ የኩመይል ኢብን ዚያድ አል-መሽሑር እንደምሳሌ ሊጠቀስ ይችላል፡፡ እነዚህ ዱዓዎችና ኹጥባዎች ፍጹም ወደ ሆነ የሙስሊም ህይወት የሚመሩ በቂ መለኮታዊና ኃይማኖታዊ ትምህርቶችን ያካተቱ ናቸው፡፡

በእርግጥም ከነቢዩና ከቤተ-ዘሮቹ የተላለፉ ዱዓዎች ለአንድ ሙስሊም አማራጭ የሌለው ወደ ትክክለኛው መንገድ የሚመራ መመሪያ ነው፡፡ ስለ ዱዓዎቹ ጠለቅ ብሎ ላሰበ ሰው የእምነት ጥንካሬን በውስጡ የሚጭሩ፣ በአላህ መንገድ ላይ መስዋዕት የመክፈል ስሜትን የሚያጎለብቱ፣ የአምልኮን ምስጢር የሚገልጹ፣ ወደ አላህ ዱዓእ የማድረግን ጥፍጥናን የሚያሳዩና ከአላህ ውጭ ያለው ነገር በሙሉ የማክሰም ችሎታን የሚያጎናጽፉ ሆኖ ያገኛቸዋል፡፡ የሰው ልጅ ኃይማኖቱን አስመልክቶ ማወቅ ያለበትን የሚያስተምሩና ወደ አላህ እንዴት መቃረብ እንደሚችልና ከሙስና፣ ከግል ስሜትና የሐሰት ፈጠራዎች እንዴት መራቅ እንዳለበት የሚያመላክቱ ጠንካራ መመሪያዎችን ያካተቱ ናቸው፡፡ በአጭሩ በነዚህ ዱዓዎች ውስጥ መልካም ስብዕናን (ሞራሊቲ)፣ የነፍስ ስልጠናና ኢስላማዊ እምነቶችን በተመለከተ ጠቅለል ባለ ሁኔታ የጠለቀ ትምህርት የተከማቸበት መሆኑን እንረዳለን፡፡ በሌላ አንፃር ደግሞ በስነ-መለኮት መስክ ላይ ጥናት ለማድረግና ሥነ-ምግባርን ለማጥናት የፍልስፍናዊ ሐሳቦች ዋነኛ ምንጭ ሆነው ሊያገለግሉ ይችላሉ፡፡

በነዚህ የመጠቀ ትርጉም ባላቸው ዱዓዎች ውስጥ ያሉትን መመሪያዎች የሰው ልጆች ከቶ ቢከተሉ- ዳሩ ምን ያደርጋል የሰው ልጅ ማድረግ አይችልም እንጂ- አሁን ምድርን ሞልቶ የምናየው ሙስናና በደል ዱካው አይታይም ነበር፡፡ በሐጢአት የተጠፈሩ ነፍሶችም ወደ ተቀደሰው ሰማይ በነፃነት በተጓዙ ነበር፡፡ ዳሩ ግን ለነዚህ የተሃድሶ ጀግኖችና የሰውን ልጅ ወደ ፍጹም እውነት ለሚጠሩ ወገኖች ትኩረት መስጠት ከቶ የማይቻል ነገር ሆነ፡፡ ይኸውም የአላህ ቃል ለሰው ልጆች ተገለጠ፡-

إِنَّ النَّفْسَ لَأَمَّارَةٌ بِالسُّوءِ

«*ነፍስ ሁሉ በመጥፎ ነገር በእርግጥ አዛዥ ናትና፡፡...*» (12፡53)

وَمَا أَكْثَرُ النَّاسِ وَلَوْ حَرَصْتَ بِمُؤْمِنِينَ

«*አብዛኛዎቹም ሰዎች (ለማመናቸው) ብትጓጓም የሚያምኑ አይደሉም፡፡*» (12፡103)

በሰው ልጅ ውስጥ የመጥፎነት ምንጭ ራስን ማታለልና ጥፋት የሚባል ነገር የለም እያሉ ጥፋታቸውን ባለማወቅ ጥፋት መልካም ነገር መስሎ እንዲታያቸው ማድረጋቸው

ነው፡፡ ስለዚህ የሰው ልጅ ሌሎችን ይጨቁናል፣ የሌሎችን ንብረት ይቀማል፣ ይዋሻል፣ ያታልላል፣ ለገዛ ስሜቱ ተገዥ እየሆነ ለስሜቱ ተገዥ እንዳልሆነ በማሰብ ራሱን ያታልላል፡፡ ኃጢአቱን አቅልሎ ለማየት ጥፋት መሆናቸውን ክዶ መደረግ ያለባቸው ነገሮች ናቸው እያለ በጥፋት ውስጥ ይዘቅጣል፡፡ ጥንካሬውን ከመለኮታዊ ራዕይ የተጎናጸፈው ቀጥሎ የተላለፈው ዱዓዕ የሰው ልጅ ከራሱ ተላቆ ከአላህ ጋር ብቻ እንዲሆን ይገፋፋዋል፡፡ በተጨማሪም ኃጢአቱን እንዴት መናዘዝ እንዳለበትና ጥፋተኝነቱንና መጥፎ ሠሪ መሆኑን ያስተምረዋል፤ ከአላህ ይቅርታን በመጠየቅና ንስሃ በመግባት ጊዜውን መሰዋት እንዳለበትና እራሱን ማታለሉን ለራሱ እንዲያስታውስና እንዲያጤን ያነቃቃዋል፡፡ ስለዚህ ዱዓእ አድራጊው በኩሜይል ኢብን ዚያድ ዱዓእ ወደ አላህ ይማጸናል፡፡

وَلَيْتَ شِعْرِى يَا سَيِّدِى وَإِلَهِى وَمَوْلاَىَ أَتُسَلِّطُ النَّارَ عَلَى وُجُوهٍ خَرَّتْ لِعَظَمَتِكَ سَاجِدَةً وَعَلَى أَلْسُنٍ نَطَقَتْ بِتَوْحِيدِكَ صَادِقَةً وَبِشُكْرِكَ مَادِحَةً وَعَلَى قُلُوبٍ اعْتَرَفَتْ بِإِلَهِيَّتِكَ مُحَقِّقَةً

وَعَلَى ضَمَائِرَ حَوَتْ مِنَ الْعِلْمِ بِكَ حَتَّى صَارَتْ خَاشِعَةً
وَعَلَى جَوَارِحَ سَعَتْ إِلَى أَوْطَانِ تَعَبُّدِكَ طَائِعَةً وَ أَشَارَتْ
بِاسْتِغْفَارِكَ مُذْعِنَةً مَا هَكَذَا الظَّنُّ بِكَ وَلاَ أُخْبِرْنَا بِفَضْلِكَ

*አምላኬ ሆይ፣ ጌታዬ ሆይ! ለታላቅነትህ በፊትህ በአምልኮ በሚደፉ ፊቶች ላይ ወይም ስለ አንድነትህ የሚያወሱና በምስጋናና በውዳሴ በሚያመሰግኑህ ምላሶች ላይ፣ ወይም ደግሞ መለኮታዊነትህን በእርግጠኝነት በሚመሰክሩ ልቦች ላይ፣ ወይም የበታችነትና መተናነስ እስኪጎናጸፉ ድረስ አንተን የመረዳት ዕውቀት የተቸሩ አዕምሮዎች ላይ፣ ወይም ደግሞ ጸጸታቸውን ለማሳየት (ንስሃ ለመግባት) በፈቃድህ እጅ በመስጠት በፈቃደኝነት ሊያመልኩህ ረዥም ጉዞ በተጓዙ እግሮችና እጆች ላይ እንዴት እሳት እንደምታነግስ ከቶ ባወቅኩ ኖሮ! እንዲህ ታደርገናለህ ብለን ፍጹም አናስብም፡፡ የምህረትንና የቸርነትህን ጥልቀት አስመልክቶ የተነገረን ይህ አይደለምና፡፡*

እስቲ ይህንን ምንባብ ደጋግመህ ቅራው (አንብብ)! የማሳመን ኃይሉን፣ የቋንቋውን ምጥቀትና ጥፍጥና፣ መስህቡንና ፍሰቱን አስተውል፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ

በአንድ መልኩ ነፍስ ያለባትን ጉድለት እንድትናዘዝና የአምልኮ አገልግሎቷን እንድታወሳ ሲያደርግ በሌላ መልኩ ደግሞ ከአላህ ምህረትና ቸርነት ተስፋ እንዳትቆርጥ ያዛታል፡፡ ከዚያም በረቀቀና በሰከነ ሁኔታ ነፍስን እያናገራት በነዚህ በተቀደሱ ተግባራት ያዛታል፡፡ እነዚህን ተግባራት የመፈጸም ግዴታ እንዳለባት ለስለስ አድርጎ ያሳስባታል፡፡ የሰው ልጅ እንዚህን ተግባራት በመፈጸም የአላህን ምህረት እንዴት ማግኘት እንደሚችል ያስተምራታል፡፡ ይህ ደግሞ ቀደም ሲል ከኃላፊነቱ ተዘናግቶ የነበረው ሰው ልቡን በማዳመጥና በመስማት መፈጸም ያለበትን ግዴታውን መወጣት እንዳለበት የሚያደርግ ነው፡፡ ከዚያ ደግሞ ከተመሳሳይ የዱዓዕ መድበል በተለየ ዘይቤ እንዲህ ይቀጥላል፡-

فَهَبْنِى يَا إِلَهِى وَسَيِّدِى وَمَوْلاَىَ وَرَبِّى صَبَرْتُ عَلَى عَذَابِكَ
فَكَيْفَ أَصْبِرُ عَلَى فِرَاقِكَ وَهَبْنِى (يَاإِلَهِى) صَبَرْتُ عَلَى حَرِّ نَارِكَ
فَكَيْفَ أَصْبِرُ عَنِ النَّظَرِ إِلَى كَرَامَتِكَ

*አቤት በለኝ፣ አምላኬ፣ ጌታዬና ፈጣሪዬ ሆይ! ቅጣትህንስ እችለው ይሆናል፤ ግን ከአንተ መለየትን እንዴት አድርጌ እችላለሁ?*

*ጌታዬ ሆይ መልስልኝ! የገሃነምን ቃጠሎ እችለው ይሆናል፤ ግን ወደ ቸርነትህና ግርማህ ላለመመልከት እንዴት አድርጌ እታገሳለሁ?*

ይህ ወደ አላህ በመቃረብና ቸርነቱንና ኃያልነቱን በማጤን ደስታና ብልጽግና የመፈለግ አስፈላጊነትን አስመልክቶ ለነፍስ የተሰጠ ትዕዛዝና መመሪያ ነው፡፡ በአላህ ዘንድ ያለውን ነገር በመሻትና በመመኘት ለሱ ያለንን ፍቅር ለማጎልበት ለነፍስ የሚሰጥ ስልጠና ነው፡፡ ወደ አላህ በመቃረብ የሚገኘው ሀሴት አንጻር ከሱ መራቅና ብቸኛ መሆን ከገሃነም እሳት ቃጠሎ የከፋ ቅጣት እስከ መሆን ደረጃ ይደርሳል፡፡ ይህ ማለት የሰው ልጅ የገሃነም እሳትን መቋቋም ይችል ይሆናል፣ ነገር ግን የመትተውና የመገለል ስቃይን መታገስ አይችልም እንደ ማለት ነው፡፡ እነዚህ የዱዓእ መድብሎች የሚያሳውቁትን ነገር ወደ አላህ በመቃረብ የሚገኘው ደስታና ፍቅር ጥፋተኛ ለሆነ ሰው አላህ ይቅር ይለው ዘንድ እጅግ

ምርጥ የሆነ የምልጃ ተግባር ነው ማለት ነው፡፡ እንዲህ ዓይነቱ የጠለቀ መተናነስና ለስላሳነት፣ መሃሪና አዛኝ፣ ተውባ ተቀባይና ሁሉን ቻይ ከሆነው ጌታ ምህረትንና ውዴታን እንደሚቀዳጅ አይጠረጠርም፡፡

ይህንን ርዕስ የመጠቁ ድንቅ ስብዕናዎችን በሚዘረዝርና እያንዳንዱ የሰው ልጅ ክፍልና ቡድን ሊቋደሰው በሚገባው አጭር ዱዓእ መጠቃለል ክፋት የለውም ብለን እናስባለን፡፡

"اللهم ارزقنا توفيق الطاعة وبعد المعصية ، وصدق النية وعرفان الحرمة وأكرمنا بالهدى والاستقامة ، وسدد ألسنتنا بالصواب والحكمة واملأ قلوبنا بالعلم والمعرفة ، وطهر بطوننا من الحرام والشبهة ، واكفف أيدينا عن الظلم والسرقة، واغضض أبصارنا عن الفجور والخيانة ، واسدد أسماعنا عن اللغو والغيبة "

" وتفضل على علمائنا بالزهد والنصيحة، وعلى المتعلمين بالجهد والرغبة، وعلى المستمعين بالإتباع والموعظة ".

" وعلى مرضى المسلمين بالشفاء والراحة، وعلى موتانا بالرأفة والرحمة ".

" وعلى مشايخنا بالوقار والسكينة ، وعلى الشباب بالإنابة والتوبة، وعلى النساء بالحياء والعفة ، وعلى الأغنياء بالتواضع والسعة ، وعلى الفقراء بالصبر والقناعة".

( وعلى الغزاة بالنصر والغلبة ، وعلى الاسراء بالخلاص والراحة ، وعلى الأمراء بالعدل والشفقة ، وعلى الرعية بالإنصاف وحسن السيرة )

( وبارك للحجاج والزوار في الزاد والنفقة، واقض ما أوجبت عليهم من الحج والعمرة ).

( بفضلك ورحمتك يا أرحم الراحمين ).

*«ጌታዬ ሆይ! አንተን በመታዘዝ የምንፀና አድርገን፣ ከሐጢአት የመራቅ ፀጋን አላብሰን፡፡*

*አስተሳሰባችንን ቀና ልቦናና እውነተኝነትን የተላበሰ አድርግልን፣ የተቀደሱና ምስጢራዊ የሆኑ ነገሮችን ለማወቅ የሚረዳን ዕውቀት ለግሰን፡፡*

*ቅኑን መንገድ የመመራት በጽናት የመዝለቅ ፀጋን አላብሰን፣*

*አንደበቶቻችንን በቁም ነገር፣ በምክንያትና ጥበብ አትምልን፣*

*ልቦቻችንን በትምህርትና በዕውቀት ሙላልን፣*

*ሆዳችንንና ውስጣችንን እርም ከሆኑ ነገሮችና እርግጠኛ ካልሆንነባቸው ነገሮች የጸዱ አድርግልን*

*እጆቻችንን ከጭቆናና ከስርቆት ጠብቅልን፣*

*ወንጀል፣ ማጭበርበር፣ ተንኮልና ክህደትን ከዓይኖቻችን ሰውርልን፣*

*ሐሜትና የማይረባ ንግግርን ከጆሮዎቻችን አርቅልን፣*

*ለአዋቂዎቻችን ቅንጦት ከመፈለግ ነፃነትንና የመምከር ጥበብን፣ ለዕውቀት ፈላጊዎች (ተማሪዎች) የመማር ፍላጎትና የመተግበር ችሎታንና ለታዳሚዎቻቸው የመታዘዝና በሰሙት ነገር ተጠቃሚነትን ለግስልን፣*

*በታመሙት ሙስሊሞች ላይ ፈውስና ምቾትን፣ በሙታን ላይ እዝነትህንና ምህረትህን አውርድልን፡፡*

*የዕድሜ ባለፀጋዎችን ላይ ክብርና መረጋጋትን አውርድልን፣*
*ወጣቶቻችንን እውነትን ለመቀበልና ለንስሃ ልቦቻቸውን ክፍት አድርግልን፣*
*ሴቶቻችንን ጨዋነትና ሀያእ አጎናጽፍልን፣*
*ሀብታሞቻችንን በመተናነስና ልግስና ሙላልን፣*
*በደኃዎቻችን ላይ ትዕግሥትና መብቃቃትን አውርድልን፣*
*ለታጋዮችና ዘማቾች የበላይነትና ድልን አጎናጽፍልን፣*

*ለእስረኞች ነፃነትና ሰላምን፣*
*ለገዢዎች ፍትህና ርህራሄን፣*
*ለህዝቡ ሚዛናዊነትንና መልካም ፀባይን ለግስልን፣*

*ለሀጅ አድራጊዎችና ጎብኚዎች ስንቅና ምጽዋታቸውን ባርክላቸው፣*
*ባላቸው ፀጋና ንብረት ለጋስ ይሁኑ ዘንድ እርዳቸው*
*የታዘዙትን የሐጅና ዑምራ ተግባር እንዲወጡ አድርጋቸው፣*
*በወደር የለሽ እዝነትህና ምህረትህ፣*
*እጅግ ርህሩህና እጅግ አዛኝ የሆንከው ጌታችን ሆይ!»*

ይህንን ዱዓእ እንድትቀሩና እንድትጠቀሙ ለአንባቢዎች -ለወንድሞቼ አደራ እላለሁ፡፡ ይህንን ዱዓእ ትርጉሙን በጥሞና በማሰብ፣ ዓላማዎቹን በመረዳት በሙሉ ልብና በሰከነ አዕምሮ በመተናነስ ወደ አላህ ለመቃረብ የመጠቀም ዕድሉ እንዳያመልጣችሁ እመክራችኋለሁ፡፡ በዱዓዎቹ ውስጥ የተጠቀሱት አባባሎችና ቃላት አንተ ራስህን እንደሚያናግሩህ በማሰብ የነቢዩ ቤተ-ዘሮች ባስቀመጡት ሥርዓት መሠረት ከልብህ በጥሞና ከአላህ ጋር ተነጋገር፡፡ ትርጉማቸውን ጠለቅ ብለን ሳናስብና ዓላማቸው ሳይገባን ምንም ትኩረት ሳንሰጥ እንዲሁ አፋችንን ሞልተን ማነብነብ ወይም ማንበብ ምንም ዕውቀት አይጨምርልንም፣ ወደ አላህ በዚህ መልኩ መቃረብም አንችልም፡፡ በእንዲህ ዓይነት አኳኋን የምናደርገው ዱዓእ ችግራችንን አይቀርፍልንም፣ አላህ ዘንድ ተቀባይነትም አይኖረውም፡፡

አላህ ዱዓን ከጨለመ ልብ አይቀበልም፡፡ ስለዚህ ዱዓእ በምታደርግበት ጊዜ ልብህን አቅርብ፣ ዱዓዬ ተቀባይነት አይኖረውም ብለህ አትጠራጠር፡፡

## 35. ከአል-ሰሒፈህ አል-ሰጃዲያህ ዱዓዎች የሚገኙ ዋና ዋና መልዕክቶች

ከአሳዛኙ የከርበላ ክስተት በኋላና ኡመያዎች የኢስላማዊ ማህበረሰቡን አመራር ከሰወዱ በኋላ፣ ከመጠን ያለፈ ጭቆና መፈጸምና ደም መፍሰስን በሰፊው ገቡበት፡፡ በኢስላማዊ አስተምህሮዎች ላይ ማፌዝ ጀመሩ፡፡ በአጠቃላይ ኃይማኖቱን ማጥፋትና ሥርዓት አልባ የሆነ ኑሮ መግፋትን አጀንዳቸው አደረጉ፡፡ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ኢማም ዘይነል ዓቢዲን - ሰይድ አስ-ሳጂዲን በቤታቸው ውስጥ በብቸኝነት ከመኖር ውጭ ሌላ አማራጭ አልነበራቸውም፡፡ በሐዘንና በቁጭት ተውጠውና ተገልለው የድብቅ ኑሮ ከመኖር ውጭ የተሻለ አማራጭ አልነበረም፡፡ ወደ ቤታቸው በመሔድ ሊያገኛቸው የደፈረ ሰው አልነበረም፡፡ህዝቡን በተፈለገው ሁኔታ እንዳይመሩ ተከልክለው ነበር፡፡

የዱዓን መንገድና ዘዴ ለመከተል ተገደው ነበር (ቀደም ሲል እንደተገለጸው መልካም ስብዕና ለማጎልበትና የጠራ ባህሪን ለማልማት ከሚጠቅሙ ዘዴዎች አንዱ ነው)፡፡ የቁርአንን አስተምህሮዎች ለማሰራጨት፣ የኢስላም

መመሪያዎችን ለማስተማርና ለማሳወቅ፣ የነቢዩ ቤተ-ዘሮችን መልዕክት ለማድረስ፣ በህዝቡ አዕምሮና ልብ ውስጥ መንፈሳዊነትንና ጽድቅን ለመቅረጽ፣ ውስጣዊ ጥራትን (የነፍስ ንጽህናን) እና ሥነ-ምግባርን የማበልጸግ አስፈላጊነትን ለማስረጽ ከሚረዱ ዘዴዎችና መንገዶች አንዱ በዱዓዎች መልክ የሚሰጥ ትምህርት ነው፡፡ ይህ አካሄድ የአምባገነን መሪዎቹን ጥርጣሬ ሳይነካኩና ለክስና ወቀሳ የሚያበቃቸውን መረጃ አሳልፈው ሳይሰጡ ሐቅን ለማስተማርና ለማሰራጨት የተጠቀሙበት ዘዴ ነበር፡፡ ለዚህም ነው አንዳንድ በሰሒፋህ አል-ሰጃዲያህ ውስጥ የተሰበሰቡት በቋንቋ የመጠቁና መልዕክታቸው የገዘፉ የዱዓእ መድብሎች ዘቡር አሊ ሙሐመድ (የነቢዩ ቤተ-ዘሮች መዝሙረ-ዳውድ) ተብለው የሚጠሩት፡፡ በዚህ መድብል ውስጥ የኢስላማዊ አስተምህሮ በርካታ ርዕሰ-ጉዳዮች ተካተው እናያለን፡፡ ሥነ-ጽሑፋዊ ዘይቤውና መልዕክቱ በአረብኛ ቋንቋ ሥነ-ጽሁፍ ውስጥ ከሚጠቀሱ ታላላቅ ምሳሌዎች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ዱዓዎቹ የእውነተኛው ኃይማኖት አስተምህሮዎችን አምቀው የያዙ ናቸው፡፡ የተውሂድና ኑቡወህ (በአምላክ አሀዳዊነት የማመን እምነትነና የነቢይነት ሥርዓት) ጥልቅ ንዑስ

ርዕሶችን ያካተቱ ናቸው፡፡ የነቢዩ ሙሐመድን ሥነ-ምግባርና ኢስላማዊ ሞራሊቲን ለማስፋፋት እጅግ ምርጥ የሆነ መንገድ ነው፡፡ ስለዚህ በዱዓእ መልክ የቀረቡ መንፈሳዊና ሥነ-ምግባራዊ አስተምህሮዎች ናቸው ማለት ነው፡፡ ወይም ደግሞ መንፈሳዊ አስተምህሮዎችንና ሥነ-ምግባርን ያማከለ ዱዓዎች ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ ያለ ምንም ጥርጥር ከቁርአንና ነህጀል በላጋህ ቀጥሎ በአረብኛ ሥነ-ጽሑፍ ውስጥ ታላቅ ምሳሌና በፍልስፍናዊና ሥነ-መለኮታዊ ጉዳዮችና ሥነ-ምግባር ትንተናና ውይይት ውስጥ በቀዳሚነት ሊነሳ የሚችል ድንቅ ቅርስ ነው፡፡

እንግዲህ ከዚህ አላህን እንዴት ማወደስ እንዳለብን፣ ለክብሩ እንዴት እንደምንዘምር፣ እንዴት እንደምናመሰግነውና በንስሃ ወደሱ እንዴት እንደምንመለስ እንረዳለን፡፡ በዚህ መንገድ ነው እንዴት ከአላህ ጋር ወደጅነት ፈጥረን የውስጥ ምስጢራችንን በግል ልንገልጽ እንደምንችል የምንረዳውና በሱ ላይ ብቻ የመመካት ጥበብን የምንቀስመው፡፡ በዚህ መንገድ ነው በአላህ ነቢይ ላይ፣ በመልዕክተኞቹና ከፍጡራኑ በመረጣቸው ላይ ሰለዋት የማውረድ ትርጉሙ ምን

እንደሆነና እንዴትስ ተደርጎ መደረግ እንዳለበት የምንረዳው፡፡ ለወላጆች እንዴት በጎ መዋል እንዳለብን፣ አባት ለልጅ ያለው ግዴታና ኃላፊነት፣ ልጅ ለአባት ያለው ግዴታና ኃላፊነት፣ ዘመዶችና ጎረቤቶችን አስመልክቶ ያለብንን ግዴታና ኃላፊነት፣ የመላው ሙስሊም አጠቃላይ ግዴታና ኃላፊነት፣ ደኃው የህብረተሰብ ክፍል ስለ ሀብታሙ ክፍል ያለበት ግዴታና ኃላፊነትና ሀብታሙ ስለደኃው ያለው ግዴታና ኃላፊነት ወዘተ… እንማርበታለን፡፡

ያለብንን ዕዳ መክፈል እንዳለብን ያስጠነቅቀናል፡፡ ንግድና ግብይት ውስጥ እንዴት መሆን እንዳለብን ይመክረናል፡፡ ከዘመዶቻችን ጋር፣ ከጓደኞቻችንና ከሁሉም ሰዎች ጋር ፍላጎታቸውንና ስሜታቸውን ጠብቀን የመተባበር ስሜት እንዴት መፍጠር እንዳለብንና መረዳዳት እንደሚገባን ያስተምረናል፡፡ በዚህ መልኩ የሰው ልጆች መልካም ባህሪያት ሁሉ ይፋ ይወጣሉ፣ ይተገበራሉ፡፡ እነዚህ የዱዓእ መድብሎች የስነ-ምግባር ሳይንስ አጠቃላይ መመሪያዎችን አጭቀው የያዙ ናቸው፡፡

እነዚህን ዱዓዎች በመቅራት በችግር በመከራ ጊዜ እንዴት በትዕግስት መወጣት እንዳለብንና በሽታንም ሆነ ጤንነትን እንዴት መቀበልና ማስተናገድ እንደሚገባን እንረዳለን፡፡ የኢስላማዊ ጭፍራዎችና ወታደሮቻቸውን ግዴታዎች፣ ህዝቡ ስለ ወታደሮቹ ያለበት ኃላፊነት፣ ግዴታና ሌሎች የኢስላም መሠረታዊያንና የወረዳውን ሸሪዓ መሠረት ያደረጉ በርካታ ጉዳዮችን ይዳስሳል፣ ያብራራል፡፡ ይህ ሁሉ የተደረገው በዱዓእ (በፀሎት) መልክ ነው፡፡

ቀጥሎ ያሉት ዋና ዋና መልዕክቶች በሰሒፋህ አል-ሰጃዲያህ ውስጥ የሚዘወተሩና በተደጋጋሚ የተገለጹ ናቸው፡-

i. ስለ አላህ ታላቅነት፣ ኃያልነት፣ አንድነትና ዘለዓለማዊነት በሚመጥኑ፣ በምጥንና በሳል ቃላትና አባባሎች መግለጽና ማወደስ፡- ይህ መልዕክት በሁሉም ዱዓዎች ውስጥ በተለያዩ ዘይቤዎችና የአገላለጽ መንገዶች ተጠቅሶ ይገኛል፡፡ ለምሳሌ

**በመጀመሪያ ዱዓእ ውስጥ የሚከተለውን ምንባብ እናገኛለን፡፡**

أَلْحَمْدُ للهِ الاوَّلِ بِلا أَوَّل كَانَ قَبْلَهُ، وَ الاخِر بِلاَ آخِر يَكُونُ بَعْدَهُ. الَّذِي قَصُرَتْ عَنْ رُؤْيَتِهِ أَبْصَارُ النَّاظِرِينَ، وَ عَجَزَتْ عَنْ نَعْتِهِ أَوهامُ اَلْوَاصِفِينَ ابْتَدَعَ بِقُدْرَتِهِ الْخَلْقَ اَبتِدَاعَاً، وَ اخْتَرَعَهُمْ عَلَى مَشِيَّتِهِ اختراعاً،

*ምስጋና ሁሉ ለአላህ ነው፣*

*ከሱ በፊት ጅማሮ ሳይኖር የመጀመሪያ የሆነ፣*
*ከሱ ወዲያ የመጨረሻ ላይኖር የመጨረሻ የሆነ፣*
*በተመልካቾች እይታ ከመታየት የላቀ፣*
*ከጥልቅ አሳቢዎችና ተመራማሪዎች አዕምሮ የራቀ፡፡*

*በኃያልነቱ ፍጥረታቱን ከምንም አስገኘ*
*ለፈቃዱ (ለመሻቱ) ፍጹም ተገዥ አደረጋቸውም፡፡*

በዚህ ምንባብ ውስጥ የአላህን «የመጀመሪያነት» እና «የመጨረሻነት» ጠለቅ ባለ አገላለጽ ታገኛለህ፡፡ የአላህን የዘለዓለማዊነት ጽንሰ-ሐሳብ በቀላል ቋንቋ በመግለጽ ኃያሉ ጌታ ከሰዎች እይታና ከአዕምሮ ምርምር የራቀና የላቀ መሆኑንና ፍጥረታትን በሙሉ ከምንም ነገር ያስገኘ መሆኑን በመግለጽ ስለ ፍጥረታት ማወቅ ያለብንን ትክክለኛውን አስተሳሰብ ይጠቁመናል፡፡

በሰድስተኛው ዱዓእ ውስጥ ደግሞ የአላህ ኃይልነትና ሁሉን ቻይነት በተለየ አባባል ዘይቤ) ሲገለጽ ታነባለህ፦

أَلْحَمْدُ للهِ الَّذِي خَلَقَ اللَّيْلَ وَالنَّهارَ بِقُوَّتِهِ، وَمَيَّزَ بَيْنَهُمَا بِقُدْرَتِهِ، وَجَعَلَ لِكُلِّ وَاحِد مِنْهُمَا حَدّاً مَحْدُوداً، وَأَمَداً مَمْدُوداً، يُولِجُ كُلَّ وَاحِد مِنْهُمَا فِي صَاحِبِهِ، وَيُولِجُ صَاحِبَهُ فِيهِ بِتَقْدِير مِنْهُ لِلْعِبَادِ فِيمَا يَغْذُوهُمْ بِهِ وَيُنْشِئُهُمْ عَلَيْهِ، فَخَلَقَ لَهُمُ اللَّيْلَ لِيَسْكُنُوا فِيْهِ مِنْ حَرَكَاتِ التَّعَبِ، وَنَهَضَاتِ النَّصَبِ، وَجَعَلَهُ لِبَاساً لِيَلْبَسُوا مِنْ رَاَتِهِ وَمَنَامِهِ، فَيَكُونَ ذَلِكَ لَهُم جَمَاماً وَقُوَّةً، وَلِيَنَالُوا بِهِ لَذَّةً وَشَهْوَةً

*ሌሊትና ቀንን በኃያልነቱ የፈጠረ፣*
*በችሎታው ያፈራረቃቸውና የለያያቸው፣*
*ለእያንዳንዳቸውም የተወሰነ ገደብ ያደረገ፣*
*ባሪያዎቹ ሲሳያቸውን ያገኙ ዘንድ ሌቱን በቀን፣ ቀኑን በሌት ያከታተለ፣*

*ከቀኑ ድካምና ሩጫ ተገተው ያርፉ ዘንድ ሌሊቱን የፈጠረላቸው፣*
*አዲስ ኃይልና ብርታት ይሰበስቡ ዘንድ ሌሊቱን የእረፍትና ምቾት*
*ልብስ ያደረገላቸው ጌታ ምሥጋና ሁሉ ለአላህ ነው፡፡*

የቀንና ሌሊት ጥበባትን በመጠቃቀስ ይቀጥላል፡፡ የቀንና ሌሊትን ፍጥረት አስመልክቶ የሰው ልጅ ለፈጠራቸውና ላስተናበራቸው ጌታ ምሥጋና የማድረስ ግዴታ እንዳለበት ያወሳል፡፡

በሰባተኛው ዱዓእ ውስጥ ደግሞ ነገሮች ሁሉ በአላህ እጅ ውስጥ ስለመሆናቸው በሚከተለው መልኩ ይገለጻል፡-

يَا مَنْ تُحَلُّ بِهِ عُقَدُ الْمَكَارِهِ، وَيَا مَنْ يُفْثَأُ بِهِ حَدُّ الشَّدَائِدِ، وَيَا مَنْ يُلْتَمَسُ مِنْهُ الْمَخْرَجُ إِلَى رَوْحِ الْفَرَجِ، ذَلَّتْ لِقُدْرَتِكَ الصِّعَابُ وَتَسَبَّبَتْ بِلُطْفِكَ الاسْبَابُ، وَجَرى بِقُدْرَتِكَ الْقَضَاءُ وَمَضَتْ عَلَى إرَادَتِكَ الاشْياءُ، فَهْيَ بِمَشِيَّتِكَ دُونَ قَوْلِكَ مُؤْتَمِرَةٌ، وَبِإِرَادَتِكَ دُونَ نَهْيِكَ مُنْزَجِرَةٌ.

*በፈቃድህ የችግሮች ሁሉ ቀንበር የሚሰበር አላህ ሆይ!*
*በፈቃድህ የማይበጁን ነገሮች እስርና ትብታብ የሚፈታ ጌታችን ሆይ!*
*የመከራና ችግር ስለት በፈቃድህ የሚዶለዱም ጌታ ሆይ!*
*በችግር ጊዜ እፎይታን ለማግኘት የምንማፀንህ አላህ ሆይ!*

*አስቸጋሪና የማይጠሩ ነገሮች በችሎታህ ፊት ይዋረዳሉ፣*
*የነገሮች ሁሉ አስባብ በፀጋህ ይከሰታሉ፣*
*በፈቃድህ ትዕዛዝህን ይከተላሉ*
*ነገሮች ሁሉ እንደፈቃድህ ይውላሉ*
*በቃልህ ትዕዛዝ ሳትሰጥ በመሻትህ ይታዘዛሉ*
*በቃልህ ሳትከለክል በፈቃድህ ይታቀባሉ*

ii. **በሰሒፈህ አል-ሰጃዲያህ ውስጥ የሚዘወተረው ሁለተኛው መልዕክት አላህ ለሰው ልጆች የዋለላቸውን ችሮታዎችና ፀጋ የሚመለከት ሲሆን የሰው ልጅ በአምልኮውና በመታዘዙ እንዲሁም በሱ ላይ በብቸኝነት በመመካት ችሮታውንና ፀጋውን መክፈል አለመቻሉን ያወሳል፡፡ በ38ኛው ዱዓእ እንደሚከተለው እናገኛለን፡፡**

أللَّهُمَّ إنَّ أَحَداً لاَ يَبْلُغُ مِنْ شُكْرِكَ غَايَةً إلاّ حَصَلَ عَلَيْهِ مِنْ إحْسَانِكَ مَا يُلْزِمُهُ شُكْرَاً، وَلا يَبْلُغُ مَبْلَغاً مِنْ طَاعَتِكَ وَإن اجْتَهَدَ إلاَّ كَانَ مُقَصِّراً دُونَ اسْتِحْقَاقِكَ بِفَضْلِكَ، فَأَشْكَرُ عِبَادِكَ عَاجِزٌ عَنْ شُكْرِكَ وَأَعْبَدُهُمْ مُقَصِّرٌ عَنْ طَاعَتِكَ،

*አላህ ሆይ! የምስጋናህን ድካ ማንም አይደርስበትም፣*
*ለበለጠ ምሥጋና የሚዳርግ ፀጋህ ድካ የለውምና*
*(በተመሰገንክ ቁጥር ፀጋህ እየሰፋ ያሸንፋልና)*

*ምን ያህል ቢለፋ እንኳን ለአንተ በመታዘዝ ድካ የሚደርስ አንዳችም የለም፣*
*ከችሮታህ አንጻር ምሥጋናው እምነት ነውና፡፡*

*ከባሪያዎች እጅጉን አመስጋኙ ምሥጋናህን አድርሶ ከቶ አይችልም፣*
*እጅጉን አምላኪህና ታዛዥህ አምልኮህን አድሶ ከቶ አይችልም፡፡*

ለአንድ አፍታ እንኳን ከማይቋረጠው ወደር-የለሽና ሥፍር ቁጥር የለሽ የአላህ ፀጋና ችሮታ አንጻር የሰው ልጅ የሚገባውን ያህል ምሥጋና ማድረስ አይችልም፡፡ እጅግ አመስጋኝና እጅግ ታዛዥ የሆኑት እንኳን የምሥጋናውን ድካ ሊደርሱበት አይችሉም፡፡ ታዲያ ጥፋት ያለመፈጸም ኃያሉና ፈቃዱ በእጁ እያለ በድፍረት የአላህን ትዕዛዝ በመጣስ የወነጀለ ሰው ለጥፋቱ ምን ማካካሻ መስጠት ይችል ይሆን? ይህ ደግሞ ቀጥሎ ባለው በአስራ ስድስተኛው ምንባብ ውስጥ እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

يَا إِلهِي لَوْ بَكَيْتُ إِلَيْكَ حَتَّى تَسْقُطَ أَشْفَارُ عَيْنَيَّ، وَانْتَحَبْتُ حَتَّى يَنْقَطِعَ صَوْتِي، وَقُمْتُ لَكَ حَتَّى تَتَنَشَّرَ قَدَمَايَ، وَرَكَعْتُ لَكَ حَتَّى يَنْخَلِعَ صُلْبِي، وَسَجَدْتُ لَكَ حَتَّى تَتَفَقَّأَ حَدَقَتَايَ، وَأَكَلْتُ تُرَابَ الارْضِ طُولَ عُمْرِي، وَشَرِبْتُ مَاءَ الرَّمَادِ آخِرَ دَهْرِي

وَذَكَرْتُكَ فِي خِلاَلِ ذَلِكَ حَتَّى يَكِلَّ لِسَانِي ثُمَّ لَمْ أَرْفَعْ طَرْفِي
إِلَى آفَاقِ السَّمَاءِ اسْتِحْيَاءً مِنْكَ مَا اسْتَوْجَبْتُ بِذَلِكَ مَحْوَ سَيِّئَة
وَاحِدَة مِنْ سَيِّئَاتِي،

*ጌታዬ ሆይ!*
*ዓይኖቼ ወጥተው እስኪወድቁ ባነባ እንኳ፣*
*ድምጼ ተዘግቶ እስኪጠፋ ባለቅስም፣*
*እግሮቼ እስኪሰነጣጠቁ በፊትህ ብቆም፣*
*ጀርባዬ እስኪደነዝዝና እስኪወልቅ ድረስ በፊትህ ባጎነብስ፣*
*ዓይኖቼ እስኪፈሱና በአጥንቴ እስኪቀር ድረስ በፊትህ (በሱጁድ) ብደፋ፣*
*ህይወቴን ሙሉ አፈር እየበላሁ ብኖር፣*
*ዕድሜ ልኬን በአመድ የደፈረሰ ውሃ ብጠጣ፣*
*አንደበቴ እስኪዘጋ ድረስ ክብርህን ብዘምር፣*

*እንዲህም ሁኜ አምላኬ ሆይ - ከሰራኋቸው ሐጢአቶች አንዱንም ትምረኝ ዘንድ ወደ ሰማይ አድማስ ዓይኔን ለማንሳት አፍራለሁ፡፡*

iii. ሦስተኛው በተደጋጋሚ የምናገኘው መልዕክት መለኮታዊ ሽልማትና ቅጣትን - ጀነትና ጀሀነምን - በተመለከተ ነው፡፡ እዚህ ላይ አላህ የሰው ልጆችን የሚሸልመው ወይም ለጀነት የሚያበቃቸው በፀጋውና በችሮታው ብቻ እንደሆነና የሰው ልጅ በመሠረቱ ለእጅግ ትንሹ ሐጢአቱ እንኳን የሚገባው ቅጣት እንጂ ሌላ እንዳልሆነ እንረዳለን፡፡

በሰሒፋህ አል-ሰጃዲያህ ውስጥ ያሉ ዱዓዎች በሙሉ በሰው ልጆች ውስጥ የቅጣት ፍርሃትን ለመፍጠርና ለአላህ ሽልማትና ምህረት ተስፋ እንዲኖራቸው ለማድረግ ይህንን ጉዳይ በተደጋጋሚ ያነሳሉ፡፡ ይህ ሁሉ የተገለጸው የሰው ልጅ በሐጢአት አረንቋ ውስጥ እንዳይዘፈቅ በሰው ልብ ውስጥ ጥልቅ ፍርሃት ለመፍጠር በሚያስችል እጅግ በረቀቀ ዘይቤ ነው፡፡ ለምሳሌ በአርባ ስድስተኛ ዱዓእ ውስጥ የሚከተለውን እናገኛለን፡፡

حُجَّتُكَ قَائِمَةٌ، وَسُلْطَانُكَ ثَابِتٌ لا يَزُولُ، فَالْوَيْلُ الدَّائِمُ لِمَنْ جَنَحَ عَنْكَ، وَالْخَيْبَةُ الْخَاذِلَةُ لِمَنْ خَابَ مِنْكَ، وَالشَّقاءُ الاشْقَى لِمَنِ اغْتَرَّ بِكَ. مَا أَكْثَرَ تَصَرُّفَهُ فِي عَذَابِكَ، وَمَا أَطْوَلَ تَرَدُّدَهُ

فِيْ عِقَابِكَ، وَمَا أَبْعَدَ غَايَتَهُ مِنَ الْفَرَجِ، وَمَا أَقْنَطَهُ مِنْ سُهُولَةِ
الْمَخْرَجِ عَدْلاً مِنْ قَضَائِكَ لاَ تَجُورُ فِيهِ، وَإنْصَافاً مِنْ حُكْمِكَ
لاَ تَحِيفُ عَلَيْهِ، فَقَدْ ظَاهَرْتَ الْحُجَجَ، وَأَبْلَيْتَ الاعْذَارَ،

*ውሳኔህ ግልጽ ነው በማንም በምንም ላይቀለበስ፣*
*ስልጣንህና የበላይነትህ ዘለዓለማዊ ነው በምንም ላይገታ፣*

*ከአንተ ላፈነገጠ ዘለዓለማዊ ቅጣት አለለት*
*ከአንተ የሸሸ አይጠፉ ጥፋት ጠፋ*
*ከአንተ የዞረ በከፋ አደጋ ውስጥ ወደቀ*
*በቅጣትህ ምን ያህል ይሰቃያል?!*
*በስቃይ ውስጥ ምን ያህል ይዳክራል?!*
*ከእረፍትና ከእፎይታ ምኑን ያህል የራቀ ነው?!*
*ከዚህ ጉድ ለመውጣት ተስፋው እንዴት ይጨልማል?!*

*ፍርድህ ሁሉ ፍትሓዊ ነው ማንም የማይጋፈጠው፣*
*ውሳኔህ ሁሉ ቅን ነው ማንም የማይቀለብሰው፣*
*ሁሉን ነገር ቀድመህ ግልጽ አደረግክ*
*ለአቤቱታ ቦታ የለህም…*

**እንዲሁም በሰላሳ አንደኛው ዱዓእ ውስጥ እንዲህ እናነባለን፡-**

أَللَّهُمَّ فَارْحَمْ وَحْدَتِي بَيْنَ يَدَيْكَ، وَوَجِيبَ قَلْبِي مِنْ خَشْيَتِكَ، وَاضْطِرَابَ أَرْكَانِي مِنْ هَيْبَتِكَ، فَقَدْ أَقَامَتْنِي يَا رَبِّ ذُنُوبِي مَقَامَ الْخِزْيِ بِفِنَائِكَ، فَإِنْ سَكَتُّ لَمْ يَنْطِقْ عَنِّي أَحَدٌ، وَإِنْ شَفَعْتُ فَلَسْتُ بِأَهْلِ الشَّفَاعَةِ

*ጌታዬ ሆይ! ለብቻዬ ፊትህ ለቆምኩት፣*
*ለፍራቻህ ለራደው ልቤ፣*
*ለሞገስህ ለተብረከረከው አካላቴ፣*
*ምህረትህን ቸረን፡፡*

*ጌታዬ ሆይ! ሐጢአቴ በፊትህ አፍሬና ተሸማቅቄ እንድቆም ያደርጉኛል፤*
*ዝም ካልኩኝ የሚናገርልኝ የለም፣ የሚያማልድልኝ (የሚያማልደኝ) አንድ ሰው ካልተገኘ በቀር የምልጃ መብትም የለኝም፡፡*

**በሰላሳ ዘጠነኛው ዱዓእ ውስጥም የሚከተለውን እናገኛለን፡፡**

فَإنَّكَ إنْ تُكَـافِنِي بِالْحَقِّ تُهْلِكْنِي، وَإلاّ تَغَمَّـدْنِي بِرَحْمَتِكَ تُوبِقْنِي ... وَأَسْتَحْمِلُكَ مِنْ ذُنُوبِي مَا قَدْ بَهَظَنِي حَمْلُهُ، وَأَسْتَعِينُ بِكَ عَلَى مَا قَدْ فَدَحَنِي ثِقْلُهُ. فَصَلِّ عَلَى مُحَمَّد وَآلِهِ، وَهَبْ لِنَفْسِي عَلَى ظُلْمِهَا نَفْسِيْ، وَوَكِّلْ رَحْمَتَكَ بِاحْتِمَالِ إصْرِي،

*(በሰራሁት ጥፋት) በፍትህ የምትቀጣኝ ከሆነ መጥፋቴ ነው፣*
*በምህረትህ ካልሸፈንከኝ በቀር መውደቄ ነው*

*ጌታዬ ሆይ! ጀርባዬን ያጎበጠውን የሐጢአት ሸክሜን እንድታነሳልኝ እማፀንሃለሁ፣*
*በጉልበቴ ያንበረከከኝን ሸክሜን እንድታስወግድልኝ እጠይቅሃለሁ፡፡*

*በሙሐመድና ቤተ-ዘሩ ላይ ሰላም አውርድ፡፡ በራሴ ላይ በደል ለፈጸመችው ነፍሴ ምህረትህን ለግስ፡፡ በምህረትህ የሐጢአቴን ሸክም አንሳልኝ፡፡...*

iv. **የዱዓዎቹ አራተኛው መልዕክት ዱዓዎቹን የሚቀሩ ሰዎችን ወደ ፍጹምነት ደረጃ ማንሳት፣ ከእኩይ ተግባራትና ክፉ ባህሪያት ማራቅ፣ አዕምሮአቸውን ማጥራትና ልቦቻቸውን ማጽዳት የሚቻልበትን አካሄድ የሚጠቁሙ መሆናቸው ነው፡፡ በሃያኛው ዱዓእ ውስጥ የሚከተለውን እናገኛለን፡፡**

أللَّهُمَّ وَفِّرْ بِلُطْفِكَ نِيَّتِي، وَصَحِّحْ بِمَـا عِنْدَكَ يَقِينِي، وَاسْتَصْلِحْ بِقُدْرَتِكَ مَا فَسَدَ مِنِّي.

أللَّهُمَّ صَلِّ عَلَى مُحَمَّد وَآلِ مُحَمَّد، وَمَتِّعْنِي بِهُدىً صَالِح لا أَسْتَبْدِلُ بِهِ، وَطَرِيقَةِ حَقٍّ لا أَزِيْغُ عَنْهَا، وَنِيَّةِ رُشْد لاَ أَشُكُّ فِيْهَا

أللَّهُمَّ لا تَدَعْ خَصْلَةً تُعَابُ مِنِّي إلاّ أَصْلَحْتَهَا، وَلا عَائِبَةً أُوَنَّبُ بِهَا إلاّ حَسَّنْتَهَا، وَلاَ أُكْـرُومَـةً فِيَّ نَاقِصَةً إلاّ أَتْمَمْتَهَا

*ጌታዬ ሆይ! ሐሳቤን በእዝነትህ ሙላልኝ፡-*
*አንተ ጋ ባለው የቂኔን (እርግጠኝነቴን) እውን አድርግልኝ*
*እኔ ጋ የተበላሸውን አንተ በችሎታህ አቅናልኝ…*

*...ጌታ ሆይ! በሙሐመድና ቤተ-ዘሩ ላይ ሰላምና በረከትህን አውርድ!*
*ልቀይረው የማልችለውና የሂዳያ መንገድ ምራኝ፣*
*ልልቀው የማልችለው የሐቅ ጎዳና ላይ አኑረኝ*
*የማልጠረጥረውን የፀናና እውነተኛ ኒያ ለግሰኝ...*

*አላህ ሆይ!*
*ያለብኝን እኩይ ባህሪ ሳታርምልኝ አትተወኝ፣*
*ያለብኝን መጥፎ ሁሉ ሳታቃናልኝ አትለፈኝ፣*
*ካለብኝ ጉድለት ሁሉ በምሉዕነት ሳትልቀኝ አትተወኝ፡፡*

v. **አምስተኛው የዱዓዎቹ መልዕክት ደግሞ ዱዓውን የሚቀራ ሰው ከአላህ ውጭ ባሉት ነገሮች ላይ መመካት እንደሌለበትና በአላህ ላይ የመመካት አስፈላጊነትን አስመልክቶ የማነሳሳት ሥራ የሚሰራ ነው፡፡ በሌሎች ፊት ራሱን እንዳያዋርድና ለሚፈልጋቸው ነገሮች ሁሉ በአላህ እንጂ በሌላ ነገር ላይ እንዳይተማመን ሥልጠና ይሰጣል፡፡ ለሌሎች ሰዎች ንብረት መሰገብገብ ከሰው ልጅ መጥፎ ባህሪያት አንዱ ነውና፡፡ በሃያኛው ዱዓእ ውስጥ እንዲህ ይነበባል፡-**

وَلا تَفْتِنّي بِالاسْتِعَانَةِ بِغَيْرِكَ إذَا اضْطُرِرْتُ، وَلا بِالْخُضُوعِ لِسُؤالِ غَيْرِكَ إذَا افْتَقَرْتُ، وَلاَ بِالتَّضَرُّعِ إلَى مَنْ دُونَكَ إذَا رَهِبْتُ فَأَسْتَحِقَّ بِذلِكَ خِذْلانَكَ وَمَنْعَكَ وَإعْرَاضَكَ

*...በችግሬ ጊዜ አንተን ብቻ እንጂ ሌላ እንድማፀን አትፈትነኝ፣*
*አንተን እንጂ ሌሎች ፍጡራንን በመለመን እራሴን እንዳዋርድ አታድርገኝ፣*

*ፍርሃት ሲያድርብኝ አንተን ብቻ እንጂ ሌላ እንድጣራ አታድርገኝ፡፡*
*በነዚህ ተግባራት በረከትህን እንዳልነፈግ፣ ከፀጋህ እንዳልርቅና ከችሮታህ እንዳልባረር አንተው ጠብቀኝ፡...*

**በሃያ ስምንተኛው ዱዓእ ደግሞ የሚከተለውን እናገኛለን፡-**

اللَّهُمَّ إنِّي أَخْلَصْتُ بِانْقِطَاعِي إلَيْكَ، وَصَرَفْتُ وَجْهِي عَمَّنْ يَحْتَاجُ إلَى رِفْدِكَ، وَقَلَبْتُ مَسْأَلَتِي عَمَّنْ لَمْ يَسْتَغْنِ عَنْ فَضْلِكَ، وَرَأَيْتُ أَنَّ طَلَبَ الْمُحْتَاجِ إلَى الْمُحْتَاجِ سَفَهٌ مِنْ رَأيِهِ وَضَلَّةٌ مِنْ عَقْلِهِ،

*…ጌታ ሆይ! እነሆ በእርግጥ እራሴን ለአንተ ብቻ አሳደርኩ፣ እራሳቸው ከአንተ እርዳታ ከሚሹ ሰዎች እርዳታ ከመፈለግ ተብቃቅሁ፡፡ እራሳቸው ከአንተ ፀጋ ካልተብቃቁ ሰዎች ላይ ተስፋ ከማድረግና ከመተማመን ፊቴን አዞርኩ፡፡*

*አንድ የሚቸገር ሰው ከሌላ የሚቸገር ሰው ድጋፍ መፈለግ የአስተሳሰብ ጅላጅልነትና የአዕምሮ ቅዠት ነው፡፡*

**በተጨማሪም በአስራሦስተኛው ዱዓእ ውስጥ እንዲህ ይነበባል፡-**

فَمَنْ حَاوَلَ سَدَّ خَلَّتِهِ مِنْ عِنْدِكَ وَرَامَ صَرْفَ الْفَقْرِ عَنْ نَفْسِهِ بِكَ فَقَدْ طَلَبَ حَاجَتَهُ فِي مَظَانِّها وَأَتَى طَلِبَتَهُ مِنْ وَجْهِهَا وَمَنْ تَوَجَّهَ بِحَاجَتِهِ إِلَى أَحَد مِنْ خَلْقِكَ أَوْ جَعَلَهُ سَبَبَ نُجْحِهَا دُونَكَ فَقَدْ تَعَرَّضَ لِلْحِرْمَانِ، وَاسْتَحَقَّ مِنْ عِنْدِكَ فَوْتَ الإحسان

*ችግሩን በአንተ መቅረፍ የሞከረና ድህነትን በአንተ ከራሱ ለመመከት የጣረ ሰው በእርግጥ ችግሩንና ፍላጎቱን ወደ ትክክለኛው ቦታ አቤት ብሏል፣ የሚፈለገውንም ነገር ከትክክለኛው አቅጣጫ ፈልጓል፡፡ ነገር ግን ችግሩን*

*ከፍጡሮችህ በአንዱ ለማስወገድ የሞከረና ከአንተ ውጭ ያለውን ነገር ለስኬቱ መንስዔ ይሆናል ብሎ ያሰበ ሰው እራሱን ለኪሳራ ያጋለጠና የፀጋህና ችሮታህ እጦት የተገባው ነው፡፡*

vi. በስድስተኛ ደረጃ እነዚህ ዱዓዎች ህዝቡን የሚያስተምሩት፣ የሌሎች ሰዎችን መብት የመጠበቅ አስፈላጊነትና ግዴታ፣ ሌሎችን መርዳት፣ ለሌሎች ሰዎች አዛኝና ርህሩህ መሆን፣ ለሌሎች ሰዎች ጉዳይ መስዋዕት መክፈልና በአጠቃላይ ኢስላማዊ ወንድማማችነትን እውን የማድረግ ተግባራትን ነው፡፡ ለምሳሌ ከሰላሳ ስምንተኛው ዱዓእ የሚከተለውን እናነባለን፡-

أَللَّهُمَّ إنِّي أَعْتَـذِرُ إلَيْـكَ مِنْ مَـظْلُوم ظُلِمَ بِحَضْرَتِي فَلَمْ أَنْصُرْهُ، وَمِنْ مَعْرُوف أُسْدِيَ إلَيَّ فَلَمْ أَشْكُرْهُ، وَمِنْ مُسِيء أعْتَذَرَ إلَيَّ فَلَمْ أَعْذِرْهُ، وَمِنْ ذِيْ فَاقَة سَأَلَنِي فَلَمْ أُوثِرْهُ، وَمِنْ حَقِّ ذي حَقٍّ لَزِمَنِي لِمُؤْمِن فَلَمْ أوَفِّـرْهُ، وَمِنْ عَيْبِ مُؤْمِن ظَهَر لِي فَلَمْ أَسْتُرْهُ،..

*…ጌታ ሆይ! እኔ ባለሁበት ቦታ የተበደለ ሰው አጋጥሞኝ ሳልረዳው በመቅረቴ ይቅርታ እጠይቅሃለሁ፣ ውለታ የዋለልኝን ሰው ሳላመሰግን በመቅረቴ ይቅር በለኝ፣ በደል አድርሶብኝ ይቅርታ ለጠየቀኝ ሰው ይቅርታ ሳላደርግ በመቅረቴም በአንተ ፊት እፀፀታለሁ፣ ችግር ገጥሞት እርዳታ ለጠየቀኝ ከራሴ አስቀድሜ ሳልረዳው በመቅረቴም ይቅር በለኝ፣ በኔ ላይ ግዴታ የሆነ መብት ያለውን አማኝ መብቱን ሳላሟላ በመቅረቴም ይቅርታ እጠይቀሃለሁ፣ የአንድን አማኝ ሰው ነውር አውቄ ሳልደብቅ የቀረሁ እንደሆነ ይቅር በለኝ…*

ይቅርታ መጠየቅ ነፍስ ለላቀ መለኮታዊ ስብዕና የሚያስፈልጉ ተግባራት በመሥራት ትነቃቃ ዘንድ ውጤታማ የሆነ የምክር ዘዴ ነው፡፡

በሰላሳ ዘጠነኛው ዱዓእ ከዚህ የበለጠ ጠቃሚ ነገር እናገኛለን፡፡ የበደለህን ሰው ይቅር የማለት ግዴታ እንዳለብህ ያስተምርሃል፡፡ ከብቀላ እንድትታቀብ ያስገድዳሃል፣ በዚህ መልኩ ወደ ጻድቆች ደረጃ ከፍ ያደርገሃል፡፡

أللَّهُمَّ وَأَيُّمَا عَبْد نالَ مِنِّي مَا حَظَرْتَ عَلَيْهِ، وَانْتَهَكَ مِنِّي مَا حَجَرْتَ عَلَيْهِ، فَمَضَى بِظُلاَمَتِي مَيِّتاً، أَوْ حَصَلْتَ لِيْ قِبَلَهُ حَيّاً، فَاغْفِرْ لَهُ مَا أَلَمَّ بِهِ مِنِّي، وَاعْفُ لَهُ عَمَّا أَدْبَرَ بِهِ عَنِّي، وَلاَ تَقِفْـهُ عَلَى مَا ارْتَكَبَ فِيَّ، وَلاَ تَكْشِفْهُ عَمَّا اكْتَسَبَ بِيْ، وَاجْعَلْ مَا سَمَحْتُ بِـهِ مِنَ الْعَفْـوِ عَنْهُمْ وَتَبَـرَّعْتُ بِـهِ مِنَ الصَّدَقَةِ عَلَيْهِمْ أَزْكَى صَدَقَاتِ الْمُتَصَدِّقِينَ وَأَعْلَى صِلاَتِ الْمُتَقَرِّبِينَ، وَعَوِّضْنِي مِنْ عَفْوِي عَنْهُمْ عَفْوَكَ وَمِنْ دُعَائِي لَهُمْ رَحْمَتَكَ حَتَّى يَسْعَدَ كُلُّ وَاحِد مِنَّا بِفَضْلِكَ

*ጌታ ሆይ! ከባሮችህ አንዱ ሐራም ባደረከው ነገር ከበደለኝ፣*

*በከለከልከው ነገር መብቴን ከተጋፋና እንደበደለኝ ሞት ቢደርስበት ወይም በህይወት እያለም ክሴ ቢኖርበት*

*በኔ ላይ ላደረሰው በደል ይቅር በለው፡፡*

*በኔ ላይ ዞሮ ላጠፋው ጥፋት ይቅርታ አድርግለት፣*

*በኔ ላይ ላደረሰው በደል አትጠይቀው፣*

*በኔ ላይ በፈጸመው በደል አተጋልጠው፣*

*በኔ አማካይነት ባገኘው ነገር አታዋርደው፣*

*ያደረግኩላቸውን ይቅርታና ያቀረብኩላቸውን ስጦታ*
*የመጽዋቾች ምርጥ ምጽዋት አድርግልኝ፣*
*ወደ አንተ ቅርብ የሆኑ ሰዎች ምርጥ ስጦታ አድርግልኝ፣*

*ለነሱ ያደረግኩትን ምህረት በምህረትህ ተካልኝ፣*
*ለነሱ ያደረግኩትን ዱዓእ በይቅርታህ ካሰኝ*
*በዚህ መልኩ እያንዳንዳችን በእዝነትህ ደስታን*
*እንድንጎናጸፍ አድርገን፣*
*ሁላችንንም በችሮታህ አድነን፡፡*

ምንኛ ድንቅ አባባሎች ናቸው! ለሁሉም የሰው ልጆች ደስታና ብልጽግና ቀና የማሰብ አስፈላጊነትን በሚማርክ ሁኔታን ነፍስን እየኮረኮሩ የምሉዕ ሰው ባህሪን የሚገነቡ ናቸው፡፡ ምንኛ ባመረ መልኩ የመልካም ሰዎችን ልብ ሰብረው ለበደላቸውና ላስቀየማቸው ሰዎች እንኳ ደስታን እንዲመኙ እንደሚያስጠነቅቁ ልብ በል!

በሰሒፊህ አል-ሰጃዲያህ ውስጥ እነዚህን የመሳሰሉ በርካታ ምሳሌዎች አሉ፡፡ የሰው ልጅ ብሎለት ትኩረት ቢሰጣቸው! ትኩረት ቢሰጣቸውማ በሁሉም ዓይነት

መለኮታዊ ሞራሊቲ አስተምህሮዎች የተሞሉ ሆነው ያገኛቸው ነበር፡፡

## 36. የመቃብር ቦታዎችን መጎብኘት/ዚያራ አስመልክቶ ያለን እምነት

ሺዓዎችን ከሌሎች የኢስላም ቡድኖች (መዝሐቦች) ከሚለያቸው ተግባራት አንዱ የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እና የኢማሞች መቃብሮችን መጎብኘት (መዘየር) አስመልክቶ የሚሰጡት ትኩረት ነው፡፡ በተጨማሪም ሺዓዎች እጅግ ያማሩና የተከበሩ ደሪሆችን (የመታሰቢያ ግንቦችን) እና በመቃብር ላይ የሚገነቡ ቤቶችን በመገንባት ከሌሎች መዝሐቦች በተለየ ሁኔታ ይታወቃሉ፡፡

እነዚህ ሁሉ ነገሮች የሚሰሩት በኢማሞቹ አስተያየት መሠረት ነው፡፡ ኢማሞቹ ተከታዮቻቸው ወደ ቅዱሳን መቃብሮች በመሄድ ዚያራ እንዲያደርጉ (እንዲጎበኙ) በተደጋጋሚ ይገፏፏቸውና ያበረታቷቸው ነበር፡፡ ይህንንም በማድረግ ከአላህ ታላቅ የሆነ አጅር (ሽልማት) እንዲያገኙ ያበረታቱ ነበር፡፡ ከግዴታ አምልኮዎች (ዒባዳዎች) ቀጥሎ ከሚመጡ የአምልኮ ተግባራት ምርጡ

ሲሆን መካነ-መቃብሮቹ ደግሞ ዱዓእ (ፀሎት) ለማድረግና ወደ አላህ ለመቃረብ ምርጥ ቦታዎች ናቸው፡፡

በተጨማሪም በኢማሞቹ ሐዲስ መሠረት ይህ የዚያራ ተግባር ለኢማሞቹ ታማኝ መሆን የሚገለጽበት የተግባር ዓይነት ነው፡፡ ኢማም ሪዳ (ዐ.ሰ) ሲናገሩ፡-

«*በእያንዳንዱ ኢማምና በተከታዮቹ መካከል ቃል-ኪዳን አለ፡፡ ዚያራ ደግሞ ለቃል-ኪዳኑ ታማኝ መሆን የሚገለጽበት መንገድና ቃል የሚጠበቅበት መንገድ ነው፡፡ በራሱ ተነሳሽነት አምኖበት ዚያራ ያደረገ ሰው የቂያማ ቀን የኢማሞቹን ሸፈዓ (ምልጃ) ያገኛል፡፡*»

ከዚያራ (ጉብኝት) የሚገኙ ማህበራዊና ኃይማኖታዊ ጥቅሞች አሉ፡፡ ስለዚህ ኢማሞቻችን ለዚህ ተግባር ትልቅ ትኩረት ሰጥተው ነበር፡፡ ዚያራ በኢማሞቹና ተከታዮቻቸው መካከል ያለው ግንኙነት እንዲጎለብትና መልካም ስብዕናቸውና ገድላቸው እንዲሁም ለእውነት ያደረጉት ትግል እየተወሳ እንዲኖር ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም ሙስሊሞች በአንድ ቦታ በመሰባሰብ

እንዲተዋወቁና ወዳጅነታቸው እንዲጎለብትና ለአላህ ለመታዘዝ ያላቸው ቁርጠኝነትና ትዕዛዛቱንና መመሪያውን ለማክበር ያላቸው ጽኑነት በልቦቻቸው እንዲታተም ያደርጋል፡፡ የዚያራን ትክክለኛውን ትርጉም እንዲያገኙ፣ የተውሂድን እውነታ፣ የኢስላምን ቅድስና፣ የሙሐመድን ነቢይነት እንዲያረጋግጡና የላቀ ስብዕናን ለመጎናጸፍ፣ የፍጥረታት ሁሉ አዛዥ በሆነው አላህ ፊት ዝቅ በማለት ማምለክ፣ በዚያራው ወቅት በሚቀሩ ዱዓዎች አላህን መማጸን፣ ለፀጋዎቹ ማመስገንና ሌሎችን ኢስላማዊ ተግባራትን ለመተግበር አመቺ ሁኔታና ቦታ የሚፈጥር ተግባር ነው፡፡በዚያራው ወቅት የሚቀሩ ዱዓዎች ደግሞ የመጠቀ ትርጉም ያላቸው ናቸው፡፡ ለምሳሌ ኢማም ዘይነል ዓቢዲን (ዐ.ሰ) የአያታቸውን የአሚረል ሙዕሚኒን ዓሊን መቃብር ሲጎበኙ (ሲዘይሩ) ያጠናቀሩት «አሚን አላህ» የተሰኘው ዱዓእ ይጠቀሳል፡፡

በተጨማሪም በዚያራው ወቅት የሚቀሩ ዱዓዎች የኢማሞቹን ድንቅ ባህሪያትና ህይወት፣ ለእውነት የከፈሉትን መስዋዕት፣ ኃይማኖቱን ከፍ ለማድረግ ያሳለፉትን ገድልና ለአላህ በመታዘዝ ረገድ የነበራቸውን ቆራጥነት የሚጠቁሙ ናቸው፡፡ በቀላሉ መረዳት በሚቻሉ

ሐረጎች የተሞሉ በመጠቀ ቋንቋ የተቃና ነበሩ፣ በምርጥ አረቢኛ የተጻፉ የሚመስጡ አባባሎችን ያዘሉ ናቸው፡፡ በነዚህ ዱዓዎች ውስጥ ተውሂድ በመጠቀ ሁኔታ የተገለጸበትና አላህ ፊት ዱዓእ ለማድረግ ምርጥ አባባሎች የታጨቁበት ሆነው እናገኛለን፡፡ በእርግጥ ከነዚህ ውስጥ ደግሞ ከቁርአን ቀጥሎ የምናገኘው ታላቅ ኃይማኖታዊ ሥነ-ጽሑፍ ነህጀል በለጋና የኢማምቹ ሌሎች ዱዓዎችን ነው፡፡ ምክንያቱም ኢማሞቹ ኢስላማዊ ጉዳዮችንና ሞራሊቲን በተመለከተ በነዚህ መጽሐፍት ውስጥ አጠቃላይ በሆነ መልኩ አካተዋልና፡፡ በአንዳንድ የዚያራው ሥርዓቶች ወቅት ደግሞ የሙስሊሙን መንፈሳዊ ግንዛቤ የሚያጎለብቱ፣ ለደጋው ህብረተሰብ የማዘን ስሜትን የሚጭሩ፣ ወንድማማችነት እንዲጠነክርና እንዲያድግ የሚያነሳሱ፣ መልካም ሥነ-ምግባር እንዲዳብርና በሰዎች መካከል መረዳዳት እንዲኖር የሚያደርጉ አስተምህሮዎችና መመሪያዎችን ያዘሉ ሆነው እናገኛለን፡፡

እነዚህ ሥርዓቶች ወደ መቃብሩ ቦታ ሳይገባና የተለመደው የዚያራ ዱዓእ ሳይቀራ መደረግ ያለባቸው

ሥርዓቶች ናቸው፡፡ ሌሎቹ ደግሞ ወደ ቦታው በሚገባበት ወቅትና ከዚያ በኋላ የሚባሉ ናቸው፡፡ እዚህ ላይ ሐሳቡን ግልጽ ለማድረግ አንዳንዶቹን ለመጠቆም እንወዳለን፡፡

1. በመጀመሪያ ኢስላማዊ ህጉ በሚያዘው መሠረት ጎብኚው (ዚያራ አድራጊው) መታጠብ (ጉስል ማድረግ) አለበት፡፡ ይኸውም የዚያራ ሥርዓቱን ከመጀመሩ በፊት ሰውነቱን ንጹህ ማድረግ አለበት ማለት ነው፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ከማንኛውም ቆሻሻ እንዲፀዳ፣ ከማንኛውም በሽታዎች እንዲከላከል፣ ሌሎች ሰዎች በመጥፎ ጠረኑ እንዳይቸገሩና ይህ በእንዲህ እንዳለ መንፈሱንና አዕምሮውን ከሞራል እድፎች እንዲያነጻ ለማድረግ ነው፡፡

(ይህንን አስመልክቶ ኢማም ዓሊ አሚረል ሙዕሚኒን ሲናገሩ፡-

*«ሰውነታችሁን በውኃ በመታጠብ መጥፎ ጠረናችሁን አስወግዱ፣ ራሳችሁን በንጽህና ጠብቁ፡፡ ሰዎች አጠገባቸው በተቀመጡ ጊዜ ጠረናቸው (መጥፎ ሽታቸው)*

*የሚያስቀምጥ ንጽህና የኀደላቸው ሰዎችን አላህ ይቆጣቸዋል፡፡»*

ዚያራ አድራጊው ታጥቦ ከጨረሰ በኋላ ትኩረቱን በዚህ ታላቅ ዓላማ ላይ እንዲያደርግ ምን ማለት እንዳለበት የሚያወሱ ሐዲሶች ተዘግበዋል፡፡ ዚያራ አድራጊው እንዲህ ማለት አለበት፡-

( اللهم اجعل لي نورا وطهورا وحرزا كافيا من كل داء وسقم ومن كل آفة وعاهة, وطهر به قلبي وجوارحي وعظامي ولحمي ودمي وشعري وبشري ومخي وعظمي وما أقلت الأرض مني, واجعل لي شاهدا يوم حاجتي وفقري وفاقتي ).

*«አላህ ሆይ! ብርሃንና ንጽህናን ስጠኝ፣ ከማንኛውም በሽታ፣ ህመም፣ አደጋና እኩይ ነገር ሁሉ ሰውረኝ፡፡ በዚህ ትጥበቴ ልቤን፣ ሰውነቴን፣ አጥንቶቼን፣ ሥጋዬን፣ ደሜን፣ ፀጉሬን፣ ቆዳዬን አዕምሮዬን ነርቮቼን እንዲሁም በመሬት ላይ የነኳኋቸው ቦታዎች ሁሉ ንጹህ አድርግልኝ፡፡*

*በድህነቴ፣ በችግሬና 1ቀበመከራዬ ቀን መስካሪ አድርግልኝ፡፡»*

2. በሁለተኛ ደረጃ ዚያራ አድራጊው ያለውን ምርጥና ንጹህ አልባሳት መልበስ አለበት፡፡ ምክንያቱም በእንዲህ ዓይነቱ የመሰባሰብ ወቅት ሰዎች እንዲዋደዱና እንዲተዛዘኑ ያደርጋል፡፡ ክብራቸውም ስለሚጨምር የዚያራን አስፈላጊነትና ጥቅም እንዲረዱ ያደርጋል፡፡ እዚህ ላይ መታወቅ ያለበት ዚያራ አድራጊው መልበስ ያለበት ማግኘት የሚችለውን ምርጥና ንጹህ ልብስ ማለታችን ነው እንጂ በገበያ ላይ ሊገኙ የሚችሉትን እጅግ ምርጥ ልብሶች የግድ ማግኘት አለበት ማለት አይደለም፡፡ ሁሉም ሰው ምርጥና ውድ የሆነ ልብስ መልበስ ስለማይችል እንዲህ ዓይነቱ ትዕዛዝ ደኃዎችን ተስፋ ያስቆርጣል፡፡ ይህ ደግሞ የአላህን ፍላጎት የሚጻረር ነው፡፡ ስለዚህ እዚህ ላይ ጥንድ ትርጉም ያለውን ሐሳብ ልብ ማለት አለብን፡፡ ይኸውም ሰዎች በጥሩ ሁኔታ መልበስ አለባቸው፣ እንዲሁም የጸኃዎችንም ሁኔታ በደንብ ማጤን አለባቸው የሚል ነው፡፡

3. በሦስተኛ ደረጃ ደግሞ ዚያራ አድራጊው ከተቻለ ሽቶ መቀባት አለበት፡፡ ምክንያቱም የሽቶ መቀባት ጥቅሙ ልክ እንድ በጥሩ ሁኔታ መልበስ ነውና፡፡
4. አራተኛ ደግሞ አቅሙ በፈቀደው መሠረት ለደኃዎች መመጽወት አለበት፡፡ የዚህ ዓላማው በመጀመሪያ ደረጀ ደኃውን ክፍል ለመርዳት ሲሆን ሌላው ደግሞ በዚያራ አድራጊዎቹ ውስጥ የልግስና ስሜትን ለመጫር ነው፡፡
5. ዚያራ አድራጊው ወደ መቃብሩ ሥፍራ በቀስታና በእርጋታ መሄድ አለበት፡፡ ዙሪያውን እየቃኘና በግድ-የለሽነት መሆን የለበትም፡፡ ይህ ደግም በግልጽ የሚያሳየው ለተቀደሰው ሥፍራ (ሀረም)፣ ለዚያራውና በቦታው ለተቀበሩ ሰዎች ክብር መስጠት ብቻ ሳይሆን ትኩረቱን ሁሉ ወደ አላህ ማድረግንና በመንገዱ ላይ ሌሎች ሰዎችን እንዳይረብሽ ጥንቃቄን ማድረግን ነው፡፡
6. በስድስተኛ ደረጃ ደግሞ ዚያራ አድራጊው «አላህ አክበር» (አላህ ታላቅ ነው) የሚለውን የቻለውን ያህል ደጋግሞ ማለት አለበት፡፡ አንዳንድ የሐዲስ ሊቆች መቶ ጊዜ ደጋግሞ እንዲል ያዛሉ፡፡ በዚህም የአላህን

ታላቅነትና ልዕልና ያስታውሳል፣ ከሱ በላይ የላቀና የተቀደሰ ምንም ፍጡር አለመኖሩን ያረጋግጣል፡፡ ይህ ተግባርም ለአላህና ለክብሩ ተብሎ የሚደረግና የተቀደሱ የኢስላም ሥርዓቶችን ለማንሰራራት ኃይማኖቱን ለማጠናከር የሚተገብር መሆኑን ይረዳል፡፡

7. ሰባተኛ ደግሞ የነቢዩን ወይም የአንድን ኢማም መቃብር ከዘየረ በኋላ ዚያራ አድራጊው ቢያንስ ሁለት ረከዓዎች መስገድ አለበት፡፡ ይህ የሚደረገው አላህን ለማምለክ፣ ለማመስገንና ዚያራ የተሳካና ተቀባይነት ያለው እንዲሆን ለመለመን ነው፡፡ ከዚያም የፀሎቱ መንፈሳዊ ሽልማት (አጅር) በቦታው ለተቀበረው ነፍስ እንዲሆን አላህን መለመን አለበት፡፡

ቀጥሎ የሚቀርበው ዚያራ አድራጊው ሰላቱን ከጨረሰ በኋላ የሚቀራው ዱዓእ በዚያራ ወቅት የሚተገበሩ የአምልኮና የፀሎት ተግባራት ለአላህ ብቻ የተገቡና ከሱ ውጭ አምልኮ የሚገባው ምንም ነገር የሌለ መሆኑን ያሳያል፡፡ የአላህን ውዴታ የማግኘት መንገድ ብቻ መሆኑን እንረዳለን፡፡ ዚያራ አድራጊው እንዲህ ይላል፡-

( اللهم لك صليت ولك ركعت ولك سجدت وحدك لا شريك لك, لأنه لا تكون الصلاة والركوع والسجود إلا لك, لأنك أنت الله لا إله إلا أنت. اللهم صل على محمد وآل محمد, وتقبل مني زيارتي وأعطني سؤلي بمحمد وآله الطاهرين).

«*አላህ ሆይ! ለአንተ ብቻ እሰግዳለሁ ለአንተ ብቻ ሰገድኩም፣ ለአንተ ብቻ ሩኩዕ አደረግኩ፣ በአንተ ፊት ብቻ (በሱጁድ) ዝቅ አልኩ፡፡*

*አንተ አንድ ነህ!*

*አምሳያ የለህም፣*

*ከአንተ ውጭ ላለ ነገር መስገድ፣ ሩኩዕ መውረድና ሱጁድ ማድረግ ሀጢአት ነው፡፡*

*አላህ ሆይ! በነቢያችን በሙሐመድና በቤተ-ዘሩ ላይ ሰላትና ሰላምን አውርድ!*

*ዚያራዬን ተቀበለኝ፣ በሙሐመድና ከርክሰት ሁሉ ባጠራሃቸው ቤተ-ዘሩ ይሁንብህና ልመናዬን ተቀበለኝ፡፡*»

ይህ ዱዓእ፣ ማወቅ ለሚፈልጉ ሰዎች የዚያረተል ቁቡርን (*መቃብር የመጎብኘትን*) ዓላማና ተግባር በግልጽ ያስቀምጣሉ፡፡ በኢማሞቹና ተከታዮቻቸው ይደረግ

የነበረውን የመቃብር ጉብኝት ተግባራትንና ዓላማ ይገልጻሉ፡፡ ዚያራ በአላህ የማጋራት (ሽርክ) ተግባር ነው ብለው ለሚያስቡ ወገኖችና መካነ-መቃብሮችን መዘየር (መጎብኘት) መቃብሮቹን እንደመገዛትና ወደ ሙታን መቃረብ አድርገው ለሚያወናብዱ ቡድኖች የማያወላውል መልስ ይሰጣል፡፡

የእንዲህ ዓይነቶቹ አጥፊዎች ዓላማ ሺዓዎች እርስ በርሳቸው በመገናኘት የሚያገኙትን ጥቅም ለማዳከምና በዚያራው ወቅት የሚጠነክረውን አንድነታችን ለማፈን መሆኑ ጥርጥር የለውም፡፡ ምክንያቱም እንዲህ ዓይነቱ ወንድማማችነትና አንድነት በሙሐመድ ጠላቶች አይን የተደገነ ቀስት ሆኖ ነው የሚታያቸው፡፡ የኢማሞቹን ዓላማና አስተሳሰብ ጠንቅቀው ያውቃሉና፡፡ እያንዳንዱ ቃላቸውና ተግባራቸው ለአላህ የሆነና ለአላህ ኃይማኖት ብለው ደማቸውን ያፈሰሱ ሰዎች ወደ ሽርክ ተግባር ይጣራሉ ብሎ ማሰብ የማይመስል ነገር ነው፡፡

8. በመጨረሻ - በዚያራው ወቅት ከሚያስፈልጉ ነገሮች አንዱ ደግሞ «ዚያራ አድራጊው ሰው ሌሎች ዘያሪዎችን በትህትናና ክብር በተሞላበት መልኩ

መልካም ወዳጅነት ማሳየት አለበት፡፡ ቁም ነገርና አስፈላጊ የሆነ ነገር ከመናገር ውጭ ወሬ ማብዛት የለበትም፣ አላህን በብዙ ማስታወስ አለበት፡፡ አላህን በብዙ መፍራት አለበት፡፡ ሰላትንና በነቢዩና ቤተ-ዘሩ ላይ ሰለዋት ማውረድን ማብዛት አለበት፡፡ ዓይኖቹን ዝቅ አድርጎ መሔድ ይኖርበታል፡፡ በሌሎች ላይ እያፈጠጠና ሁሉን እየቃኘ መሄድ የለበትም፡፡ ድጋፍ የሚሹትን መርዳትና የተቸገሩትን ማጽናናት ይገባል፡፡ ከእኩይ ተግባራትና ከተከለከሉ ነገሮች መራቅ ይኖርበታል፡፡ ስለእምነትና አስተሳሰብ አንስቶ መጨቃጨቅና መጣላት ፍጹም አያስፈልግም፡፡»

(*አላህን ማስታወስ ስንል በቃላትና በአንደበት እያወሳን መናገር ብቻ አይደለም፡፡ ለምሳሌ «ሱብሃነላህ ወል ሐምዱ ሊላህ» (ለአላህ ጥራት ይገባው፣ ምስጋና ሁሉ ለአላህ ነው) በማለት ደጋግመው ማሰማት ብቻ አይደለም፡፡ አላህን ማስታወስ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ኢማም ጀዕፈር አል-ሳዲቅ (ዐ.ሰ) ሲገልጹ፡- «ሱብሀነላህ፣ ወል ሐምዱ ሊላህ፣ ወላ ኢላሀ ኢለላህ፣ ወላሁ አክበር» ማለት አላህን የምናስታውስባቸው መንገዶች ቢሆኑም እንዲህ ብቻ ብለን አንተውም፡፡ ይልቁንስ እሱን መታዘዝ ላይ ሆነህም ሆነ ጥፋት ላይም ሆነህ አላህን በሁሉም ቦታዎችና ጊዜያት ማስታወስ አለብህ፡፡*)

በዚያራው ጀርባ ያለው እውነቱ ሌላ ሳይሆን ለነቢዩና ለኢማሙ ሰላምታ ማቅረብ ነው፡፡ ይኸውም በቁርአን መሠረት፡-

بَلْ أَحْيَاءٌ عِنْدَ رَبِّهِمْ يُرْزَقُونَ

«*ከጌታቸው በሆነ ሲሳይ የሚስተናገዱ ህያዋን ናቸው፡፡*» (3፡168) የተባሉ በመሆናቸው የዘያሪውን ድምጽ በመስማት ለሰላምታው ምላሽ ይሰጣሉ፡፡ ለምሳሌ በነቢዩ መቃብር ፊት «አስ-ሰላሙ ዓለይከ ያረሱለላህ» (የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ሰላም በአንቱ ላይ ይሁን) ማለት በቂ ነው፡፡ ነገር ግን በነቢዩ ቤተ-ዘሮች (አህለል ቤይት) የታዘዙትን ቃላት መጠቀም የተሻለ ነው፡፡ ምክንያቱም የአህለል ቤይቱ ዱዓዎች የመጠቀ ኒያህ የሚገልጹ፣ በተዋበ ቋንቋ ጥልቅ የሆኑ ኃይማኖታዊ ጉዳዮችን የሚያስታውሱና ዘያሪው ስለአላህ ተፈኩር የሚያደርግበት እጅግ ምርጥ ዱዓዎች ስለሆኑ ነው፡፡

## 37. የ«ሺዓ» ትርጉም በነቢዩ ቤተ-ዘሮች እይታ

የአህለል ቤይት ኢማሞች (ዐ.ሰ) ከመሪነት ከተገለሉ በኋላ መሪነቱን መልሰው ለመውሰድና ለማስመለስ ፍላጎት

አልነበራቸውም፡፡ በመሆኑም አላህ ባዘዛቸው መሠረት ሙስሊሙን ህብረተሰብ በትምህርት በማነጽና በማቅናት ተግባር ላይ ጊዜያቸውን ሰውተው አሳለፉ፡፡ ለነሱ ታማኝ ከሆኑት ሰዎች ጋር ብቻ ለመሆን በቁ፡፡ ለታማኝ ተከታዮቻቸው ምስጢራቸውን አካፈሉ፣ እነሱን ለማስተማርና ለማነጽ፣ ሁሉንም ኃይማኖታዊ ትዕዛዛትና መመሪያዎችን ለማስተማርና ኃይማኖታዊ ዕውቀትን በውስጣቸው ለማስረጽ እንዲሁም ለሰው ልጅ የሚበጀውንና የማይበጀውን ለይተው እንዲያውቁ ለማድረግ ብዙ ችግርና መከራን አሳለፉ፡፡ አንድ ሰው የአላህን ትዕዛዛት ተቀብሎ ካልተገበረ በስተቀር፣ ከግል ፍላጎቱና ስሜቱ ተላቆ ያስተማሩትንና የጠቆሙትን ነገር ካልተገበረ እንጂ ማንንም ሰው «ሺዓ» ወይም ተከታያቸው አድርገው ቆጥረው አያውቁም፡፡ አንድ ሰው እነሱን በመውደዱ ብቻ ሊድን አይችልም፡፡ ያ ሰው ስሜቱን የሚከተል ከሆነና አላህን ባለመታዘዙ ሰበባ ሰበብ በመፈለግ የሚጽናና ዓይነት ሰው ከሆነና አስተምህሮ-አቸውንና መንገዳቸውን የማይከተል ከሆነ እነሱን መውደዱና ስሙ ብቻ አይፈይደውም፡፡ ምክንያቱም በመልካም ምግባራትና ንጹህ ሥራዎች፣ በሐቅ፣ በቅንነት፣

በአላህ ፍራቻና በበጎ ስብዕና ካልታጀበ በስተቀር ፍቅር ብቻውን ፋይዳ እንደሌለው በግልጽ አስቀምጠዋልና፡፡

ኢማም ባቂር (ዐ.ሰ) ሲናገሩ፡-

«*ኸይሰማ ሆይ! ሥራው ጥሩ የሆነ ሰው በስተቀር በአላህ ፊት ምንም ልንፈይዳቸው እንደማንችልና በበጎ ምግባራቸው ካልሆነ በቀር ወዳጅነታችንን (ዊሊያችንን) እንደማያገኙ ንገራቸው፡፡ ራሳቸውን በአድል (ፍትሐዊነት) በመሰየም ነገር ግን በተግባር ለመተርጎም ያልቻሉ ሰዎች በላይ የቂያማ ቀን ቁጭትና ሐዘን የሚገጥመው ሰው እንደሌለ አሳውቃቸው፡፡*»

(ኡሱል አል-ካፊ፣ ኪታቡል ኢማን፣ ባብ ዚያረተል አኽዋን)

ኢማሞቹ ተከታዮቻቸው ሌሎችን ሰዎች ወደ ቅን መንገድ እንዲመሩና የመልካም ምግባራትን መንገድ እንዲጠቁሙ አጥብቀው ይመኙና ይህንኑ ከህዝቡ ይጠብቁ ነበር፡፡ ሕዝቡን በቃላት ብቻ ሳይሆን በተግባር እንዲሳዩና እንዲያስተምሩ ያዙ ነበር፡፡ በቃላት ከመስበክ ይልቅ በተግባር ማሳየት ትክክለኛ አካሄድና ውጤታማ እንደሆነ አበክረው ይመክሩ ነበር፡፡

«በአንደበታችሁ ብቻ ሳይሆን በመልካም ሥነ-ምግባርና በበጎ ነገር ህዝቡን ወደ እውነት የምትጠሩ ሁኑ! በዚህ መልኩ ታዛዥነታችሁንና እውነተኝነታችሁን አስመስክሩ፡፡» (ቀደም ሲል የተገለጸው ምንጭ፣ ባብ አል-ወረዕ)

ቀጥሎ ኢማሞቹ ህዝቡን ለማስተማር ያላቸውን ጉጉት አንባቢው ይገንዘብ ዘንድ በኢማሞቹና በተከታዮቻቸውን መካከል የተደረጉ ቃለ-ምልልሶችን በመቀነጫጨብ እናቀርባለን፡፡

1. ኢማም ባቂር ከጃቢር አል-ጁዕፊ ጋር ካደረጉት ንግግር፡-

«ጃቢር ሆይ! እራሱን የኛ ተከታይ አድርጎ የሚቆጥር ሰው እንዴት አድርጎ ነው እኛን በመውደዱ ብቻ መርካት የቻለው? በአላህ እምላለሁ፣ የኛ ተከታዮች (ሺዓዎቻችን) አላህን የሚፈሩና የሚታዘዙ እንጂ ሌላ አይደሉም፡፡ መለያቸውም መተናነስ፣ የአላህ ፍራቻ፣ ታማኝነት፣ አላህን በብዙ ማስታወስና መዘከር፣ ጾም፣ ሰላት፣ ለደኃዎች፣ ለተቸገሩትና ለወላጅ አልባዎች ማዘንና መርዳት፣ እውነት

መናገር፣ ቁርአን መቅራት፣ ሰዎችን በበጎ ካልሆነ በስተቀር በክፉ አለመናገር፣ ለቀረቧቸው ሰዎች በማንኛውም ነገር ታማኝና አማና ጠባቂ መሆን ናቸው፡፡ (እናንተ ተከታዮች ሆይ!) አላህ ጋ ላለው ነገር (ለሽልማቱና ለውዴታው) መልካም ሥራን ሥሩ፣ ፍሩትም፡፡ እነሆ አላህ ፊት አንዱ ከሌላው የሚሻልበት ነገር የለም - አላህ ዘንድ የዝምድና ቅርበት የለም፡፡ አላህ ዘንድ ተወዳጁና በላጩ አገልጋይ ለሱ ይበልጥ ታዛዥ የሆነና ይበልጥ እሱን የሚፈራ ነው፡፡»

(ተመሳሳይ ሐሳብ ላይ አሚረል ሙዕሚኒን ዓሊ (ዐ.ሰ) «አል-ቃሲዓህ» በተሰኘው ንግግራቸው ውስጥ ሊገልጹ፡- «*የአላህ ትዕዛዛትና ፍርድ በምድር ላይ ላሉትም ሆነ በሰማይ ላይ ላሉት እኩል ነው፡፡ አላህ የከለከለውን ድንበር ያልፍ ዘንድ በአላህና በባሪያው መካከል ለአንዱ የተለየና የተሻሻለ ህግ ሊኖር አይችልም፡፡*»)

«ጃቢር ሆይ! ለሱ በመታዘዝ በማደር ካልሆነ በስተቀር ወደ አላህ የሚቃረብ የለም፡፡ በዚህ ካልሆነ ከጀሀነም ቅጣት የሚድን የለም፣ በአላህ ፊት የሚቀርብም

ማስተባበያና አቤቱታ የለም፡፡ አላህን የሚታዘዝ ወዳጃችን ነው፣ እሱን የማይታዘዝ ደግሞ ጠላታችን ነው፡፡ በመልካም ሥራና በጎ ሥነ-ምግባር ካልሆነ በስተቀር የኛን ወዳጅነት ማግኘት የለም፡፡

2. ኢማም ባቂር ከሰዒድ ኢብን አል-ሐሰን ጋር ካደረጉት ንግግር፡-

ኢማም፡ «*አንድ ሰው ገንዘብ ቸግሮት አንዱ ወንድሙን በመቅረብ በዛ ወንድሙ ኪስ ውስጥ እጁን አስገብቶ ገንዘቡን ሲወስድ ባለ ገንዘቡ ወንድም ወሳጁን የማይከለክልበት ሁኔታ አጋጥሞህ ያውቃል?*»

ሰዒድ፡- «*እንዲህ ዓይነት ነገር አጋጥሞኝ አያውቅም፡፡*»

ኢማም፡ «*እንዲህ ከሆነ በእርግጥ ምንም ነገር በመካከላችሁ የለማ!*»

ሰዒድ፡ «*ታዲያ በዚህ ጉዳይ የተነሳ ለጥፋት እንዳረጋለን ማለት ነው?*»

ኢማም፡ «*በእርግጥ አዎ! እንዲህ ዓይነቶቹ ሰዎች የሚናገሩትን ነገር በተግባር ላይ ያላዋሉ ናቸውና፡፡*»

3. ኢ.ማም ጃዕፈር አል-ሳዲቅ ከአቢ. አስ-ሰባህ አል-ከናኒ ጋር ካደረጉት ንግግር፣

አል-ከናኒ፡ «*እንዲያው ለአንተ ብለን ስንት መከራ አየን?*

ኢ.ማም ጃዕፈር፡ «*ምነው፣ ምን ችግር ገጠመህ?*»

አል-ከናኒ፡ «*በኛና በነሱ መካከል የሆነ ነገር በተነሳ ጊዜ ፈጥነው ጃዕፈሪዎች መጥፎ ናቸው እያሉ ይወቅሱናል፡፡*»

ኢ.ማም ጀዕፈር፡ «*በኔ የተነሳ ሰዎች ይወቅሱናል ነው የምትለኝ?*»

አል-ከናኒ፡ «*አዎ! በጣም እንጂ፡፡*»

ኢ.ማም ጃዕፈር፡ «*በነገራችን ላይ ከናንተ ውስጥ የኔ ትክክለኛ ተከታዮች በጣም ጥቂት ናቸው፡፡ ታላቅና እውነተኛ ስብዕናና ምግባር ያላቸውና ተግባሮቻቸውን ሁሉ ለአላህ ብቻ ብለው የሚሰሩ ሰዎች ብቻ ናቸው የኔ ተከታዮች፡፡ የሥራቸውን ውጤት ሽልማት ከአላህ ብቻ ለማግኘት ብለው ለሱ ያደሩ ናቸው የኔ ተከታዮች፡፡*»

4. ይህንን ጉዳይ አስመልክቶ ከኢ.ማም ጃዕፈር የተነገሩ በርካታ ሐዲሶች አሉ፡፡ ጥቂቶችን ብቻ መርጠን እንደሚከተለው አስቀምጠናል፡፡

- አንድ ሰው አንድ መቶ ሺህ ነዋሪዎች ባላት ከተማ ውስጥ የሚኖር ከሆነና ከዛች ከተማ ነዋሪዎች አንዱ ሰው በመልካም ምግባርና ስብዕናው ከዛ ሰው የሚበልጥ ከሆነ የሰው የኔ ተከታይ አይደለም፡፡

- መመሪያዎቻችንን በሙሉ የሚቀበልና የሚታዘዝ ካልሆነ በስተቀር ማንንም ሰው ከአማኞች አባል አድርገን አንቆጥርም፡፡ ጽድቅ የተከታያችን መለያ ስለሆነ እራሳችሁን በጽድቅ በመልካም ምግባር አንዱ፣ የአላህ ምህረት ለናንተ ይሁንና፡፡

- ጨዋነቱና ከማይፈቀድ የጾታ ግንኙነት የመታቀቡ ጉዳይ በሴቶች ውስጥ የመነጋገሪያ አጀንዳ ለመሆን ያልበቃ ሰው የኛ ተከታዮች አባል አይደለም፡፡ አሥር ሺህ ሰዎች በሚኖሩበት ከተማ ውስጥ የሚኖር አንድ ሰው ከነዋሪዎቹ ውሰጥ አንድ ሰው በጽድቅ የሚበልጠው ከሆነ ያሰው የኛ ተከታይ አይደለም፡፡

- የጃዕፈር ትክክለኛ ተከታይ ሆዱንና ሥጋዊ ፍላጎቱን የማያዳምጥ፣ በኢስላም መንገድ ላይ የሚታገል፣ የአላህን ሽልማት ብቻ በማሻትና ቅጣቱን ብቻ

በመፍራት ማንኛውንም ነገር ለአላህ ብቻ ብሎ የሚያደርግ ሰው ነው፡፡ አዎ! በእርግጥ የጃዕፈር ተከታዮች እነዚህ ናቸው!

## 38. በደልና ጭቆናን አስመልክቶ ያለን እምነት

በኢማሞቹ እምነት መሠረት በሰው ልጆች ውስጥ ከሚከሰቱ የከፋ ሐጢአቶች አንዱ በሰው ልጆች መካከል የሚፈጸም የርስ በርስ ጠላትነትና በደል ነው፡፡ በቁርአን ውስጥም እንዲህ ይጠቀሳል፡-

وَلَا تَحْسَبَنَّ اللَّهَ غَافِلًا عَمَّا يَعْمَلُ الظَّالِمُونَ إِنَّمَا يُؤَخِّرُهُمْ لِيَوْمٍ تَشْخَصُ فِيهِ الْأَبْصَارُ

«*አላህንም በደለኞች ከሚሠሩት ግፍ ዘንጊ አድርገህ አታስብ፡፡ የሚያቆያቸው ዓይኖች በእርሱ እስከሚፈጡበት ቀን ድረስ ብቻ ነው፡፡*» (14፡42)

እንዲሁም አሚረል ሙዕሚኒን ዓሊ (ዐ.ሰ) ሲናገሩ በጭቆናና በደል ላይ ያላቸውን ጥላቻና ተቃውሞ እንዲህ ይገልጹታል፡፡

*«በአላህ እምላለሁ! የምድር አህጉራትና ከፀሐይ በታች ያለው ነገር በሙሉ አላህ ፊት ሀጢአት እንድሰራ ቢሰጠኝ፣ ከአንዲት ጉንዳን አንዲት የገብስ ፍሬ መስረቅ እንኳን ብትሆን አላደርገውም፡፡»*

ይህ የሚያሳየው በደል መፈጸም ምን ያህል እርኩስ ነገር እንደሆነና የሰው ልጅ ከዚህ ጉዳይ እራሱን ለመጠበቅ ምን ያህል መጠንቀቅ እንዳለበት ነው፡፡ «የመሬት ሀብት በሙሉ ቢሰጠው እንኳ አንዲት የገብስ ፍሬን በመስረቅ አንዲት ጉንዳንን መበደል እንደማይሞክር ዓሊ ይነግረናል፡፡» ታዲያ የሙስሊሞችን ደም በከንቱ የሚያፈስ፣ ንብረታቸውን እንደፈለገ የሚበዘብዝና የሚዘርፍና ክብራቸውን የሚያዋርድና የሚያቋንሽሽ ሰው ቦታው ምን ይሆን? ከዓሊ ጋር እንዴት አድርጎ እራሱን ያወዳድር? ከዓሊ ጥበብ ጋር ሲነጻጸር ቦታው የት ይሆን? በእርግጥም የዓሊ ስብዕናና ጽድቅ ኢስላም በሰው ልጆች ውስጥ ሊያሰርጽ የሚፈልገው አንጸባራቂ የኃይማኖታዊ ትምህርት ድንቅ ተምሳሌት ነው፡፡

ስለዚህ በደልና ጭቆና አላህ ከከለከላቸው ታላላቅ ሐጢአቶች አንዱ ነው፡፡ ለዚህም ነው የነቢዩ ቤተ-ዘሮች (አህለል ቤይት) በቃላቸውና በዱዓዎቻቸው ተከታዮቻቸውን ከምንም በላይ በዚህ ጉዳይ ላይ ያስጠነቀቁት፡፡ እንዲህ ነበር የእነሱ ፓሊሲና ባህሪ፡፡ ለወዳጆቻቸው ብቻ ሳይሆን ክብር ለነፈጉዋቸውና መጥፎ ሁኔታ ላደረሱባቸው ወገኖችም ቅንና ፍትሓዊ ነበሩ፡፡

እዚህ ላይ ኢማም ሐሰን የሻም (ደማስቆ) ሰው በሰደባቸው ጊዜ ያሳዩት ትዕግሥትና ቻይነት አብዛኛውን ጊዜ ይጠቀሳል፡፡ በዚህ ወቅት ሰውየው ስህተቱን ይረዳ ዘንድ በለዘበ አንደበትና በትህትና አናገሩት፡፡ *(ከዕለታት አንድ ቀን ኢማም ሐሰን ፈረሳቸው ላይ ሆነው በጉዞ ላይ ሳሉ አንድ የደማስቆ ሰው ሰደባቸው፡፡ ኢማም ሐሰን ግን ምንም ምላሽ ሳይሰጡ ዝም አሉት፡፡ ሰውየው ስድቡን ከጨረሰ በኋላ ኢማሙ ሰውየው አየት አድርገው ፈገግ በማለት እንዲህ አሉት፡- «ወንድም! እንግዳ ነህ መሰለኝ፣ ስለኛም የተሳሳተ አመለካከት ያለህ ይመስለኛል፡፡ ወቀሳም ሆነ ምክር ካለህ የምትለውን ለመቀበል ዝግጁ ነን፣ የምትፈልገው ነገር ካለም እንሰጠሃለን፣ መመሪት የምትፈልግም ከሆነ እናመራሃለን፣ መጓጓዣ የምትፈልግ ከሆነም እንረዳሃለን፣ ርቦህም ከሆነ እናበላሃለን፣ ልብስም ከሌለህ እናለብስሃለን፣ የፈለግከውን እንሰጠሃለን፣ መጠጊያ/መጠለያ ከሌለህም እናስጠጋሃለን፣ የሆነ*

*ዓላማም ካለህ እንረዳሃለን፣ እንግዳችን ሆነህ እስከፈለግክበት ጊዜ መቆየት ከፈለግክም ጥሩ ሐሳብ ነው፤ ምክንያቱም ብዙ አገልጋዮችንና አስተናጋጆችን ጨምሮ በቂ ንብረትና ሲሳይ በእጃችን አለ፡፡» ሰውየው ይህንን ሲሰማ ለቅሶውን መቆጣጠር አቅቶት እያነባ እንዲህ አለ፡- «በምድር ላይ የአላህ ዘኪ (ኸሊፋ) መሆንህን በሙሉ ልቤ እመሰክራለሁ፡፡ አላህ መልዕክቱን የት ማድረግ እንዳለበት በእርግጥ ያውቃል፡፡ አንተና አባትህ እጅግ ከምጠላቸው ሰዎች ውስጥ የመጀመሪያዎቹ ነበራችሁ፡፡ አሁን ግን ለኔ እጅግ ተወዳጅ የሆናችሁ ፍጡራን ናችሁ፡፡»*

*ሻንጣውን ወደ ኢማሙ ቤት በመውሰድ ጉዞውን እስከቀጠለበት ጊዜ ድረስ እንግዳቸው ሆኖ ቆየ፡፡ በኢማሞቹ አመነ፣ ወደዳቸውም፡፡)*

**ቀደም ሲል በኢማም አስ-ሳጂዲን ዱዓእ ውስጥ እንዳነበብከው ኢማሙ ለበደላቸውና ክብራቸውን ለነካ ሰው እንኳ የአላህን ይቅርታ ሲማጸኑለት አይተሃል፡፡ ይህ ወደር የለሽ ርህራሄና የመጠቀና የተቀደሰ አዕምሮ የተቸረው ፍጹም የሆነ ሰው የሚጎናጸፈው ድንቅ ጥበብ ነው፡፡ በኢስላም ውስጥ አንድን ሰው በበደለን መጠን የመበቀል በአላህ ፊት የመራገም መብት ቢኖርም ከመበቀል ይልቅ ይቅር ማለት ይበረታታል፡፡ ይቅርታ ማድረግ የመልካም ስብዕናና ጽድቅ መገለጫ ነውና፡፡ በእርግጥ በኢማሞቹ መሠረት አንድን የበደለን ሰው መራገም ራሱ ሌላ በደል መፈጸም እንደሆነ ይቆጥራሉ፡፡**

ኢ.ማም ሳዲቅ (ዐ.ሰ) ሲናገሩ፡-

*«እውነት እላችኋለሁ፣ አንድ ባሪያ ጨቋኝ ጌታውን ከመራገም እስከታቀበ ድረስ በጭቆና ሥር ነው፡፡ ነገር ግን የሚራገም ከሆነ እራሱ ጨቋኝ ይሆናል፡፡»*

ይህ እንዴት ድንቅ አባባል ነው! ጨቋኝን መራገም በራሱ የጭቆና ተግባር ከሆነ፣ እነዛ በደልና ጭቆናን የሚያራምዱ፣ በሰዎች ላይ የኃይል እርምጃ የሚወስዱ፣ ክብራቸውን የሚያጎናጽፉ፣ ንብረታቸውን የሚዘርፉ፣ በጨቋኞችና በዳዮች ፊት የሚኮንኑ፣ ለጥፋትና ጉዳት እንዲዳረጉ የሚያታልሉና የሚያጭበረብሩና የሚሰልሉ ሰዎች ምን ሊባሉ ነው? ከኢ.ማሞቹ ጥበብ አንጻር ቦታቸው የት ሊሆን ነው? በእርግጥ እንዲህ ዓይነቶቹ ሰዎች ከአላህ ምህረት እጅጉን የራቁ ናቸው፡፡ ስብዕናቸውና ምግባራቸው አስከፊ እንደነበረ ሁሉ ቅጣታቸውም እጅግ አሰቃቂ ይሆናል፡፡

## 39. ከጨቋኞች ጋር መተባበርን አስመልክቶ ያለን እምነት

ጭቆና እጅግ አደገኛ ነገር ስለሆነና እርኩስ የሆነ ውጤት ስላለው አላህ የሰው ልጆች ከጨቋኞች ጋር እንዳይተባበሩና እንዳይወዳጁ ያስጠነቅቃል፡፡
አላህ እንዲህ ይላል፡-

وَلَا تَرْكَنُوا إِلَى الَّذِينَ ظَلَمُوا فَتَمَسَّكُمُ النَّارُ وَمَا لَكُمْ مِنْ دُونِ اللَّهِ مِنْ أَوْلِيَاءَ ثُمَّ لَا تُنْصَرُونَ

«*ወደእነዚያም ወደ በደሉት አትጠጉ፡፡ እሳት ትነካችኋለችና፡፡ ከአላህም ሌላ ጠባቂዎች የሏችሁም፡፡ ከዚያም አትረዱም፡፡*» (11፡113)

የነቢዩ ቤተ-ዘሮች ያስተማሩን ይህንን ነው፣ አስተምህሮዎቻቸው ከቁርአን ጋር አንድ ነው፡፡ የተምር ግማሽን መስጠት ቢሆን እንኳ ከጨቋኞችና በዳዮች ጋር በምንም መልኩ የሚወዳጁና በምንም ሁኔታ የሚተባበሩና ድጋፍ የሚሰጡ ሰዎች ላይ ኃይለኛ የሆነ ተቃውሞና ጥላቻ እንደነበራቸው ይነገራል፡፡ በእርግጠኝነት ለመናገር

ኢስላምንና ሙስሊሙን የከፋ እጣ ፋንታ ያጋጠመበት ትልቁ ምክንያት ከጨቋኖቹ ጋር መተባበርና ከነጭቆና ተግባሮቻቸው ደህንነት ማላበስና ጥብቅና መቆሙን ሆድ ይፍጀው ብለን ብናልፍ እንኳ የጨቋኞችን ክፉ ተግባራት በተመለከተ ጽኑ አቋም በመነፈጋቸውና ከጨቋኞቹ ጋር የፈጠሩት ትስስር ያመጣው መዘዝ ነው፡፡

ለሙስሊሞች ድክመትና ኋላቀርነት መንስኤ ከኢስላም ትክክለኛ ጎዳና ከማፈንገጣቸው የባሰ ሌላ ምክንያት የለም፡፡ በዚህ የተነሳ ኃይማኖቱ ኃይሉን ያጣና ቀን በቀን እያሽቆለቆለ ይሄዳል፣ የማታ ማታ ለህዝቡ ባዳና እንግዳ ሆኖ ይቀርባል፡፡ በዚህ መልኩ ሙስሊሞች ወይም ራሳቸውን ሙስሊም ብለው የሚጠሩ ወገኞች አቅም አልባ ይሆኑና ከአላህ ጥበቃ እየራቁ የሚኖሩትን እንደ አይሁዶች ያሉና እዚህ ግቡ የማይባሉ ደካማና ጥቃቅን ጠላቶቻቸውን እንኳ መጋፈጥ ይሳናቸዋል፡፡

በተቻለው መጠን ኢማሞቹ፣ ባልደረቦቻቸውና ዘመዶቻቸው ከጨቋኞች ክፍል ጋር እንዳይተባበሩና ምንም ድጋፍ እንዳይሰጡ አጥብቀው ይከለከሉ ነበር፡፡

ይህንን በተመለከተ የሐዲስ ተራኪዎች ስፍር ቁጥር የለሽ ሐዲሶችን ተርከዋል፡፡ ከነዚህ ውስጥ ኢማም ዘይን አል-ዓቢዲን (ዐ.ሰ) ለሙሐመድ ኢብን ሙስሊም አዝ-ዙሐሪ የጻፉት መልዕክት ነው፡፡ ምንም ዓይነት የበደል ተግባር እራሱ እንዳይፈጽም ካስጠነቀቁት በኋላ ከጨቋኞች ጋር መተባበርን አስመልክተው የሚከተለውን መልዕክት ጻፉለት፡-

«ከአንተ የሚፈልጉት ነገር ሌላ ሳይሆን እንደ ወፍጮ ሊጠቀሙብህ ነው፡፡ ወደ እርኩስ ዓለማቸው የሚሻገሩበት ድልድይ ሊያደርጉህ ነው፣ ለወጠኑት ደባና አሻጥር መሰላል እንድትሆንላቸው ነው፡፡ ለወንጀሎቻቸው ወኪልና ቀስቃሽ ሊያደርጉህ ነው፡፡ በአንተ አማካይነት አሻጥራቸውን ከአዋቂዎች ሊደብቁና የማኃይማንን ልብ ሊሰርቁ ነው፣ ታዋቂ ሚኒስትሮቻቸውም ሆኑ ጠንካራ ረዳቶቻቸው አንተ ጥፋታቸውንና ተንኮላቸውን የምትሸፍንላቸውን ያህል ሊሰሩ አይችሉም፡፡ የሰጡህ ነገር ከአንተ ከወሰዱት ግዙፍ ነገር ጋር ሲነጻጸር ምንኛ ኢምንት ነው! ያደረጉብህ ነገር ካደረጉልህ ነገር ምንኛ የከፋ ነው! ራስህን ጠብቅ፣ ነፍስህን የሚጠብቅልህ ሌላ

ሰው የለምና፡፡ ኃላፊነት የሚሰማው ሰው የሚያስበውን አስብ፣ ነፍስህን መርምራት!»

«ሓሲብሃ ሒሳበ ረጁል መስኡል» (ኃላፊነት የሚሰማው ሰው የሚያስበውን አስብ፣ ነፍስህን መርምራት) የሚለው አባባል እንዴት ድንቅ ነው! ምክንያቱም የሰው ልጅ በስሜቱ ከተሸነፈና ለስጋዊ ፍላጎቱ ከተዋረደ ከሰውነት ጎዳና ወጥቶ ወራዳ ፍጡር ይሆንና ለሚያደርጋቸው ነገሮች ኃላፊነት እንደሌለበት ይሰማዋል፡፡ የእኩይ ተግባራቱ እርኩስነት ሳይታየውና ሳይሰማው ቀርቶ ምንም እንዳላጠፋና እንደማይጠየቅበት ሆኖ ይሰማዋል፡፡ ይህ ያልተገራ የሰው ልጅ ነፍስ ሚስጢሮች አንዱ ነው፡፡

ኢማሙ ይህንን መንፈሳዊ ሚስጥር ነው አዝ-ዙሐሪን ማስታወስ የፈለጉት፡፡ ይህንን የባህሪው (የአዝ-ዙሐሪ) አካል የሆነውን ምስጢር በማሳወቅ አስተሳሰቡ እንዳይበከልና ኃላፊነቱን እንዳይዘነጋ ለማነቃቃት የሰጡት ታላቅ ትምህርት ነው፡፡

እላይ ከተጠቀሰው በበለጠ አስገዳጅ የሆነና ነገር ግን በተመሳሳይ ርዕስ ላይ የተደረገ ሌላው ንግግር ከኢማም ሙሳ አል-ካዚም የተገኘ ነው፡፡ ኢማሙ ከሰፍዋን አል-ጀማል ጋር ያደረጉት ንግግር ነው፡፡ የአል- ጀማልን የህይወት ታሪክ ያጠናቀረው አል-ኪሽሺ መሠረት ሰፍዋን ተከታያቸው (ሺዓቸው)ና የሐዲሳቸው ታማኝ ተራኪ ነበር፡፡

አል-ጀማል ኢማም ሙሳ ለመጠየቅ (ለመዘየር) በሄደ ጊዜ እንደሆነ ይነገራል፡፡

«*ሱፍያን ሆይ! ሥራህ ሁሉ ጥሩ ነው፣ ግን አንዷ ስትቀር፡፡*»

«*እኔ ለርስዎ ፊዳ ልሁንና እንዲያው ምንድን ነው ጥፋቴ?*»

«*ለዛ ለሐሩን ግመሎችህን የምታከራየው ነገር፡፡*»

«*በአላህ እምላለሁ! ይህን ያደረጉት ተንደላቆ እንዲኖር ፈልጌ አይደለም፣ አደን እንዲያድንበትና እንዲዝናና-በትም አስቤ አይደለም፣ ምናልባት ለሐጅ ወደ መካ እንዲጓዝበት ብዬ ነው፡፡ ደግሞ እኔ ከሱ ጋር አልሆንም፣ ግመሎቼንና ኃላፊነቱን ለአገልጋዮቼ ሰጥቼ ከነሱ ጋር የምልካቸው፡፡*»

*«ለግመሎቹ ይከፍላል አይደል?»*

*«አዎን!»*

*«ክፍያውን እስኪፈጽም ድረስ እንዲኖር ትፈልጋለህ?»*

*«አዎን!»*

*«እነሱ (ጨቋኞቹ) በህይወት እንዲኖሩ የሚመኝ ሰው በእርግጥ የነሱ አባል ነው፣ የጀሐነም እሳት ይገባልም፡፡»*

ሰፍዋን ወዲያው ሂዶ ግመሎቹን ሁሉ እንደሸጠ ይተርክልናል፡፡

ጨቋኞችና በዳዮች በህይወት እንዲኖሩ የሚመኝ ሰው መጨረሻው እንዲህ ከሆነ እነሱን የሚረዳቸው ሰው፣ ከነሱ ጋር የሚሳተፍ፣ ሥራቸውን የሚሰራላቸውና የሚታዘዛቸው ሰው መጨረሻው ምን ያህል የከፋ ይሆን?

## 40. በጨቋኝ መንግስት ሐገር ውስጥ መስራትን አስመልክቶ ያለን እምነት

ኢማሞቻችን የአንድ ተምር ፍሬ ግማሽ መስጠት ያህል እንኳ ቢሆን ጨቋኞችን ከመርዳትና በህይወት እንዲኖሩ መልካም ምኞት ከመመኘት እንኳ አጥብቀው

ስላስጠነቀቁን ከነሱ ጋር የሚተባበርና በመንግሥታቸው ውስጥ ተሳታፊ ሆኖ የሚሠራ ደግሞ ከዚህ የከፋ ማለት ነው፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ለነሱ ተቀጥሮ የሚሰራ ወይም ከግዛታቸው መሥራቾች አንዱ የሆነ ወይም መንግስታቸውን ለመጠበቅና ለመከላከል በታማኝነት ለመሥራት የበቃ ሰውም ከዚሁ ጎራ ይመደባል፡፡ ምክንያቱም፡-

«ለጨቋኝ መንግስት ታማኝ መሆን ማለት እውነትና እውነታን ሙሉ በሙሉ የሚጻረርና የሚደብቅ፣ እንዲሁም ሐሰትን፣ ጭቆናና በደልን፣ ሙስናን የሚሰብክና የሚያስፋፋ የወንጀለኛ ተቀጣሪ ወንጀለኛ ማለት ነው፡፡» ይህ ከኢማም ጃዕፈር አል-ሳዲቅ (ዐ.ሰ) የተነገረ ነው፡፡

ነገር ግን ከጨቋኞች ጋር መገናኘትም ሆነ በመንግስታቸው ውስጥ ተሳታፊ ሆኖ መሥራቱ ፍትህን ለማስፈንና የአላህ ትዕዛዛት ለመተግበር የሚያስችለን ከሆነና ለአማኞቹ አዎንታዊ ተጽእኖ ማምጣት የሚቻልበት ሁኔታ ከተፈጠረ እንዲሁም በጎ ተግባርን ለማበረታታትና ከእኩይ ተግባር መከልከልን የሚያመቻች

ሁኔታ የሚፈጠር ከሆነ በዚህ መልኩ ተሳትፎ ማድረጉን አስመልክቶ ኢማሞቻችን ፈቅደዋል፡፡

ኢማም ሙሳ (ዐ.ሰ) ሲናገሩ፡-

«*እውነት እላችኋለሁ፣ ከጨቋኞች ጋር ከተወዳጁ ሰዎች መካከል በነሱ አማካኝነት አላህ መንገዱን ብሩህ ያደረገባቸው ሰዎች አሉ፡፡ ወዳጆቹን የሚጠብቁበትንና የሙስሊሞቹን ችግር የሚፈቱበትን ኃይል ሰጣቸው፡፡ እነሱ በእውነት ካመኑ ሰዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ወደ አላህ የሚመሩ ቅኑን መንገድ አመላካቾችና በባሪያዎቹ ውስጥ ብርሃን ናቸው፡፡*»

የገዢዎችን ኃላፊነትና የመንግስት ሠራተኛ ሆነው የሚሰሩትን ሰዎች ግዴታና ኃላፊነት አስመልክቶ እንዲሁም ከመንግስታቱ ጋር ተስማምቶ የሚሰሩትን ሰዎችን በተመለከተ በርካታ ሐዲሶች ተነግረዋል፡፡ ለምሳሌ ኢማም ሳዲቅ (ዐ.ሰ) የአህወዝ ገዢ ለነበረው አብዱላህ አል-ነጃሺ የጻፉት ደብዳቤ ተጠቃሽ ነው፡፡ (ለዝርዝሩ አል-ወሳኢል፣ ኪታቡል ቤይዕ፣ ክፍል 78 ይመልከቱ)

## 41. ለኢስላማዊ አንድነት መጣራትን አስመልክቶ ያለን እምነት

በግል እንደሚታወቀው የነቢዩ ቤተ-ዘሮች (አህለል ቤይት) የኢስላም መገለጫዎችንንና ልዕልና እንደነበረ ለማቆየት፣ ሙስሊሙ ህዝብ ክብሩን መልሶ እንዲያገኝ በመጣራት፣ የእምነት አንድነታቸው እንዲጠበቅ ለማድረግ የተቻላቸውን ጥረት ሁሉ በማድረግ እንዲሁም ኢስላማዊ ወንድማማችነትን ለማስጠበቅና ከሙስሊሞች ልብ ውስጥ ደባና ጠላትነትን ለማስወገድ በጽኑ መታገላቸው በግንባር ቀደምትነት ይጠቀሳል፡፡

እዚህ ላይ ኢማም ዓሊ የኸሊፋነቱን ቦታ ቀድመው ከወሰዱት ተፎካካሪዎቹ ጋር በምን ሁኔታ እንዳሳለፈ ሳንጠቅስ አናልፍም፡፡ ለሱ የሚገባውን መብት ነጥቀው እንደወሰዱ ቢያምንም ጉዳዩን በተለየ አስተያየት ነበር የያዘው፡፡ ከነሱ ጋር በመስማማት ሰላምን በጠበቀ መልኩ በመቻቻል ዓይን ጊዜው እስከፈቀደ ድረስ ችሎ ቆየ፡፡ ለኸሊፋነቱ ቦታ ያለውን መብት በተመለከተ ቦታውን ለመቆናጠጥ እስከቻለበት ጊዜ ድረስ በአደባባይ ከመናቆር ታቀበ፡፡ ከዚያም የቀሩትን የነቢዩ ሰሃቦች (ነቢዩ ዓሊን

ኸሊፋ አድርገው በሾሙበት ወቅት ገዲር ላይ የነበሩና እስከዛ ጊዜ ድረስ በህይወት ለመኖር የበቁትን ሰሃቦች) ሰብስበው ኸሊፋ ሆኖ ስለመመረጡ እንዲመሰክሩ አደረ፡፡ ለኢስላምና፣ ለሙስሊም ይበጃል ያለውን ነገር ከመፈጸምና ሐሳብ ከመስጠት ወደ ኋላ ያለበት አንድም ሁኔታ አልነበረም፡፡ ብዙ ጊዜ እንዲህ ይል ነበር፡-

«*ኢስላምና ሙስሊሞችን የማልረዳ ከሆነ ለጥፋትና ውድመት ይዳረጋሉ ብዬ ሰጋሁ፡፡*»

የኹለፋዎችን ቦታ፣ ኃይልና ስልጣን በተመለከተ ምንም አላለም፣ ምንም አላደረገምም፡፡ ምን እየሰሩ እንደነበረ በግልጽ ያይ የነበረ ቢሆንም በቤቱ ውስጥ እራሱን ሰብስቦ በፀጥታ ማለፍን መረጠ፡፡ በድንቅ ባህሪውና እጹብ ስብዕናው አድናቆትን ማትረፍ እስኪችል ድረስ ለኢስላም ደህንነትና ፍላጎት ሲል በዚህ መልኩ ያንን ወቅት አሳለፈ፡፡ ሁለተኛው ኸሊፋ ኡመር ኢብን አል-ኸጣብ ብዙ ጊዜ እንዲህ ይል ነበር፡-

«*አቡ ሐሰን (ዓሊ) በቦታውም መፍትሔ ያልሰጠበት አንዳችም ችግር ኢጋጥሞኝ ኢያውቅም፡፡ አስቸጋሪ ጉዳይ በገጠመን ጊዜ ሁሉ ከእሱ መፍትሔ ያጣንበት ጊዜ*

የለምና፡፡ ዓሊ ባይኖር ኖሮማ ኡመር (እራሱ) በጠፋ ነበር፡፡»

ኢማም ሐሰን ከሙዓዊያህ ጋር የነበረውን ሁኔታ ታሪክ መርሳት አይችልም፡፡ ከሙዓዊያህ ጋር የሰላም ስምምነት ፈጠረ፡፡ ምክንያቱም በትግልና ውጊያ ከቀጠለ የቁርአን ብርሃንና ፍትሓዊ መንግስት እንደሚጠፉ ተረዳ፡፡ ከዚያም አልፎ የኢስላም ስም ከነአካቴው እንደሚጠፋ፣ መለኮታዊ ሸሪዓም እንደሚወድምና በቀጣይነት የሚነሱ ኢማሞችም እንደሚረሸኑ ከወዲሁ ተገንዝበው ነበር፡፡ ስለዚህ የኢስላምን ስምና ክብር ለማስጠበቅ መረጠ፡፡ በዚህ ምክንያት የኢስላምና ሙስሊሞች ቀንደኛ ጠላት ከሆነውና ኢማም ሐሰንና ተከታዮቹን እጅግ ይጠላ ከነበረው ሙዓዊያህ ጋር የሰላም ስምምነት አደረገ፡፡ በሱና በተከታዮቹ ላይ ሙዓዊያህ በደል እንደሚፈጽምባቸው ጠንቅቆ ያውቅ ነበር፡፡ ቤተሰቦቹና ተከታዮቹ ራሳቸውን ለመከላከል እንዲዋጉ ኃላፊነት መስጠት ብችልም የኢስላም ፍላጎት ከዚህ ሁሉ የላቀ በመሆኑና ከነሱ በላይ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ በመሆኑ ያንን ውሳኔ አልወሰደም፡፡

ሦስተኛው መሪ ቅዱሱ ሸሂድ ኢማም ሁሴይንም በበኒ ኡመያህ ላይ አምጾ የተነሳው በዚሁ ምክንያት ነው፡፡ በኒ ኡመያዎች በዛ አስጸያፊ ሥራዎች ከቀጠሉና ጥፋታቸው የሚያጋልጥ ኃይል ካልተነሳባቸው ኢስላምና ክብሩን ለማጥፋት እንደተነሱ ከወዲሁ ስለተረዳ ነው፡፡ ስለዚህ ጭቆናቸውንና በደላቸውን ይፋ ለማውጣትና የነቢዩን ኃይማኖት ለማጥፋት ያሴሩትን ደባ ለማክሸፍ ያንን ቆራጥ ውሳኔ ወሰደ፡፡ በእርግጥም የኋላ ኋላ ነገሮች ሁሉ እንደተጠበቁ ሆኑ፡፡ ያንን ቅዱስ ዘመቻ ባያደርግ ኖሮ ኢስላም ያለፉ ህዝቦች ኃይማኖት ተደርጎ ይዘገብ ነበር፡፡ የውሸት ኃይማኖት ተደርጎም ይታሰብ ነበር፡፡

ቅዱስ ዘመቻውን ማጠናቀቁን በጭቆናና በደል ላይ በማመጽ ለተቀደሰ ዓላማ የከፈሉትን መስዋዕትነት በመዘከር ኢማሞቹ ባስተማሩት መሠረት ሺዓዎች የከርበላን አሳዛኝ ታሪክ በተለያየ መልኩ በማስታወስና በማክበር ታሪኩ እንዲያንሰራራና ህያው ሆኖ እንዲኖር በየዓመቱ በማክበር ያሳልፉታል፡፡

የነቢዩ ቤተ-ዘሮች (አህለል ቤይት) የኢስላምን ክብር ለማስጠበቅ የከፈሉትን መስዋዕትነት ኃይማኖቱን ለመጠበቅ ምን ያህል እንደለፉና ጥረት እንዳደረጉ በግልጽና በሚገባ ለመረዳት ምንም እንኳ ቤተሰባቸው ቢገደሉባቸውና ክብራቸው ቢዋረድም ኢማም ዘይነል ዓቢዲን የኡመያድ ነገሥታትን በምን መልኩ ይቀርቡ እንደነበርና ከነሱ ጋር የነበራቸውን ግንኙነት በጥልቀት ማጤን ተገቢ ነው፡፡ በአባታቸው ሞትና በቤተሰቡ በሙሉ ላይ የደረሰውን ስቃይና ሰቆቃ እያስታወሱ ሁሌም ልባቸው እየደማ የኖሩ ቢሆንም ይህንን ሁሉ በመቻልና በማለፍ የሙስሊሞቹ ጭፍራ ሁሌም ድል እንዲቀናው ይፀልዩ ነበር፡፡ የኢስላም ክብር እንዲጠበቅና ሙስሊሞቹ በደህንነት ውስጥ እንዲኖሩ በሚስጥር ወደ አላህ ይፀልዩ ነበር፡፡ የኢስላም ዕውቀትን ያስፋፉና በፀሎት ብቻ ተከታዮቻቸውን እምቅ ዕውቀት ያስጨበጡና ተከታዮቻቸው ለሙስሊሞች ድል ተግተው እንዲፀልዩ አጥብቀው ያስተምሩ ነበር፡፡ ለኢስላም ድንበር ጠባቂዎች በታወቀው ዱዓቸው (ፀሎታቸው) እንዲህ በማለት ይፀልዩ ነበር፡-

አላህ ሆይ! በሙሐመድና በቤተ-ዘሩ ላይ ሰላምና በረከት አውርድ፡፡ ዘራቸውን አብዛ፣ ቁጥራቸውን አሳድግ፣ ጎራዴያቸውን የሰላ አድርግላቸው፣ መኖሪያቸውንና መቀመጫቸውን ጠብቅላቸው፣ አገራቸውን ጠብቅላቸው፣ በመካከላቸው ወዳጅነት እንዲያብብ አድርግላቸው፣ ሥነ-ምግባራቸውንና ፀባያቸውን የላቀ አድርግላቸው፣ ለኑሮ የሚሆን በረከትና የዕለት ጉርስ አብዛላቸው፣ እርዳቸው፣ ትዕግሥት አጎናጽፋቸው፣ የብልጦችና የጉብዝና መንገድ አስተምራቸው፡፡ (በከሃዲዎች ላይ የአላህ እርግማን እንዲወርድ ከፀለዩ በኋላ)

አላህ ሆይ! በዚህ መልኩ የኢስላም ህዝቦችን አጠንክር፣ መሬታቸውን ተከላከልላቸው፣ ንብረታቸውን ባርክ፡፡ በግልና በሚስጢር ያመልኩህ ዘንድ የኢስላም ወታደሮችን ከጦርነት ነፃ አድርጋቸው፣ በምድር ላይ ከአንተ ውጭ ሌላ የሚመለክ ነገር አይኑር፣ በአንተ ፊት እንጂ የሚያጎበድድ አንዳችም ነገር አይኑር፡፡

ከዚያም ዱዓቸውን በመቀጠል (ከዱዓዎቹ ረዥሙ የሆነውን) የሙስሊሙ ጭፍራ ኃላፊነት ምን መሆን

እንዳለበት፣ ፀባያቸውና ምግባራቸው ምን መሆን እንዳለበትና እንዴት መልካም ባህሪይ ሊኖራቸው እንደሚገባ እንዲሁም ጥሩ ትጥቅ ሊኖራቸው እንደሚገባ በዝርዝር አወሱ፡፡ ይህ ዱዓእ ቅዱስ ትግልን (ጂሐድ) አስመልክቶ ያሉትን ግንዛቤዎች፣ ዓላማና ውጤቱን፣ ሙስሊሞች ከጠላቶቻቸው እንዴት መጠንቀቅ እንዳለባቸው፣ ጥቃትን እንዴት መከላከልና እራሳቸው መጠበቅ እንዳለባቸው ያሉትን መመሪያዎችና ህግጋትን ያካተተ ነው፡፡ በተጨማሪም ግዴታቸውን አስመልክቶ ያሉትን መመሪያዎች በመጠቆም ሙስሊሞች ምንጊዜም አላህን ማስታወስ እንዳለባቸው፣ ከማንኛውም እኩይ ተግባር መራቅ እንዳለባቸውና ጂሐዱን ለአላህ ብለው በጥራት መፈጸም እንዳለባቸው በማተት በዱዓ አማካይነት ታላቅ ትምህርት ሰጥተዋል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ ምንም እንኳ በዘመኑ በነበሩ ነገሥታት አሳዛኝ ጭቆናና ሰቆቃ ቢደርስባቸውም፣ ጭካኔ በተሞላበት መልኩ ለትልቅ እንግልትና ስቃይ የተዳረጉ የነበሩ ቢሆንም ሌሎች ኢማሞችም በጊዜው ከነበሩ

ነገሥታት ጋር መሆን የሚገባውን ነገር በሰላማዊ መንገድ ለማስኬድ ያላሰለሰ ጥረት ሲያደርጉ ቆይተዋል፡፡

ኢስላማዊ መንግሥት ደግሞ መመስረት እንደማይችል በተረዱ ጊዜ በኢስላማዊ ዕውቀት አስፈላጊነትና ወደር-የለሽነት ላይ በመተኮር ህዝቡን በኢስላማዊ ዕውቀት ለማነጽ በሰፊው የማስተማር ሥራ ላይ ተጠናከሩ፡፡ በቤተሰቦቻቸው አባላትም ሆነ በሌሎች ሰዎች ከተፈጠሩ አንድም የሽምቅ እንቅስቃሴ በኢማሞቹ ትዕዛዝ የተደረገ አልነበረም፡፡ በተቃራኒው እንዲህ ዓይነቱ እንቅስቃሴ ግልጽ ትዕዛዛቸውን የሚጻረር ነበር፡፡ ምክንያቱም የኢስላም መንግሥትን ለመከላከል የተቻላቸውን ጥረት ሁሉ ያደርጉ ነበርና፡፡ የአባሲድ ኹለፋዎችን እንኳ ጨምሮ መንግሥቱን ለመከላከል እንደ እነሱ የጣረ አልነበረም፡፡

ኢማም ሙሳ ኢብን ጃዕፈር (ዐ.ሰ) ለተከታዮቻቸው የሰጡትን ምክር ማየቱ ብቻ በቂ ይሆናል፡-

*«ንጉሳችሁን እንድትታዘዙ አዛችኋለሁ፡፡ በእምቢተኝነት ብርታታችሁን/ኃይላችሁን አትጡ፡፡ ፍትሐዊ ከሆነ አላህ ህይወቱን እንዲጠብቅ ፀልዩለት፡፡ ጨቋኝ ከሆነ ደግሞ አላህ እንዲያስተካክለው ፀልዩለት፡፡ ፍላጎታችሁ ከፍላጎቱ*

*ጋር አንድ ነውና፡፡ እውነት እላችኋለሁ ፍትሐዊ የሆነ ንጉሥ ልክ እንደ አባት ነው - ለራሳችሁ የምትመኙትን ነገር ተመኙለት፣ ለራሳችሁ የማትመኙለትን ነገር አትመኙለት፡፡»*

ይህ ህዝብ ለአንድ ንጉሥ የሚያደርገውን ጥበቃ አስመልክቶ የምናገኘው ምርጥ አባባል ነው፡፡ «ለራሳችሁ የምትመኙትን ነገር ተመኙለት፣ ለራሳችሁ የማትመኙትን ነገር አትመኙለት፡፡»

እስቲ ይህንን እውነታ በዘመናችን ያሉ አንዳንድ ጸሐፊዎች የሚጽፉትን እጅግ አስነዋሪ የሆነ አሉባልታ ጋር አነጻጽሩ፡፡ ሺዓዎች ድብቅ የሆኑ አጥፊ ቡድኖች እንደሆኑ አድርገው ሲናገሩ ይደመጣሉ፡፡ ለበቀል የተነሱ አብዮተኞች እንደሆኑ አድርገው ሲያወሩ ይሰማሉ፡፡ በእርግጥ የነቢዩን ቤተ-ዘሮች አስተምህሮ የሚከተል ሰው ከሞራል እይታ አንጻር ጭቆናንና ጨቋኞችን መናቅና ከእኩይ ተግባሮቻቸው መጽዳትና መራቅ፣ መጥፎነታ-ቸውንና አስጸያፊነታቸውን ማሰብ እንዲሁም በጥላቻ ዓይን ማየትና ደጋፊዎቻቸውንና ተከታዮቻቸውን በሙሉ

መቃወምና መጥላት ይኖርበታል፡፡ እነዚህ ስሜቶች በሺዓዎች ህይወት ከትውልድ እስከ ትውልድ በልቦቻቸው ተቀርጸው ይገኛሉ፡፡ ነገር ግን አመጸኞች አይደሉም፣ እራሱን የኢስላም መንግሥት አድርጎ በሚጠራው ጨቋኝና አምባገነን መንግሥት ላይም ቢሆን በድብቅም ሆነ በግልጽ አመጽ የመቀስቀስና ችግር የመፍጠር ፍላጎትም የላቸውም፡፡

እምነቱ ከእምነታቸው የተለየ ቢሆን እንኳ የአንድን ሙስሊም ህይወት በድንገት እንዲያጠፉ ወይም እንዲከዱት የኢማሞቹ አስተምህሮ አይፈቅድላቸውም፡፡ ነገር ግን በአስተምህሮአቸው መሠረት በተውሂድና በሙሐመድ ነቢይነት (ኑቡወህ) እምነት የመሰከረ ሰው መከበር አለበት፤ ደሙ፣ ንብረቱና ቤተሰቡ የደህንነት ዋስትና ሊኖራቸው ይገባል፡፡ «የአንድን ሙስሊም ንብረት ከፍላጎቱ ውጭ መውሰድ ተገቢ አይደለም፡፡» ሁሉም ሙስሊሞች ወንድማማቾች ናቸው፡፡ ቀጥሎ እንደሚገለጸው እያንዳንዱ ሙስሊም በሌላው ላይ የወንድማማችነት መብት አለው፡፡

## 42. ሙስሊም በሙስሊም ላይ ያለውን መብት በተመለከተ ያለን እምነት (የሙስሊሞች የወንድማማችነት መብትና ግዴታ)

ድንቅና ጥብቅ ከሆኑት የኢስላም መመሪያዎችና አስተምህሮዎች አንዱ ያለምንም የትውልድ፣ የደረጃና ቦታ ልዩነት በሙስሊሞች መካከል የጠበቀ ወንድማማችነት መኖር እንዳለበት የሚያዝና የሚያስተምር ነው፡፡ ነገር ግን በሚያሳዝን ሁኔታ ሙስሊሞች ይህንን ጉዳይ ችላ ብለውታል፡፡ የዚህ ኢስላማዊ ወንድማማችነት አነስተኛው ግዴታ ቢያንስ አንድ ሙስሊም ለራሱ የሚወደውንና የሚመኘውን ነገር ለሌላው ሙስሊም መመኘትና ለራሱ የማይመኘውን ነገር ደግሞ ለወንድሙም አለመመኘት ነው፡፡ ይህንን ጉዳይ ከኢማም ሷዲቅ (ዐ.ሰ) ሐዲስ ውስጥ እንጠቅሳለን፡፡ ይህንን ግዴታ ሁሉም ሙስሊም በጥልቀት ሊያጤነው ይገባል፡፡ በአህለል ቤይቶች አስተያየት መሠረት ይህ ተግባር ትንሽ ቦታ የተሰጠው ነው፡፡ ይህ ማለት ከዚህ የበለጠ ማድረግ ከወንድማማችነቱ የሚጠበቅ ግዴታ ነው ማለት ነው፡፡ ሞራላቸውና ባህሪያቸው ከኢስላማዊው

መንፈስ ስለራቀ ሙስሊሞች ይህንን ግዴታ መወጣት አይችሉም ብሎ አንድ ሰው ሊያስብ ይችላል፡፡ እስቲ በዚህ ትንሽ ኃላፊነት ላይ በጥሞና እናስብ፡፡ ሰዎች ይህንን መመሪያ ቢያከብሩ ኖሮ ዛሬ በምድራችን ላይ ጭቆና ወይም ጠላትነት ወይም ሌብነት፣ ውሸት፣ ኃሜት ወይም የተሃድሶ አስፈላጊነት በመካከላቸው ባልኖረ ነበር፡፡ ውጤቱን ተገንዝበው በትግበራው ላይ ጥንቃቄ በማድረግ በትክክል በሥራ ላይ ቢያውሉ ኖሮ ጭቆናና ጥላቻ ከምድረ-ገጽ በጠፉና ሁሉም በወንድማማችነት መንፈስ በደስታና በብልጽግና ሰላም የሰፈነበት ኑሮ ለመኖር በቻሉ ነበር፡፡ የጥንት ፈላስፋዎች መዲናህ አል-ፈዲላህ (ትሩፋተ-ብዙ ከተማ/ግዛት) እውን በሆነ ነበር፡፡ (መዲና አል-ፈዲላህ፣ አል-ፈራቢ (259-339/872-950) የግሪክ ፖለቲካዊ ጽንሰ-ሐሳብን በመንተራስ በአስተዳደርና ፖለቲካ ፍጹም የሆነ ሞዴል የሆነ የመንግሥት አስተዳደር የገለጸበት ነው፡፡) በዚህ መሠረት ምንም ዓይነት መንግሥት፣ ፍርድ ቤት፣ ፖሊስ፣ እሥር ቤት፣ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አያስፈልግም ነበር፡፡ ከቀኝ ገዢዎችና ጨቋኞች ነፃ በሆኑ ነበር፡፡ ጨቋኞችና

አምባገነኖች በህዝቡ ላይ በደል ማድረስ ባልቻሉ ነበር፡፡ ምድራችን ምድራዊ ገነት ትሆን ነበር፡፡

በተጨማሪም ኢስላማዊ ወንድማማችነት በሰዎች መካከል ቢነግሥ ኖሮ «ፍትህ» የሚለው ቃል ከመዝገበ ቃላት ውስጥ በጠፋ ነበር፡፡ ፍትህና ህግጋቱ ባላስፈለጉ ነበር፡፡ መልካምነትን፣ ሰላምን፣ ደስታንና ብልጽግናን በመካከላችን ለማስፈን ወንድማማችነት ብቻ በቂ ይሆን ነበር፡፡ በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ፍትህና ህግጋቱ ለሰው ልጅ ባላስፈለገ ነበር፡፡ እነዚህ የሚያስፈልጉት ከሰዎች ልጆች መካከል ፍቅር ሲጠፋ ብቻ ነው፡፡ እናት ለልጆቿ መልካምና አዛኝ የሆነችው ለፍትህ መመሪያዎችና ትዕዛዛት ብላ ሳይሆን ለልጆቿ ባላት ፍቅርና ሐዘኔታ ነው፡፡ የሰው ልጅ ለምን እራሱን ብቻና ለሱ የሚስማማውን ነገር ብቻ እንደሚወድ መረዳት እንችላለን፡፡ የሰው ልጅ የሆነ ነገር ወይም ሌላ ሰው የራሱ ካልሆነ በስተቀር ማፍቀር አይችልም፡፡ እንዲሁም አንድን ነገር ወይም ሌላ ሰው ከወደደ ከግል ፍላጎቱ የላቀ አንድ መመሪያ (ለምሳሌ - በፍትህና በርህራሄ ማመን) ካለ በስተቀር ለማይወደው ለሌላ ሰው አሳልፎ መስጠት

አይቻለውም፡፡ ይህ እምነት ወይም ለመመሪያዎቹ ማደር ካለ ግን የግል ፍላጎቱን አሳልፎ በመስጠት መስዋዕት መክፈል ይችላል፡፡

እንዲህ ዓይነቱ ፍጹም የሆነ አስተሳሰብ በሰው አዕምሮ ውስጥ ሲሰርጽ ያኔ የሰው ልጅ ከማንኛውም ቁሳዊ ዓለም የላቀ ቦታ የተጎናጸፈ ይሆናል፡፡ በዓለማዊ ነገሮች ብቻ የተገደበ መሆኑ ይቅርና ለሰው ልጆች መልካም ለመሆን የመልካምነትና ፍትህ የበላይነትን ይረዳል፡፡ ለሰው ልጅ እነዚህ ፍጹም የሆኑ አስተሳሰቦች የሚያስፈልጉት በሱና በሌላው ወንድሙ መካከል እዝነትና ወንድማማችነት ሳይኖር ሲቀር ነው፡፡ ይህም ማለት ሰውየው የወንድማማችነት ስሜት እስከ ሌላው ድረስ ይህን የሚያደርገው ከራስ ወዳድነትና ከግል ፍላጎቱ የመነጨ እስከሆነ ድረስ ይህ ስሜት ውስጡ እስከሌለ ድረስ የኢስላምን መመሪያዎች ከመከተል በፍትህና በርህራሄ መልካምነት ማመን ይኖርበታል፡፡ ነገር ግን በዚህም ማመን ከተሳነው ይህ ሰው ሙስሊም ተብሎ መታሰብ አይገባውም፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ሰው የአላህ ወዳጅ አይደለም፡፡ ቀጥሎ በኢማሙ ሐዲስ እንደሚወሳው ይህ

ሰው ለአላህ ብሎ ያደረገው ምንም መልካም ነገር እንደሌለው እንገነዘባለን፡፡ ብዙውን ጊዜ የሰው ልጅ በግል ስሜቱና ፍላጎቱ ይሸነፋል፡፡ ለዚህም በፍትህ ለማመን እራሱን ማዘጋጀት እንኳ ይሳነዋል፡፡ ስሜቱንና ፍላጎቱን የሚያጠፋት ያንን ፍጹም የሆነ የእምነት ደረጃ ለመቆናጠጥ ደግሞ ይበልጥ ይቸገራል፡፡

ፍላጎቱንና አስፈላጊነቱ እስካልተሰማው ድረስ የሰው ልጆች ወንድማማችነትን ማግኘት ከባድ ሆኖ እናየዋለን፡፡ ኢማም ሷዲቅ (ዐ.ሰ) ሙዓላ ኢብን ኹነይስ ለጠየቃቸው ጥያቄዎች መልስ ሲሰጡ ጠያቂው በተግባር የማዋሉን አቅም በመጠራጠር መረዳት ከሚችለው በላይ ማስተማር አልፈለጉም ነበር፡፡ ሙዓላ እንዲህ ሲል ጠየቃቸው፡-

«*አንድ ሙስሊም በሌላው ሙስሊም ላይ ያለው መብት ወይም ግዴታ ምንድን ነው?*»

«*በሱ ላይ ግዴታ የሚሆኑ ሰባት ኃላፊነቶች/ግዴታዎች አሉ፡፡ አንዱን እንኳ ቢያዛንፍ ይህ የአላህ ወዳጅ ወይም አገልጋይ አይደለም፡፡ በእርግጥም ለአላህ ብሎ ያደረገው ምንም ነገር የለም፡፡*»

«*እነዚህ ነገሮች እንዲያው ምን ምን ይሆኑ?*»

*«እኔ አዝንልሃለሁ፡፡ ካወቅክና ከተማርክ በኋላ በተግባር ማዋል ይሳንሃል ብዬ እፈራልሃለሁ፡፡»*
*«‘ላ ቁወተ ኢላ ቢላህ’ (ኃይል በአላህ እንጂ የለም)»*

ከዚያም ሰባቱን ግዴታዎች እንደነገሩት ሙዓላ ይተርካል፡፡ በመጀመሪያ የመጨረሻ ትንሹ ግዴታ ለራስህ የምትመኘውን ለወንድምህ መመኘት እንዳለብህና ለራስህ የማትመኘው ነገር ወንድምህ ላይም እንዳይደርስ መመኘት እንደሆነ ነው፡፡

ታዲያ ይህ ቀላሉ ግዴታ ነው! ይህንን ቀላል ሆኖ እናገኘዋለን? ማለትም የአሁኑ ዘመን ሙስሊሞች? እራሳቸውን ሙስሊም ብለው የሚጠሩ ሰዎች ነገር ግን ይህንን ቀላልና ጥብቅ የሆነ በተግባር ለማዋል የተሳናቸው እንዲያው ሀፍረት ይሰማቸው ይሆን? ይህ የሙስሊሞች ኋላ-ቀርነት ችግር በኢስላም ላይ መላከኩ በጣም ይገርማል፡፡ ችግሩ የሙስሊሞቹ ሁኔታና እራሳቸውን ሙስሊም ብሎ የሚጠሩት ሰዎች ይህንን ቀላሉን ግዴታ መወጣት አለመቻላቸው ሆኖ እያለ ይህንን ግዴታ ያደረገውን ኃይማኖት ተወቃሽ ማድረጉ ግራ የሚያጋባ ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ ያለንበትን ሁኔታ ከጠቀስንና

እራሳችንን ካስታወስን በኋላ ከኢማ ጃዕፈር (ዐ.ሰ) በሙዓላ የተተረከውን ሰባቱን ግዴታዎች ቀጠል በማድረግ እንዘረዝራለን፡-

1. ለራስህ የምትመኘውን ለወንድምህም ተመኝ፡፡ ለራስህ የማትመኘው ነገር በወንድምህ ላይም እንዳይደርስ መመኘት አለብህ፡፡
2. ወንድምህን እንዲናደድ አታድርግ፤ እሱን የማስደሰትና ፍላጎቱን የመታዘዝና የመጠበቅ ፍላጎት ይኑርህ፡፡
3. በህይወትህ፣ በምላስህ፣ በእጆችህና በእግሮችህ እርዳው፡፡
4. የሚያይበት ዓይኑ፣ የሚመራበት መሪውና መስታወት ሁንለት፡፡
5. እሱ ተርቦ እያለ እስክትጠግብ አትብላ፣ በጠማው ጊዜ አንተም አትጠጣ፣ በታረዘ ጊዜም አትልበስ፡፡
6. እሱ ሠራተኛ ወይም አገልጋይ ከሌለውና አንተ ግን ካለህ፣ ልብሱ እንዲታጠብለት፣ ምግብ እንዲሰራለትና መኝታው እንዲነጠፍለት ሠራተኛህን ልትልክለት በአንተ ላይ ግዴታ ነው፡፡

7. ቃል-ኪዳኑን ጠብቅ፣ ግብዣውን ተቀበል፣ በታመመ ጊዜ ጠይቀው፣ ለቅሶውን ድረሰው፣ ከመጠየቅህ በፊት ያለበትን ችግር ተከታተልና ማድረግ የምትችለው ነገር ከሆነ ጊዜ ሳትወስድ በፍጥነት አድርግለት፡፡

በመጨረሻም ኢማሙ (ዐ.ሰ) ለሙዓላ እንዲህ በማለት ንግግራቸውን ደመደሙ፡-
*«ይህንን ካደረግክ ወዳጅነትህን በወዳጅነቱ፣ ወዳጅነቱን በወዳጅነትህ ተጎናጽፈሃል፡፡»*

ይህንን ጉዳይ በተመለከተ በርካታ ሐዲሶች ከኢማሙ ተወርተዋል፡፡ አብዛኛዎቹም «ኪታብ አል-ወሳኢል» በተሰኘው መጽሐፍ ውስጥ ተዛማጅነት ባላቸው በተለያዩ ክፍሎች ውስጥ ተሰባስበዋል፡፡

(ወሳኢል አል-ሺዓ - የሺዓ ሐዲሶች በአብዛኛው የተሰባሰቡበትና ሁሉንም የፊቂህ ቅርንጫፎች በተመለከተ ተዛማጅ የሆኑ ሐዲሶች የተጠናቀሩበት ማጣቀሻ መጽሐፍ ሲሆን የተጠናቀረውም በሙሐመድ ሐሰን አል-ሁር አል-አሚሊ (1104/1693) ነው፡፡ በኢራን ውስጥ የታተመው የቅርቡ እትም 20 ጥራዞችን ያካትታል፡፡)

አንዳንድ ሰዎች ኢማሞቹ ስለወንድማማችነት ያስተማሩት በሺዓዎች መካከል ብቻ እንደሆነ አድርገው ያስባሉ፡፡ ነገር ግን ምንም እንኳን መንገዳቸውን ያልተከተሉትንና ያፈነገጡትን ወገኖች በጥብቅ ቢቃወሙና ቢያስጠነቅቁም ሐዲሳቸውን ቢያነቡ ወንድማማችነት በተከታዮቻቸው መካከል ብቻ ነው የሚለው አስተሳሰብ ምን ያህል የተሳሳተ እንደሆነ ይረዱ ነበር፡፡ እዚህ ላይ ኢማም ሷዲቅ (ዐ.ሰ) ከሙዓዊያ ኢብን ወሐብ ጋር ያደረጉትን ንግግር ማንሳቱ ይበቃል፡-

«*የኛን መንገድ ከማይከተሉ ሰዎች ጋር ምን ዓይነት ግንኙነት ሊኖረን ይገባል?*»

«*የምትከተላቸውንና የምትታዘዛቸውን ኢማሞችህን ተመልከት፡፡ እነሱን ታዘዝ፣ እነሱን ተከተል፡፡ ኢማሞቹ ሲታመሙ ይጠይቋቸዋል (ሺዓ ያልሆኑትን)፣ ለቀብራቸውን ይደርሷቸዋል፣ ለነሱ ይመሰክራሉ፣ ይመሰክሩባቸዋልም፣ አደራቸውን መልሰው ይከፍሏቸዋል፡፡*»

ኢማሞቹ በተከታዮቻቸው መካከል ግዴታ ያደረጉት ወንድማማችነት ከተለመደው ኢስላማዊ ወንድማማችነት

የላቀ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በመግቢያው ላይ በአጭሩ ተጠቅሷል፡፡ በኢማም ሷዲቅና (ዐ.ሰ) በአባን ኢብን ተግለብ መካከል የተደረገውን ንግግር መጥቀሱ በቂ ይሆናል፡-

አባን ሲናገር፡-

«*በካዕባ ዙሪያ ከኢማም ሷዲቅ (ዐ.ሰ) ጋር ጠዋፍ በማድረግ ላይ ሳለሁ (በመዞር ላይ ሳለሁ) አንዱ ጓደኛዬን ቶሎ ሂጅ እንድረዳው በምልክት ጠራኝ፡፡*» ኢማሙ (ዐ.ሰ) ሁኔታውን አይተው ኖሮ እንዲህ አሉኝ፡-

«*አባን ሆይ! አንተን ፈልጎ ነው?*»

እኔም «*አዎን*» ስል መለስኩላቸው፡፡

«*አንተ በምታምነው ያምናል?*»

«*አዎን*»

«*እንደዚያ ከሆነ ጠዋፍ ማድረግህን (መዞርህን) ተውና ከሱ ጋር ሂድ፡፡*»

ይህንን ለማድረግ ግዴታ እንዳለብኝ ጠየቅኳቸው፡፡ እሳቸውም ግዴታ እንደሆነ ነገሩኝ፡፡ ከዚያም ልረዳው ከርሱ ጋር ሄድኩኝ፡፡ ረድቼው ከተመለስኩ በኋላ የአማኞችን መብት በተመለከተ እንዲነግሩኝ ጠየቅኳቸው፡፡

«*ይህንን ጉዳይ ባትጠይቀኝ ይሻላል*» አሉኝ፡፡

እኔ ግን እንዲነግሩኝ አጥብቄ ጠየቅኋቸው፡፡

«*ካለህ ነገር ግማሹን ለወንድምህ ስጥ*» ካሉኝ በኋላ መልከት አደረጉኝ፡፡ በጣም መገረሜን ሲያዩ፡- «*አባን ሆይ! ከራሳቸው ይልቅ ሌሎቹን የሚያስቀድሙ ሰዎችን አላህ እንደሚያደንቃቸው ታውቃለህ?*» ብለው ጠየቁኝ፡፡

እኔም፡- «*አዎ*» አልኩኝ፡፡

«*ካለህ ነገር ግማሹን በሰጠህ ጊዜ ከራስህ ኣላስቀደምከውም፡፡ ነገር ግን የተቀረውን ግማሽ በሰጠህ ጊዜ ያኔ በእርግጥ ከራስህ ይልቅ እሱን አስበለጥከው ወይም አስቀደምከው ማለት ነው፡፡*»

እዚህ ላይ ሀፍረት የሚሰማን ከሆነ እራሳችንን አማኞች ነን ብለን መጥራት የለብንም፡፡ ከኢማሞቹ አስተምህሮት በእውነቱ እጅግ ርቀናል፡፡ ይህንን ሐዲስ የሚያነብ ሰው መቼስ ልክ እንደ አባን መደነቁና መደንገጡ አይቀርም፡፡ ነገር ግን ከዚያ በኋላ ምንም ትኩረት ሳይሰጠው ይረሳዋል፡፡ ሐዲሱ ቀጥታ እንደማይመለከተውና ኃላፊነት እንደሌለበት አድርጎ በቸልታ ያልፈዋል፡፡

# ክፍል አምስት

# አል-መዓድ (ትንሳዔ)

## 43. ከሞት መነሳት (ትንሳዔ) አስመልክቶ ያለን እምነት

ከሁሉ በላይ የላቀው አላህ የሰው ልጆች ከዚህች ዓለም በሞት ከተለዩ በኋላ ዳግም ህይወት ዘርቶባቸው ቃል በገባው ቀን እንደሚቀሰቅሳቸውና ታዛገሮችን በመልካም ተግባራቸው እንደሚሸልማቸውና መጥፎ ሰሪዎችን እንደሚቀጣቸው እናምናለን፡፡ በዚህ ቀላል አገላለጽ ሁሉም ሰማያዊ ኃይማኖቶችና ፈላስፋዎች የተቀበሉት ጉዳይ ነው፡፡ ነገር ግን ሙስሊሞች በዚህ ማመን አለባቸው፡፡ ምክንያቱም ይህ ጉዳይ በቁርአን ውስጥ የተጠቀሰ ነውና፡፡ ቁርአን ደግሞ ነቢያችን (ሰ.ዐ.ወ) ያመጡት የአላህ መጽሐፍ ነው፡፡ በአላህና በመልዕክተኛው ሙሐመድ የሚያምን ደግሞ በቁርአን ውስጥ የተጠቀሱ እንደ ትንሳዔ፣ የፍርድ ቀን፣ ሽልማትና ቅጣት፣ ጀነትና ፀጋው/በረከቱ (አንነዒም)፣ እሳት (አንናር) እንደ ጀሐነም/ገሀነም (አል-ጀሒም) በሙሉ ማመን ግዴታ

ነው፡፡ በቁርአን ውስጥ ወደ አንድ ሺህ የሚሆኑ አንቀጾች የትንሳዔ ቀንን አውስተዋል፡፡ አንድ ሰው አላህን፣ ኃይሉንና መልዕክተኛውን የሚጠራጠር ሰው ካልሆነ በስተቀር ትንሳዔን የሚጠራጠርበት ምንም ምክንያት የለም፡፡ በእርግጥ ይህ ሁሉንም ኃይማኖቶች እንደማስተባበልና መጠራጠር ነው፡፡

## 44. አካላዊ ትንሳዔ (አል-መዓድ አል-ጂስማኒ) በተመለከተ ያለን እምነት

ይህ በቁርአን እንደተጠቀሰው ከኢስላም መሠረቶች አንዱ ነው፡፡

بَلَىٰ قَادِرِينَ عَلَىٰ أَنْ نُسَوِّيَ بَنَانَهُ

«*አይደለም፤ ጣቶቹን (ፊት እንደ ነበሩ) በማስተካከል ላይ ቻዮች ስንሆን (እንሰበስባቸዋለን)፡፡*» (75፡4)

وَإِنْ تَعْجَبْ فَعَجَبٌ قَوْلُهُمْ أَإِذَا كُنَّا تُرَابًا أَإِنَّا لَفِي خَلْقٍ جَدِيدٍ

«*ብትደነቅም አፈር በሆንን ጊዜ እኛ አዲስ ፍጥረት እንሆናለን? ማለታቸው (ታላቅ) ድንቅ ነው፡፡ ...*» (13፡5)

በግልጽ ለማስቀመጥ አካላዊ ትንሳዔ ማለት የሰው ልጅ አካል ከጠፋና ከወደመ በኋላ ተመልሶ መንሰራራትና መሬት ውስጥ ከበሰበሰ በኋላ ደግሞ የነበረውን ቅርጽና ሁኔታ እንዲይዝ ማድረግ ማለት ነው፡፡ ትንሳዔን አስመልክቶ በእያንዳንዱ ዝርዝር ጉዳይ ማመን ግዴታ አይደለም፡፡ በቁርአን ከተገለጸው በላይ ዝርዝር ጉዳዮች ውስጥ መግባት አስፈላጊ አይደለም፡፡ ነገር ግን በቁርአን ውስጥ የተጠቀሱትን የተወሰኑ ነገሮችን፣ ለምሳሌ እንደ አል-ሂሳብ (መመርመርና መጠየቅ)፣ ሲራጥ (ድልድይ)፣ አል-ሚዛን (ሚዛን)፣ አል-ጀናህ (ጀነት)፣ አል-ናር (ጀሀነም)፣ አል-ሰዋብ (ሽልማት) እና አል-ኢቃብ (ቅጣት) የመሳሰሉትን ማመንና መቀበል ግዴታ ነው፡፡

(አስ-ሲራጥ የሚለው ቃል በሱራህ አል-ሐምድ ውስጥ የተጠቀሰው የአላህ መንገድ እንደማለት ነው፡፡ ነገር በፍርዱ ቀን (የውመል ቂያማ) የቁስ አካል ቅርጽ ያለው ነገር እንደሚሆን ይታመናል፡፡ ድልድይ እንደሆነ አድርገው የሚገልጹ በርካታ ሐዲሶችም አሉ፡፡ ሼይክ ሳዱቅ ሲናገሩ፡- «*ስለሲራጥ ያለንን እምነት በእርግጥ እውነት መሆኑንና በጀሀነም ላይ ያለ ድልድይ መሆኑን*

*ነው፡፡ በድልድዩ ላይ ሁሉም ሰዎች የማለፍ ግዴታ እንዳለበት ነው፡፡*» አላህ እንዲህ ብሏል፡-

«***ከእናንተም ወደ እርሷ ወራጅ እንጂ አንድም የለም፡፡ (መውረዱም) ጌታህ የፈረደው ግዴታ ነው፡፡***» (19፡71))

«ይህን ጉዳይ አስመልክቶ የጠለቀና ዝርዝር የሆነ ዕውቀት ማግኘት ግዴታ አይሆንም፡፡ ይህ ዐለማዊ ሥጋ እንደነበረ ይመለሳል ወይስ ይለያል?፣ ነፍስ (ህይወት) ከአካል ጋር ትጠፋለች ወይስ የፍርድ ቀን ወደ አካል ተመልሳ ለመግባት ትጠብቃለች?፣ ትንሳዔ ለሰው ልጆች ብቻ ነው ወይስ ሌሎች እንስሳትንም ያካትታል?፣ ትንሳዔ የሚከሰተው በድንገት ነው ወይስ በሂደት ነው? ጀነትና ጀሀነም መኖራቸውን እስካመን ድረስ ቀደም ሲል የተፈጠሩ ይሁኑ ወይስ ገና የሚፈጠሩ ስለመሆናቸው፣ በመሬት ላይ ወይስ በሰማይ ላይ ወይስ በሌሎች የተለያዩ ቦታዎች ይሁኑ አይሁኑ ማወቁ አስፈላጊ አይደለም፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ስለ ሚዛን ስናምን መንፈሳዊ ነገር ይሆን ቁሳዊ ነገር ማወቅም አስፈላጊ አይደለም፡፡ ሲራጥ ሲባል ቀጭን ቁስ አካል ይሆን ወይስ መንፈሳዊ ቀጥተኛነት ይሆን ማወቁ ግዴታ አይደለም፡፡

ስለዚህ ትንሳዔን በተመለከተ ኢስላም ያስቀመጣቸው ነገሮች ጠቅለል ባለ መልኩ እንጂ በዝርዝር አይደለም፡፡ አንድ ሰው በቁርአን ከተጠቀሰው ውጭ አልፎ ዝርዝር ጉዳዮች ላይ ጥያቄ በማንሳት ከአንዳንድ ራሽናል (ምክንያታዊ) የሆነ ገለጻ ከሚፈልጉ ሰዎች የሚነሱትን ጥያቄዎች አስመልክቶ ጥርጣሬውን ለማስወገድ የሚሞክር ሰው ሥህተት ውስጥ ይወድቃል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ሰው እነዚህን ጥቅል ሐሳቦች ህዋሱን በመጠቀም ዝርዝር ጉዳይ ለማወቅ በመጣሩ በችግር ውስጥ ይወድቅና ማለቂያ የሌለው ክርክር ውስጥ ይዘፈቃል፡፡ የሥነ-መለኮት ጠበብትና ፈላስፋዎች መጽሐፎቻቸውን የሞሉበት ዝርዝር ጉዳዮች በኃይማኖታዊ መጽሐፍት ውስጥ አይገኙም፡፡ እነዚህ ፈላስፋዎችና የሥነ-መለኮት ምሁራን መጽሐፎቻቸውን በዝርዝር ጉዳዮችና ገለጻዎች እንዲሞሉ የሚያደረግ ኃይማኖታዊም ሆነ ማህበራዊ እንዲሁም ፖለቲካዊ አስፈላጊነት የለም፡፡ በነዚህ ጉዳዮች ላይ ጥያቄዎችን ማንሳት በማሰብ ኃይል መፍጀት ካልሆነ በስተቀር አንዳችም ፋይዳ የለውም፡፡ ትንሳዔን በተመለከተ ዝርዝር ጉዳዮች ውስጥ መግባት መውጣት ከማንችለው ጥርጣሬ ውስጥ ከመግባትና ከመረዳት

አቅማችን በላይ የሆነ ችግር ውስጥ ከመዘፈቅ ውጭ ጥቅም የለውም ብሎ ማለፉ በቂ ይሆናል፡፡

የትንሳዔ ቀን የመከሰቱ ጉዳይ ጥርጥር የሌለው ነገር ነው፡፡ ምክንያቱም ሁሉን አዋቂውና ሁሉን ቻዩ አላህ አሳውቆናልና፡፡ የሰው ልጅ ዕውቀት፣ ሙከራም ሆነ ሌሎች የማረጋገጫ መንገዶች ሁሉ ከሰው ልጅ የልምድ አድማስ ውጭ የሆኑትን ነገሮች ተመራምሮ ሊደርስባቸው አይችልም፡፡ የሰው ልጅ ደግሞ ከዚች አላፊ ዓለም በሞት ተለይቶ ወደ ዘለዓለሙ ዓለም ከተወሰደ በኋላ ካልሆነ በስተቀር ትንሳዔን መታዘብም ሆነ ማየት አይችልም፡፡ ስለዚህ እንዴት ነው በሙከራና በመላምት ወይም በሐሳብ መካድም ሆነ ማረጋገጥ የሚችለው? እንዲያውም ዝርዝር ጉዳዩን የማወቁ ነገር ደግሞ ከእውነት የራቀ ነው የሚሆነው፡፡ ምክንያቱም ይህንን ለማድረግ መሠረት የሚያደርገው መላምት፣ የተፈጥሮ እውቀቱንና የሚገርሙና አስቂኝ የሆኑ ውኅንብሮችን ስለሆነ ነው፡፡ ይህ የሰው ልጅ በህዋሱና በሳይንስ ማወቅ ያልቻላቸውን ነገሮች በተለምዶ ለማወቅ የሚጥርበት ተፈጥሮው ነው፡፡

ይህ የትንሳዔን እንግዳነት አስመልክቶ አለማወቁን ከሚያሳይ ሰው ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ ለዚህም አላህ በቁርአኑ ውስጥ የእንዲህ ዓይነቱን ሰው መገረም አስመልክቶ በሚከተለው መልኩ ጠቅሷል፡-

قَالَ مَنْ يُحْيِي الْعِظَامَ وَهِيَ رَمِيمٌ

**«...«አጥንቶችን እነርሱ የበሰበሱ ሲሆኑ ሕያው የሚያደርጋቸው ማነው?» አለ፡፡»** (36፡78)

የመገረሙ ብቸኛው ምክንያት ሰው ተቀብሮ ከበሰበሰ በኋላ ዳግም ህይወት ዘርቶ የተመለሰ ሰው በህይወት ዘመኑ ፍጹም አይቶ ስለማያውቅ ነው፡፡ በህይወት ዘመኑ ሬሳ ተመልሶ ህያው ሲሆን አጋጥሞት ስለማያውቅ ነው፡፡ ነገር ግን መጀመሪያ ሲፈጠር ምንና እንዴት እንደነበረ ይዘነጋል፡፡ ምንም ነገር በነበረ ጊዜና የሰውነቱ ግብአቶች የትም ተበታትነው እንደነበረ ይረሳል፡፡ ከዚያም ከዚህም ከዛም ከመሬት ተሰብስበው ማሰቢያ ያለው ተናጋሪ የሆነ ፍጹም የሆነ ሰው እንደሆነ ዘንግቶታል፡፡ አላህ በቁርአን ሲናገር፡-

أَوَلَمْ يَرَ الْإِنْسَانُ أَنَّا خَلَقْنَاهُ مِنْ نُطْفَةٍ فَإِذَا هُوَ خَصِيمٌ مُبِينٌ. وَضَرَبَ لَنَا مَثَلًا وَنَسِيَ خَلْقَهُ قَالَ مَنْ يُحْيِي الْعِظَامَ وَهِيَ رَمِيمٌ

«*ሰውየው እኛ ከፍቶት ጠብታ የፈጠርነው መሆናችን አላወቀምን? ወዲያውም እርሱ (ትንሣኤን በመካድ) ግልጽ ተከራካሪ ይሆናልን? ለእኛም ምሳሌን አደረገልን፡፡ መፈጠሩንም ረሳ፡፡ «አጥንቶችን፤ እነርሱ የበሰበሱ ሲሆኑ ሕያው የሚያደርጋቸው ማነው?» አለ፡፡*» (36፡77—78)

ለእንዲህ ዓይነቱ ሰው መሰጠት ያለበት ምላሽ የሚከተለው ነው፡-

قُلْ يُحْيِيهَا الَّذِي أَنْشَأَهَا أَوَّلَ مَرَّةٍ وَهُوَ بِكُلِّ خَلْقٍ عَلِيمٌ

«*«ያ በመጀመሪያ ጊዜ (ከኢምንት) ያስገኛት ሕያው ያደርጋታል፡፡ እርሱም በፍጡሩ ሁሉ (ሁኔታ) ዐዋቂ ነው» በለው፡፡*» (36፡79)

በሁሉም ነገሮች ፈጣሪ፣ በኃይሉ፣ በመልዕክተኛውና መልዕክተኛው ባመጣው ነገር ማመኑን የሚመሰክር ከሆነ እንዴት ትንሳዔን ሊያስተባብል ይችላል? የሰው ልጅ ሳይንስ ውሱንና የተገደበ በመሆኑ የሰው ልጅ እንዴት እንደተፈጠረና ምንም ትርጉም/ጥበብ ወይም ፈቃድ በሌለው የፍትወት ፈሳሽ (ስፐርም) ጠብታ ተቀይሮ ወደ ከፍተኛው የሰው ልጅ ፍጥረት ደረጃ እንዴት እንደተሸጋገረና እንዳደገ ማወቅ አልቻለም፡፡ ከተለያዩ ቅንጣጢቶች ከተገነባ በኋላ ጥበብ፣ አርቆ በማሰብና ስሜት ያለው ፍጡር ለመሆን እንደበቃ ዝርዝር መረጃ የለውም፡፡ ታዲያ እነዚህን እውነታዎች ከተገነዘበ በኋላ አካሉ ከበሰበሰ በኋላ ህይወት የመዝራቱ ነገር የማይመስል ነገር ሆኖ እንዴት ይሰማዋል? ከውስን ዕውቀቱና ልምዱ የተነሳ ማየት የሚችለውን ነገር እንኳን መረዳት አልቻለም፡፡ ስለዚህ ከማመን ውጭ ሌላ ምንም መንገድ የለውም፡፡ የሁሉም ነገር አስተናባሪ፣ የሰው ልጅን ከምንም የፈጠረ፣ ሁሉን አዋቂና ሁሉን ቻይ፣ የሆነው አምላክ ያስተማረው ነገር እጅ ሰጥቶ በመቀበል ይህንን እውነታ ከመመስከር ውጭ ሌላ ምርጫ የለውም፡፡ ለማግኘት የማይቻለውን ነገር ፍለጋ ዕውቀት መፈለግና

በዘመኑ ዕውቀት መግለጽ ስለማይቻለው ነገር ውስጥ መዳከር በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ሁለት ቀለማትን ለመለየት እንደሚለፋ በረሃ ውስጥ የጠፋ ሰው ነው፡፡ ራዳርና ኤሌክትሪሲቲን ያገኘና አተምን መከፋፈል የቻለ የሰው ልጅ የኤሌክትሪሲቲንም ሆነ የአተምን እውነተኛና ትክክለኛ ተፈጥሮ እስከአሁን ድረስ ማወቅ አልቻለም፡፡ ባለፉት ምዕተ-ዓመታት ውስጥ ስለነዚህ ነገሮች ቢወራ ኖሮ የሰው ልጅ የማይመስል ነገር አድርጎት እንደ ፌዝ ይቆጥረው ነበር፡፡ ስለዚህ ሥነ-ፍጥረት ላይ ስለመመራመርና ሁሉን ነገር ስለማወቅ እንዴት ተስፋ ሊያደርግ ይችላል? ስለትንሳዔ ያሉትን እውነታዎች እንዴት ሊደርስባቸው ይችላል?

አንድ ሰው ኢስላምን ከተቀበለ በኋላ የራሱን ፍላጎትና ስሜቱን መከተል ትቶ ለዚህ ዓለምም ሆነ ለወዲያኛው ዓለም የሚጠቅመውን ሥራ መሥራት መጀመር አለበት፡፡ በአላህ ፊት ደረጃውን ከፍ የሚያደርግለት ተግባር ላይ ማተኮር አለበት፡፡ ከሞተ በኋላ ስለሚጠቅመው ነገር፣ በመቃብር ውስጥ ስለሚያጋጥሙት ችግሮችና በትንሳዔ ቀን ስለሚጠብቁት ነገሮች ከወዲሁ ማሰብ መቻል

አለበት፡፡ ሁሉን አዋቂ የሆነ ንጉስ ፊት በሚቀርብበት ጊዜ፡-

وَاتَّقُوا يَوْمًا لَا تَجْزِي نَفْسٌ عَنْ نَفْسٍ شَيْئًا وَلَا يُقْبَلُ مِنْهَا شَفَاعَةٌ وَلَا يُؤْخَذُ مِنْهَا عَدْلٌ وَلَا هُمْ يُنْصَرُونَ

«***(ማንኛዋ) ነፍስም ከ(ሌላዋ) ነፍስ ምንንም የማትመነዳበትን፣ ከርሷም ምልጃን የማይቀበሉባትን፣ ከርሷም ቤዛ የማይያዝበትን፣ እነርሱም የማይረዱበትን ቀን ተጠንቀቁ፡፡***» (2፡48)